www.ethiopianorthodox.org

# የመንፈስ ነፃነት

(The release of the Spirit)

አዘጋጅ፡- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ

ተርጓሚ

ዲ/ን ደስታ ፍፁም (B.TH.MA)

ከቅ. ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ

- የመጀመሪያ ዕትም ታህሳስ 1995 ዓ.ም
- ሁለተኛ ዕትም መጋቢት 1995 ዓ.ም
- ሦስተኛ ዕትም ህዳር 2001 ዓ.ም
- አራተኛ ዕትም ሐምሌ 2001 ዓ.ም

## ማውጫ

I. መግቢያ ........ 5
1. ከኃጢአት ዕውቀት ነፃ መውጣት ........ 6
2. እግዚአብሔርን ማወቅ ........ 10
3. ከዓለማዊ እሥራት መፍታት ........ 12
4. የተመሰጠ ህይወት ........ 20
5. ትንሹ አምላክ (አምላክ ዘበፀጋ) ........ 24
6. እራስህን ሁን ........ 30
7. ማንነትህን ተረዳ ........ 33
8. ውዳሴ ከንቱ ........ 42
9. ነቀፌታ ........ 49
10. እኔነትን ከውስጥህ አስወግድ ........ 53
11. ራስን መካድ ........ 56
12. ከምድራዊ ምኞቶች ነፃ መውጣት ........ 60
13. ከስሜት ህዋሳት ተጽእኖ ነፃ መውጣት ........ 63
14. ከዓለም አንዳች አልሻም ........ 67
15. አስተማሪ እግዚአብሔር ነው ........ 70
16. አለማወቅህን እወቅ ........ 73
17. አንዳች የሌለህ ስትሆን ሁሉ የእኔ ነው አትበል.. 77

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org


18. የልብ ቅድስና ይኑርህ........................................ 80

19. ደሙን ከእጅህ እፈልጋለሁ........................................ 85

20. የአገልግሎት ህይወት........................................ 90

21. በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን። ፊል 2:5........................................ 106

22. ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ህብረት አለው 1ኛ ቆሮ 6:14........................................ 116

23. የጽሞና ጊዜ........................................ 120

24. ቅድስና........................................ 123

25. አማኑኤል........................................ 125

26. እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ........................................ 128


የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ደንብና ሥርዓት የጠበቀ

## ማስታወሻ

ይህች መጽሐፍ መንፈሳዊ እውቀትን እየተመገብኩ ላደግኩባት ለዝዋይ ሐመረ ኖኅ ቅ/ኪዳነምህረት ገዳምና እጅግ በጣም ለምወዳት ለእናቴ ለወ/ሮ አስቴር ንጉሴ ማስታወሻ ትሁንልኝ።


ስለመጽሐፉ ያለዎትን አስተያየት
በስልክ ቁጥር 12 05 87 (0911 42 89 52)
በፖ.ሳ.ቁ 80250
E-mail destaf22@yahoo.com
አዲስ አበባ
ይግለጹልኝ


## መግቢያ

የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ 3ኛ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን 117ኛ ፓትርያርክ ሲሆኑ ከ100 በላይ መጻሕፍትን በመጻፍ በዓለም ዙሪያ ላሉ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ታላቅ የሃይማኖትና የሥነ ምግባር መምህር መሆን የቻሉ የቤተክርስቲያን አባት ናቸው። ይህን በእንግሊዝኛ ቋንቋ (The release of the Spirit) በሚል ርዕስ የታተመውን መጽሐፋቸውን ከቤተመጻሕፍት ተውሼ ባነበብኩበት ወቅት ታላላቅ መንፈሳዊ ምክሮችን ስላገኘሁበት ያገኘኋቸውን ቁም ነገሮች በማስታወሻዬ አስፍሬ እኔ ከተጠቀምኩባቸው በኋላ ለሌሎች በማስነብብበት ወቅት የመጽሐፉን ጠቃሚነት ብዙዎች ስላመኑበት በተቻለኝ አቅም ያለኝን ጊዜ ተጠቅሜ ሙሉውን መጽሐፍ ለመተርጎም በመወሰን በእግዚአብሔር ፈቃድ ሀሳቤ ተሟልቶልኝ በዚህ ዓይነት መልኩ ተርጉሜ ላቀርበው በቅቻለሁ።

በመጽሐፉ ውስጥ የተለያዩና ጥልቅ የሆኑ የሥነ ምግባር ትምህርቶችን እንመለከታለን። ርዕሱን «የመንፈስ ነፃነት» ያልኩበት ዋና ምክንያት ቃሉ ከእንግሊዝኛው ርዕስ ጋር ከመጣጣሙም ባሻገር መጽሐፉ ነፍሳችን ከኃጢአትና ከበደል እስራት ስትላቀቅ ልታገኝ የምትችለውን የመንፈስ ነፃነት በግልፅ ስለሚያስረዳ ነው።

እግዚአብሔር አምላካችን ከኃጢአት ሁሉ በመራቅ የመንፈስ ነፃነትን እንድናገኝ የምናነበውንም በሥራ መተርጎም እንድንችል ለሁላችንም ቅዱስ መንፈሱን ይላክልን።

ደስታ ፍፁም

### ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ይህንን የመጀመሪያ የትርጉም ሥራዬን ለሕትመት እንዳበቃ የረዳኝን አምላኬ ልዑል እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። እንዲሁም በመንፈሳዊ ስነምግባር ላሳደጉኝ ለመንፈሳዊ አባቴ ለብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የምሥራቅ ሸዋ ሀገረስብከት ሊቀጳጳስ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ይህ የትርጉም ሥራዬ ተጀምሮ እስኪያበቃ በምክር በአስተያየትና በእርማት ጊዜውን ሰውቶ ለረዳኝ ለዲ.ዘሪሁን ሙላቱ እንዲሁም የትርጉም ሥራውን በማንበብ ገንቢ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የ4ኛ ዓመት ተማሪዎች ልባዊ ምስጋናዬን በልዑል እግዚአብሔር ስም አቀርባለሁ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



# ከኃጢአት ዕውቀት ነፃ መውጣት

ስለ መንፈስ ነፃነት በስፋትና በጥልቀት ለመነጋገር የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንመልከት።

<u>መንፈሳችንን ከምንድነው ነፃ የምናደርገው?</u>

በምድር እስካለን ድረስ ከብዙ ነገሮች እንድንታቀብና መንፈሳችንን እንድናርቅ ይህ መጽሐፍ በስፋትና በጥልቀት ይመልስልናል።

ይሁንና ከሞት በኋላ ባለን ዘላለማዊ ሕይወት ካልሆነ በስተቀር መላቀቅ የማንችላቸው ነገሮች አሉ። ይህ ነገር ምንድነው?

<u>ኃጢያትን ከማወቅ ነፃ መውጣት</u>

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ንጹሕና ፍጹም አድርጎት ፈጠረው ከዚህ የተነሣ ኃጢአትን ከነስም አጠራሯ አያውቃትም ነበር። መልካሙንና ክፋውን ከምታሳውቀው ዕፀ በለስ ከመብላቱ በፊት አዳም ልክ እንደ ሕፃን ኃጢያትን የማያውቃትና የማይሰራት ነበር።

<u>ስለዚህ ሔዋን በእባቡ በተፈተነች ጊዜ የኃጢአት ዕውቀት ስላልነበራት ተሣሣተች:</u>

እባቡም ዋሽቶ እንዲህ አላት *«በእርግጥም አትሞቱም እንደ እግዚአብሔር ትሆናላችሁ»* ዘፍ 3፣5 ሔዋን ግን እውነትን እንጂ ውሸትን፣ ማመንን እንጂ ጥርጣሬን አታውቅም ነበርና ሀሳቡን ተቀበለችው።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



አዳምና ሔዋን እንደ እግዚአብሔር ከመልካም ነገር
በስተቀር አንዳች አያውቁም ነበር፡፡ እንደ እግዚአብሔር ንጹሕና
ቅዱስ ሆኖ መኖር ምን ያህል ያስደንቅ! ይሁን እንጂ ትዕዛዝን
ከማፍረስ በኋላ ኃጢያትን አወቁ መስራትም ጀመሩ፡፡

## ኃጢአት ወደ ሰው ልጅ ገባ

ታዲያ ይህ ሌላ ዕውቀት የሰውን ዘር የተፈጥሮ
ንፅሕናውን አረከሰው፡፡ ይህም የጠቢቡ ሰሎሞንን ቃል ይጋራል
«ዕውቀትን የሚጨምር ሀዘንን ይጨምራል፡፡» መክ 1፣18
በመጀመሪያ አዳም የሚያውቀው ሔዋን ሴት፣ እሱ
ወንድ እንደሆነ ይህን የፆታ ልዩነት እንጂ የሩካቤ ስሜት
አልነበረውም፡፡ ይሁን እንጂ ህግን ባፈረሰ ጊዜ የሩካቤ ስሜት
ዕውቀት ወደ እሱ ገባ፡፡ ከዚያም የሩካቤ ሥጋ ስሜት አሳፋሪ
ስለሆነበት ራቁትነቱን መሸፈን ጀመረ፡፡ ፍርሃትም በውስጡ
ነገሠ፡፡

## ውሎ እያደር ሰው ብዙ ኃጢአት አወቀ

እንደዚህ ዓይነቱ ዕውቀት በውስጡ ከተቀረጸ ጀምሮ
አእምሮው ከራሱ ጋር የሚታገልበት የጦርነት መስክ ሆነ፡፡ ይህ
ሰው በዚህ ዓይነቱ የሀሳብ ውጥረት ውስጥ ባይሆንም እንኳን በዚህ
የሀሳብ ውጥረት ውስጥ ያሉትን ይተቻል፡፡ እርስ በእርሳቸው
በማይጣጣሙና አንዱ መጥፎ ሲሆን ሌላኛው ጥሩ በሚሆኑ
ሀሳቦች ውስጥ ይኖራል፡፡
በሀሳብ ውጥረት ከመያዝ መቼ ይላቀቅ ይሆን?
አእምሮው እግዚአብሔርን ብቻ አውቆ መልካም ነገሮች ብቻ
ማሰብ የሚችለው መች ይሆን? በልማድም ይሁን በተግባር
ካካበተው ክፋት መች ይላቀቅ ይሆን፡፡ በጠቅላላው የሰው ዘር
ሞትን ከምታስከትለው ከኃጢአት ተለይቶ በቅድስና መኖር
የሚችለው መቼ ይሆን?
ሐዋርያው ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ እንደነገረው «ወደ
ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል» 2ኛ ጢሞ 4፣8





ይህን ዓይነቱን ኑሮ መኖር የምንችለው ከሞት በኋላ ባለን
ዘላለማዊ ሕይወት ውስጥ ስንኖር ብቻ ነው፡፡
በመጨረሻም ሰው ቅድስናን ይቀዳጃል፡፡ ይህ ቅድስና
ከሐጢያት ዕውቀት የሚያገለን ነው፡፡ ይህን ቅድስና ማግኘት
የሚቻለው ያለአንዳች ምስክርነት ከጌታ ብቻ ነው፡፡
ሐዋርያው «ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል
ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ያስረክበኛል
ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም»
በማለት መልስ ይሰጣል፡፡
ይህ የሚሆንበት ከኃጢአት ስንርቅ ብቻ ነው፡፡

ይህን የቅድስና አክሊል ማግኘትና መቀዳጀት የሁላችን
ፍላጎት ነው፡፡
ስለዚህም ነው በምድር ሳለን ዕለት ዕለት ኃጢአትን
ብንሰራም እንኳን፣ ለሰራነው ኃጢአት ንስሐን እንሻለን፡፡
ምክንያቱም ማንም በምድር ላይ ለአንድ ቀን ቢሆን እንኳን በራሱ
ያለ ኃጢአት መቆየት አይችልም፡፡

## የቀደመ ክብራችንን መመለስ የምንችለው በዚህ ብቻ ነው

በዘላለማዊ ሕይወት ውስጥ ስንኖር ያ አዳም በገነት
ውስጥ ይኖር ከነበረው ሕይወት በላይ እንኖራለን፣ ከነበረውም
ቅድስና የበለጠ ቅድስና ይኖረናል፡፡ ምክንያቱም አዳምና ሔዋን
በገነት ውስጥ የነበራቸው ቅድስና ኃጢአት ሊያረክሰው የሚችል
ነበር፡፡ በዘላለማዊ ሕይወት ውስጥ ስንኖር ግን የሚኖረን ቅድስና
አንዳች ነገር ሊያጎድፈው አይችልም፡፡
ይህን ዘላለማዊ ቅድስናን ለማግኘት አዳም በገነት ውስጥ
ሳለ ይዞት የነበረውን ቅድስና ልንይዝ ግድ ነው፡፡ ይህም ማለት
ኃጢአትን ባለማወቅ በቅንነት በፍጹም ንጽሕና፣ በየዋህነት መኖር
ማለት ነው፡፡



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



<u>ኃጢአትን ከነስም አጠራሯ ከነክንዋኔው መርሳት አለብን፤</u>

ብርቱ ከሆነው ከመንፈሳዊ ሕይወት፣ ከእግዚአብሔር ፍቅር በሰማይ ላይ ካለው የሰው ዓይን ካላየው ጆሮ ካልሰማውና በሰው ልጅ ልብ ውስጥ ከማይገኘው ከሰማያዊው ነገር በስተቀር በአእምሯችን ውስጥ ምንም ዓይነት ነገር መቀረጽ የለበትም።

<u>ከዚያም ሰው ከዚህ ኃጢአት ርቋል ሊባል ይችላል</u>

በምድር ላይ ሳለን ዋናው ማወቅ ያለብን ከኃጢአት ባርነትና ከሥጋ ሥራ በመራቅ በነፃነት መኖር እንደምንችል ነው።

ይህን ነፃነት ማግኘት የምትችለው ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንድትችል ከሚያደርግህ የኃጢያት እስራት ስትፈታ ብቻ ነው።





# እግዚአብሔርን ማወቅ

ለህዝብህ ስለ መልካም ነገርና ስለመልካምነት አስተማርኳቸው ነገር ግን አንተ መልካምና ቸር፣ የሁሉ ነገር መገኛ ሆነህ ሳለ ስለአንተ አንዳችም አላስተማርኳቸውም። ይህም ስለ ሁለት ምክንያት ነው።

<u>የመጀመሪያው፡-</u> ዕውቀቱ ስለሌለኝ ነው። በጸሎቴም ስለ አንተ አንድ ነገር እንደምትገልጽልኝ አውቃለሁ። የምትገልጽልኝንም ለሁሉ እገልፃለሁ። ስለዚህ በምድር ሳሉ ሰማያዊውን ክብር ይረዳሉ።

<u>ሁለተኛው ምክንያት፡-</u> ስለመልካሙ ነገር በምናገርበት ጊዜ አንተን እንዲያውቁህ ልባቸውን እንዲያዘጋጁ እፈልጋለሁ። እለት ዕለትም አንተን እንዲያመልኩህ በአፋቸውም የምስጋናን መስዋዕት እንዲሰው አደርጋቸዋለሁ። አንተን ማወቅ የምንችለው በራሳችን ጥረት ሳይሆን በጸጋህና በመለኮታዊ ምሪትህ ነው ምክንያቱም አንተን ለማወቅ የምናደርገው መንፈሳዊም ሆነ አእምሯዊ ጥረት ጸጋንና ረድኤትን የሚሰጠን የጸሎት ዓይነት እንጂ አንተን የምናውቅበት ቀመር አይደለም። ይህ ጥረት እያንዳንዱ ሰው በጸሎቱ ባገኘው ረድኤትና ፀጋ አንተን በማወቅ አምላኬ ሆይ አንተን የማውቅበትን ረድኤትና ፀጋ ሰጠኸኝ እያሉ ይዘምራሉ።

ጌታ ሆይ ከአንተ ይልቅ ስለመልካሙ ነገር ለሰዎች በመንገሬ ይቅር ትለኝ ዘንድ እየለመንኩህ የጽሑፌን አካሄድ በፊትህ እቀይራለሁ። አንተን ለማወቅ ባደረኩት ሙከራዎች ውስጥ ስለ አንተ አምላክነት የተጻፉ ጥንታዊ ጽሑፎችንና የታሪክ መዛግብትን አገላብጫለሁ።

ሐዋርያውም *«በእነዚህ ቃላት ፊት ግራ በመጋባት እቆማለሁ»* ብሎ እንደተናገረው።

ምንም እንኳን በመንግስትህ ውስጥ ዘላለማዊነት ያለው ሰማያዊና መንፈሳዊ አካል ቢኖረንም ያን ጊዜም ቢሆን እንኳን ውሱኖችና አንተን ልንረዳህ አንችልም።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ምክንያቱም በዚያ መንግስትህ ውስጥ በዚህ አለም ስንኖር ከገለጽክልን ይልቅ ስለ አንተ ትገልጽልናለህ፤ ደስተኞችም እንሆናለን። ከዚያም መቋቋም እስክንችል ድረስ ቀስ በቀስ ብዙ ነገር ትገልጽልናለህ። ምናልባትም ስለ አንተ ብዙ ከገለጽክልን ነፍሳችን ጥልቅ በሆነ በፍቅር ስሜት «ይህ ይበቃኛል» ብላ ትጮሀለች። ነፍሳችንና ልባችን ስለ አንተ ብዙ ያውቃሉ።

ፍፃሜ በሌለው በዘላለማዊ ሕይወት ውስጥ አንተን በጥቂቱ ማወቅ እንጀምራለን። ማወቃችንም ቸርነትህን እንድንረዳ ያስችለናል።

<u>መለኮታዊነትህን የምንረዳበት ዕውቀት መቼ ይኖረናል?</u>

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «*እውነተኛ አምላክ የሆንከው አንተን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።*» ይላል ዮሐ 17፥3 አንተን ለማወቅ ቀናትና ዘመናት ሳይሆን የሚያስፈልገን ዘላለማዊነት ነው።

አንተን ለማወቅ ዘላለማዊነት ካስፈለገን፤ በምድር ሳለን ስለ ዘላለማዊነት በቂ ዕውቀት አለን?

መለኮታዊ ዕውቀት በአንድ የእርሻ ቦታ ውስጥ የተደበቀ ወርቅን ይመስላል። አንድ ገበሬ ያለውን ንብረት ሁሉ ሸጦ ይህን የእርሻ ቦታ ቢገዛ ተጠቃሚ እንደሚሆን ሁሉ፤ ሰውም ይህንን መለኮታዊ ዕውቀት ለመቀበል በውስጡ ምንም ዓይነት ባዕድ ነገር ስለማያስፈልግ በአለም ይጠቅመኛል፤ ከሁሉ በላይ ያደርገኛል ብሎ የያዘውን ነገር በመተው ራሱን በእግዚአብሔር ፊት ቢያቀርብና ለማወቅ ቢጥር በዚህ ተጠቃሚ ይሆናል።

ነገር ግን ከሁሉ በላይ እንዲያደርገው ያሰበውን የአለምን ነገር አስበልጦ ከያዘ የማይቀሟትን በጎ ዕድልን መረጠች ተብሎ ከተነገረላት ከማርታ እህት ከማርያም ጋር እንዳይቀመጥና ማንም ከዚህ ምንጭ ቢጎነጭ ዳግሞ ከማያስጠማው የሕይወት ውሃ እንዳይጠጣ በራሱ ላይ መሰናክል እያበጀ ነው።

በልባችንም ውስጥ ይህ ዓይነቱ ዕውቀት እንዲኖረን እመኛለሁ። ምክንያቱም ከዚህ ዓለም ተጽእኖ የምንላቀቅበት ነውና።





# ከዓለማዊ እሥራት መፈታት

ከአንድ ከመንፈሳዊ አባት ጋር በበረሃው የአዋሽ መንገድ ላይ የሰውን ልጅ ስለሚመለከቱ ነገሮች በመነጋገር ወደ ገዳም እየሄድን ነበር።

በስጋ ሳለን መንፈሳችንን ከዚህ ከሥጋ ተጽእኖ ማላቀቅ መቻል አለብን ስንል፦ በአጠቃላይ በዓለም ከአሉ ነገሮች መራቅ እንድንችል ነው። ስለዚህ ሰው ይህን አደረገ ማለት በእግዚአብሔር ልጆች ሕይወት ውስጥ ያለውን ሰላምና ነፃነት ያገኛል ማለት ነው።

ውድ ወንድሜ አንድ ሕፃን ከተጠመቀ በኋላ ልክ እንደመጀመሪያው እግዚአብሔር ንፁሕ አድርጎ እንደፈጠረው መንፈሱ በነፃነት እንደምትሆን ታውቃለህ ከዚያም በኋላ አካባቢውን ይመስላል። በአከባቢው ያሉ ብዙ መሰናክሎች አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር እንዳያደርግና በእግዚአብሔር ሕግ እንዳይመራ ያደርጉታል። እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጆች ከእነዚህ ሁሉ አካባቢያዊ ተጽእኖዎች ማለትም ከአለማዊነት፣ ከስሜታዊነትና ከሰው ሰራሽ መሰናክሎች ከተከበቡበት አካበቢያዊ ተጽእኖ መራቅ እንዴት ይችላሉ?

በውይይታችን ላይ መነኩሴው እንዲህ አሉኝ፣ አንዳንዶች «*ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም*» ማቴ 18፥3፤ የሚለውን ቃል ሳይገነዘቡ አካላዊ ሕፃንነትን ይፈልጋሉ። ነገር ግን ጌታ ማለት የፈለገው በመንፈሳቸው ንፁሐን እንደሚሆኑት እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ በስተቀር የእግዚአብሔርን ክብር አትወርሱም ለማለት ፈልጎ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



## ህዋሳዊ ተጽእኖ

አባ መቃርስ በአንድ ወቅት ዝሙት በእኔ ላይ አይሰለጥንብኝም የገንዘብ ፍቅር አይገዛኝም የብስጭትና የቁጣ ስሜት የለብኝም ብሎ ከሚመጻደቅ ከአንድ ወጣት መነኩሴ ጋር ተገናኘ።

አባ መቃርስም ያ ወጣት ዝሙት በእኔ ላይ አይሰለጥንብኝም ብሎት ነበርና ሴት በምታይ ጊዜ ምን ይሰማሃል ብሎ ጠየቀው፤ መነኩሴውም ሴት እንደሆነች ይሰማኛል ግን የዝሙት ስሜት እንዳይጠናወተኝ ርቃታለሁ አለው።

ዳግመኛም የገንዘብ ፍቅር አይገዛኝም ብሎታልና በበረሃ ላይ ገንዘብ ቢያገኝ ስሜቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ጠየቀው፤ መነኩሴውም ገንዘቡን ከድንጋይ እንደሚለየውና ነገር ግን ብሩን ቢመለከትም ከገንዘብ ፍቅር እንደሚርቅ ነገረው። አባ መቃርስም የቁጣና የብስጭት ስሜት የለብኝም ብሎት ነበርና አንድ ሰው ቢዘልፈው ምን እንደሚለው ለሦስተኛ ጊዜ ጠየቀው። መነኩሴውም ስድቡ ቢቆጠቁጠውም እንደማያቄም መለሰለት። አባ መቃርስ አሁንም ድረስ ደካማ እንደሆነና ብዙ ጥረት እንደሚጠበቅበት በመንገር ማስተማር ጀመረ።

ከዚህ ታሪክ እንደምንረዳው የስሜት ተጽእኖ በወንድና በሴት በአሮጊትና በልጃገረድ፣ በቆንጆና በአስቀያሚ መካከል ልዩነት ያመጣል።

ስለዚህ ከቅዱስ መቃርስ ጋር የሚነጋገረው መነኩሴ ድንጋይን ከገንዘብ መለየት ከቻለ፣ ሴትን ሲያይ የዝሙት ስሜት የሚሰማው ከሆነና ሲሰድቡት ስድቡን ከምስጋና ከለየው የእርሱ ቅድስና (መመጻደቁ) ከንቱ ነው።

## የምስጋናና የዘለፋ ልዩነት ምንድነው?

በአንድ ወቅት አንድ አባት ቅ.መቃርስን ምክር ይለግሰው ዘንድ ጠየቀው ቅዱሱም ሂድና ሙታንን አመስግናቸው ብሎ





አዘዘው እሱም ሄዶ አደረገው ማንም ግን አልመለሰለትም ነበር። ቅዱሱም ዳግም ሂድና ስደባቸው ብሎ አዘዘው፤ ሄደና አደረገው በዚህም ጊዜ ምንም መልስ አላገኘም ነበር።

ከዚያም መነኩሴውም እንዲህ አለው «አንተም በአለም ሳለህ ልክ እንደዚሁ በአለማውያን ዘንድ የሞትክ መሆን አለብህ።»

አንድ ባለፀጋ ሰው በገዳም ውስጥ ላሉ መነኮሳት ብር ይዞላቸው መጣ አበምኔቱም የተግባር ትምህርት ያስተምረው ጀመር፦ ብሩን በፊቱ አስቀመጠና ደወል ደውሎ መነኮሳቱን ሰበሰበ፤ አበምኔቱም መነኮሳቱን ለባለፀጋው ሰው ከልብ የመነጨ የፍቅር ሰላምታ እያቀረቡ የፈለጉትን እንዲወስዱ ነገራቸው። እነሱ ግን ለሀብቱ የድንጋይን ያህል ክብር አልሰጡትም ነበር። በህይወታቸው ከመማረኩ የተነሣ መነኩሴ ለመሆን ጥያቄን አቀረበ። ህይወታቸው ተጽእኖ አድርጎበታልና።

ውድ ወንድሜ አለምና ሥጋችን በእኛ ስሜት ላይ ብዙ ተፅእኖ ያስከትላሉ። ይህንም ተጽእኖ አለምንና ግዑዝ ነገሮችን ከመጀመሪያ ተፈጥሮአቸው በላይ ውብ፣ ማራኪና ውጤታማ ሆነው እንዲታዩን ያደርጋል። ይሁንና መንፈሳችን ከዚህ አለም ተጽእኖዎች ሲላቀቅ የስሜት ተጽእኖዎቻችንም እግረመንገዳቸውን ይቀንሳሉ። በሌላ አነጋገር ከአለም ጭንቀቶች ይላቀቃሉ። ከዚያም አዲስ የሆነ መንፈሳዊ ግንዛቤን ያዳብራሉ።

ከቤተሰቦችህ ለብዙ ጊዜ ርቀህ በምትመለስበት ጊዜ ቤተሰቦችህ በጠለቀ ፍቅርና በከፍተኛ ናፍቆት ሊያቅፉህ እንደሚችሉ ትገምታለህ፤ ነገር ግን ይህ ፍቅርህ ለሌሎችም የምትለግሰው መሆን አለበት።

ከአለም ተጽእኖዎች ርቆ ለሰው ሁሉ አንድ ዓይነት አመለካከት ያለው ማንም ሰው ዘመዱም ሆነ ባዳ በአደጋ ውስጥ ቢሆን ራሱን መስዋዕት አድርጎ ለማዳን ይጥራል።

የመንፈሱም አገልግሎት ከስሜቱ ተጽእኖ በላይ ነው። በመንፈሣዊ ህይወት ስትኖር በተቻለህ መጠን በስሜትህ ተጽእኖ ስር ላለመውደቅ ጣር። ከዚያም ለነገሮች ሁሉ የተለየ ግንዛቤ ስለሚኖርህ በሥጋና በአለም ምኞት አትያዝም። ልክ በሰማይ እንዳሉት እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች እንደመላእክቱ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ትሆናለህ:: ጌታ በተራራው ላይ እንደተናገረው«ዓይንህ እንግዲህ ጤናማ ብትሆን ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል::» ማቴ 6፥22

በነገሮቹ ጥልቅ ሀሳብ ውስጥ ገብተን ከመነኩሴው አባት ጋር የተነጋገርነው ስለዚህ ርዕስ ጉዳይ ብቻ አይደለም:: አንድ ሰው መንፈሣዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ግንዛቤ እንዲኖረው ጥረት በሚያደርግበት ጊዜ ህዋሳዊ የስሜት አገልግሎቱን ተመልክተናል:: የስሜት ህዋሶቻችን አካላዊና ውሱኖች ስለሆኑ ወሰን ወደሌለው ወደ እግዚአብሔር መንፈስ መቅረብ አይችሉም::

በስሜት ህዋሶቻችን የምንተዳደር ከሆነ እግዚአብሔርን ሊያሳውቁን ይቅርና መልካሙንና ክፉውን እንድንለይ አያስችሉንም::

ሐዋርያቱ እንኳን ወደ ጌታ «ጌታ ሆይ አጋንንት እንኳን በስምህ ተገዝተውልናል እያሉ በደስታ በተመለሱ ጊዜ ተሳስተው ነበር:: ጌታም... በዚህ ደስ አይበላችሁ አላቸው» ሉቃ 18፥10-20

ነፍስ ገዳይም ነፍስ ካጠፋ በኋላ የሰራው ሥራ ኃጢአት ሆኖ ሳለ የጀግንነት ሥራና የደስታ ስሜት ሊሰማው ይችላል::

ውድ ወንድሜ በጸሎትህ፣ በጾምህና በምልጃህ ጊዜ ኃጢአትህን በምትናዘዝበት ጊዜ በተለያዩ ሀሳቦች ልትከበብ ትችላለህ:: ምናልባትም እነዚህ ሀሳቦችና ስሜቶች አንተነትህ የፈጠረው እንጂ ትክክለኛ ወይም እውነተኛ ስላልሆኑ ራስህን ከእነዚህ አርቅ::

ሌላው ላሳውቅህ የምፈልገው ነገር አንዱ መንፈሳዊ የሆኑ ነገሮችን መከተል በሚፈልግበት ጊዜ ሌላኛው ደግሞ አለምንና በዙሪያዋ ያሉትን መሆን ይመኛል:: ለምሳሌ ሐና የሳሙኤል እናት በቤተ መቅደስ ውስጥ ከነፍሷ በመቃተት በጌታ ፊት ብትጸልይም እንኳን በዙሪያዋ ስላሉ መሰናክሎች ግን አንዳች አልተጨነቀችም:: ካህኑ ኤሊም እንደሰከረች ስለቆጠራት «ስካርሽ እስከ መቼ ነው? የወይን ጠጅሽንም ከአንቺ አርቂ» 1ኛ ሳሙ.1፥1 በማለት ተናግሯል::

አንተም ልክ እንደ ሀና በምልጃና በጸሎት በምትያዝበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ብቻ መቃተት ስላለብህ በዙሪያህ ላሉ ነገሮች ቦታ አትስጣቸው:: በዙሪያህ በሚፈጠሩ ነገሮችና ድምፆች አትሳብ:: ምናልባትም አንዳንድ ሰዎች እየጸለይክ ሳለ ከአጠገብህ





ወሬ ሊያወሩ ይችላሉ:: አልያም ሰላም የሚነሱ ረብሻን ሊፈጥሩ ይችላሉ ወይም ቀልብህን ስለሚስቡ ጉዳዮች ሊያወሩ ይችላሉ፤ አንተ ግን እነዚህ ሁሉ ነገሮች ህሊናህን እንዲገዙ ቦታ አትስጣቸው:: ምክንያቱም አንተ ከእነዚህ ነገሮች ርቀህ መንፈሳዊ በሆነ አለም ውስጥ ገብተህ ስለመንፈሣዊ ነገር ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገርክ ነውና:: ስለዚህ ነገር ሳወራ የዮሐንስ ሐጺር (ዮሐንስ አጭሩ) ታሪክ ትዝ ይለኛል:: አብዛኛውን ጊዜ ዮሐንስ ለብዙ ሰዓት በተመስጦ በሚሆንበት ጊዜ በአከባቢው ሰዎች ሆን ብለው እሱን ለማወክና ለመረበሽ ማራኪ የሆኑ ወሬዎችን ያወሩ ነበር:: እሱ ግን የሚያወሩትን ሊያዳምጥ ቀርቶ ድምፃቸውን እንኳን አይሰማም ነበር:: እንዲያውም አንዶንዶቹ በወሬያቸው ላይ ጩኸት እየቀላቀሉ እኒያን ማራኪ ቃላት ይደግሟቸው ነበር:: ምንም እንኳን ይህን ያህል ቢፈታተኑም እሱ ግን አንዳች አልሰማቸውም:: የዮሐንስ ይህን ዓለም ረስቶ በወዲያኛው አለም መመሰጡ ምንድነው ስንል ለእርሱ በጣም ጠቃሚ በሆነ ምጡቅና ጠሊቅ ነገር ውስጥ መንፈሱ ስለሰጠመች ነው፤ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ዮሐንስን ስለፀሎትና ስለ ስርዓቱ ይጠይቁታል:: እርሱ ግን ሁል ጊዜ ሲመልስላቸው በተመስጦ ውስጥ የሚታየው ነገር ከዚህ ከቁሳዊ አለም ጋር አንዳች ግንኙነት የለውም:: ስጸልይም ያኛው ዓለም ከዚህኛው ዓለም ይልቅ ይቀርበኛል ይላቸው ነበር:: በእርግጥም እሱ ሲጸልይ የዚህ ዓለም ጫጫታና ሁካታ አይረብሸውም ምክንያቱም ከስሜት ህዋሳቱ አገልግሎትና ከሥጋ ሥራ ግዛት ውጭ ነው::

<u>መንፈስህን ከሰው ዕውቀት ግራቅ</u>

አሁን መንፈስህ ከሰው ዕውቀት የራቀች እንድትሆን እመኛለሁ:: ምክንያቱም *«እግዚአብሔር የዚህችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን?»* 1ኛ ቆሮ 1፥20 በድጋሚም የዚህች አለም ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነውና::

*«እሱ ጥበበኞችን በተንኮላቸው የሚይዝ ደግሞ ጌታ የጥበበኞችን አሳብ ከንቱ እንደሆነ ያውቃል ተብሎ ተጽፎልና»* 1ኛ ቆሮ 3፥20



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



የሰው ልጅ ተፈጥሮ ከመጀመሪያው ጀምሮ ውሱን ቢሆንም ቅሉ ገና ሲፈጠር የነበረው ዕውቀት ከአሁኑ ይሻል ነበር። እግዚአብሔርም ከፈጠረው በኋላ በእርግጥም መልካም እንደሆነ ተመለከተ። የሰው ልጅ ከውድቀቱ በኋላ ሞትን ለምታስከትለው ኃጢአት፣ በአእምሮው ላይ ትልቅ አሻራ ጥላ ለምታስከትለው ኃጢአት፣ በአእምሮው ላይ ትልቅ አሻራ ጥላ ለምታልፈውና ለዚህች ዓለም ሥርዓት ተገዢ ሆነ። ለፍርድም ተወቃሽና ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የማይቻለውና የማይገባው አደረገችው። እነኚህ ራሳቸውን በአለም ዕውቀትና ሥርዓት ብቁና ንቁ የሚያደርጉ እንዲሁም ባላቸው ዕውቀት የሚመኩ ከእግዚአብሔርና ከመንፈሳዊ ነገር የራቁ ናቸው። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ «ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በሚገልጥ ነገር እንጂ....» «...መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊ ነገር ጋር አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም።» ቆሮ 2፣4 ይላል።

ውድ ወንድሜ የሰው ልጅ ዕውቀት ምን ያህል ከንቱ እንደሆነ ተመልከት እግዚአብሔር የአለምን ጥበብ እንደሚንቅ ሁሉ ሰማያዊ ዕውቀትን ደግሞ ይደግፋል። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሰማያዊ ዕውቀት ሲያጸና «በሽማግሌዎች መከካል ግን ጥበብን እንናገራለን፣ ነገር ግን የዚህኛን ዓለም ጥበብ አይደለም። የሚሻሩትን የዚህችን ዓለም ገዢዎች ጥበብ አይደለም ነገር ግን እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን፣ ተሰውሮ የተነበረውን የእግዚአብሔር ጥበበ በምሥጢር እንናገራለን።» 1ኛ ቆሮ 2፣6 7 ይላል።

እናም የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመረዳት ከፈለክ በመጀመሪያ መንፈስህን ከአለም ዕውቀት አግልል። ስለዚህ እንደአላዋቂና ማንኛውም ዕውቀት እንደጎደለው ሰው ለማወቅ በእግዚአብሔር ፊት ቅረብ። ከዚያም ፍጹም ከሰው ልጅ ዕውቀት በሚለይና መንፈሳዊ በሆነው ዕውቀት ትሞላለህ። ይህም ዕውቀት ያልያዘው ዕውቀት የለም። «መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳን ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና» 1ኛ ቆሮ 2፣10





ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሀሳብ ሲጋራ «ማንም ራሱን አያታል ከእናንተ ማንም በዚህች አለም ጥበበኛ የሆነ ቢመስለው ጥበኛ ይሆን ዘንድ ሞኝ ይሁን» 1ኛ ቆሮ 3:18

በአንድ ወቅት አንድ እጁ የሰለለች ሰው ይፈውሰው ዘንድ ወደ ጌታ መጣ። ጌታም እጁን ይዘረጋ ዘንድ አዘዘው፤ ሰውየውም ዘረጋ እንደ ሌላኛይቱም ሆነለት ማቴ 12፤10:13። ይህ ተአምር የጌታን ኃይል ሲገልጥ፡ የሰው ልጅን ጥበብ ከእግዚአብሔር ጥበብ ሲያነጻጽር ምን ያህል ከንቱ እንደሆነ ያሳያል። ነገር ግን ይህ ሰው ሰዎች እንዲፈውሱት ዕድሉን ሰጥቷቸው ቢሆን ኖሮና አዋቂው ሰው እጅህን ዘርጋ ቢለው እጁ እንደሰለለች ስለሚያውቅ እንዴት? ብሎ በተከራከረ ነበር። እንዴት የሰለለች እጅ ልትዘረጋ ትችላለች መዘርጋት የሚቻለኝ ቢሆን ኖሮ ወደ አንተ መምጣት ለምን አስፈለገኝ? በመጀመሪያ እኔን ለማዳን አንድ ነገር አድርግ ከዚያም መዘርጋት እችላለሁ። በማለት በተሟገተ ነበር።

ነገር ግን ይህ ሰው ራሱን እንደ አላዋቂ ስለአደረገና ሁሉን ማድረግ ወደሚችለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሄደ ሊፈወስ ችሏል። ምክንያቱም እሱ የሰለለች እጅ አትዘረጋም የሚለውን የሰውን ጥበብ ቸል ብሏልና። ይህ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ ዕውቀት የተናቀበት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ተመሣሣይ ክንዋኔዎች አሉ። ይኸውም ለሰው ልጅ አእምሮ ቢከብድም ተራራን ከቦታው ወደ ሌላ ቦታ ማንቀሳቀስ፣ በባህር ላይ መራመድ የመሳሰሉትን ያካትታል።

የሰዎች ጥበብ እግዚአብሔርን ባህርዩንና ህጉን በራሳቸው ዕውቀት እንዲመረምሩት ቢያስችላቸውም ይህ ጥበብ ጥቂት ሰዎችን የእነሱን ዓላማ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመመልከት ሕገ ቤተክርስቲያንን በመያዝ የእነሱን ዕውቀት ሳያሞካሹ በእምነት እንዲቀበሉ ያስችላቸዋል።

በራሳቸው ዕውቀትና ጥበብ የሚመኩ ሰዎች እግዚአብሔርንና ባህርዩን በእምነት በመቀበል ፈንታ በራሳቸው



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



የዕውቀት ቀመር ሊመረምሩት ይወዳሉ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ይኸው ሰብዓዊ ዕውቀትና ጥበብ ያላቸው ሰዎች የራሳቸውን ዕውቀት በመተው መጽሐፍ ቅዱስንና ሕገ ቤተክርስቲያንን በማመሳከር ከዕውቀታቸው በላይ የሆነው እግዚአብሔርንና ባህርዩን ይረዳሉ፡፡

ሌላኛው አባባል የእግዚአብሔር ልጆች ማንኛውንም ነገር ያለ ምንም ተቃውሞ ይቀበላሉ፡፡ እንዲህም ይላሉ «ጌታ ሆይ በቀይ ባህር ላይ እንድንሄድ ትፈልጋለህ? መልካም እንሄዳለን ምክንያቱም የማንጠፋበትንና የማንሰጥምበትን መንገድ ታዘጋጅልናለህና»

አንድ የሚነገር ታሪክ አለ ሙሴ እጁን በባህር ላይ ውሃውን ለመክፈል በዘረጋ ጊዜ ውሃው አልተከፈለም ነበር፡፡ ነገር ግን ሙሴ በተራመደ ቁጥር ባህሩ ይከፈል ነበር፡፡ ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ባይመዘገብም ሰብዓዊ ዕውቀትን ምን ያህል ውድቅ እንደሚያደርጉት እንመለከታለን፡፡





# የተመሰጠ ሕይወት

በመፈሳዊ ሕይወት ውስጥ በአለም ከመኖር ከአለም ውጭ በመሆን ሕይወትን መምራት የበለጠ ተስፋ አለው፡፡ በአንድ ሰው በአለም የአገልግሎት እሩጫ ውስጥ እግዚአብሔርን ለማግኘት በሚያደርገው ትግል እጅግ ብዙ የአለም መሰናክሎች አሉ፡፡

ውድ ወንድሜ እውነት እልሃለሁ ልክ ወደ ካይሮ ለክብረ በዓል በተመለስኩ ጊዜ በከተማው ሁካታና ጫጫታ እጅግ ተረበሽኩ፡፡ በውስጤም እጅግ እየተበሳጨሁ ጉዞ ጀመርኩ፡፡ በዚያም በትራንስፖርት ብዛት፣ በሰዎች ትርምስ በመኪና ጥሩምባና በተለያዩ ድምፆች እጅግ ታወኩ፡፡ በዚህ ሁከት ውስጥ ሳለሁ በገዳም አገኘው የነበረው ሰላምና ደስታን ስላጣሁ ጥሩ ስሜት አይሰማኝም ነበር፡፡

የቤቱን በር ዘግቼ ለጸሎት በተነሣሁ ጊዜ እቸገር ነበር፡፡ እግዚአብሔርን ከማግኘት የሚከለክሉኝ ብዙ መሰናክሎች እንዳሉ ይሰማኛል፡፡ ስለዚህም መጸለይ ስላልቻልኩ ከቤቴ ወጥቼ ጥቂት ስልጣኔ ባለበት፣ ታላላቅ ህንጻዎች ባልተገነቡበትና በነዋሪዎች ብዛት ወዳልተጨናነቀ ቦታ ሄድኩ፡፡ ከሰዓታት ጉዞ በኋላ ጥቂቱን ፍላጎቴን የሚያሟላልኝ ቦታ አገኘሁ፡፡ ያለምንም መታወክ እጸልይበት የነበረውን ገዳም (ተራራ) እየናፈኩና ስለ እሱ እያዘንኩ ወደ ቤቴ ተመለስኩ፡፡

የገባነው የቀኖናና የሱባኤ ቀናት ሲፈጸም አስቀድመን ወደ ነበርንበት የደመቀ ከተማ ተመለስን፡፡ ይሁንና ተራራው ላይ እናሳልፍ የነበረው መንፈሳዊ አገልግሎት ከህሊናዬ አልጠፋም፡፡

ውድ ወንድሜ ነፍስህ ከጽንፍ እስከ አጽናፍ እንደሚበሩ ወፎች ነፃነትን ትሻለች፡፡ ከማንኛውም ከኃጢያት እስር ነጻ ሆነው አምላካቸውን እንደሚያመሰግኑ እንደመላእክቱ መሆንም



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ትፈልጋለች። እንደመላእክቱ ያለማቋረጥ ምስጋናን ማቅረብ ካልቻልክ ቢያንስ ቢያንስ ቤተ ክርስቲያን ባወጣችው መርሀ ግብር መሠረት መንፈሳዊ አገለግሎትን አድርግ።

ከእስካሁኑ ትንታኔ ጫጫታና ሁካታ በማይኖርበት መንደር ላሉ ገበሬዎችና መርከበኞች በተመስጦ እግዚአብሔርን ማግኘት እንዴት እንደሚቀላቸው ተረዳሁ። ዳግመኛ ከሥጋ ሥራና ከኃጢያት እስራት ተፈትን በምንጸልይበት ጊዜ ከእግዚአብሔር፣ ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር ህብረት እንደሚኖረን እረዳለሁ።

ስለዚህ ነገር ከአንድ መንፈሳዊ አባት ጋር ከተነጋገርን በኋላ ካላቸው መንፈሳዊ ልምድና ተሞክሮ ሲያካፍሉኝ በመጀመሪያዎቹ በብህትውና ህይወታቸው ለአንድ ወር እንዴት እንዳነበሩ፣ ማንንም እንዳላዩና ከማንም እንዳልተገናኙ በመንፈሳዊ ጽናታቸው ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገሩና ሠይጣንን እያሳፈሩ ይህን ወር እንዳሳለፉ አወጉኝ። በእርግጥም በዚህ ወር ነፍሳቸው ቅድስናን፣ ለኃጢአታቸው ሥርየትና ቃል ኪዳን እንዳገኙ ነገሩኝ።

ከዚህ በኋላ እኚህ አባት በጸሎት ቤታቸው ሆነ ከዚያ ውጭ ቢሆኑም አንድ ዓይነት ስሜት እንደሚኖራቸው በማሰብ ከቤታቸው ወጡ።

ስለዚህ እጅግ ጥልቅ ስለሆነው ስለ መንፈሳዊ ማዕረግ ልግለጽልህ። የመጀመሪያው ማዕረግ በአራቱም አቅጣጫ ስለሚመጡ ነገሮች ማሰብ ነው። የሁለተኛው ደረጃ አራቱንም አቅጣጫ መርሳት ነው። በዚህ ጊዜ በአከባቢህ ስላሉ ነገሮች ምንም ሳትጨነቅና ሳትናፍቅ በቤትህ ውስጥ በጸሎትም ሆነ በተመስጦ መሆን ትችላለህ። ከተፈጥሮ ህግ በላይ በሚሆን በሌላ ዓለም ትኖራለህ። ከዚያም በቤትህ ውስጥ ትሆን በውጭ ስለመሆንህ የምታውቀው ነገር አይኖርም። በምድር ሆነህ ሰማይ ወደ አንተ ቢመጣ ወይም ወደ ሰማይ ብትነጠቅ እንኳን ምንም የምትለየው ነገር አይኖርህም።





ውድ ወንድሜ አንድ ነገር ልንገርህ፣ በአካለ ሥጋ ይሁኑ በአካል ነፍስ መሆናቸውን እንኳን ሳይቀር ለይተው የማያውቁ ነበሩ። እነ ቅዱስ ጳውሎስ 1ኛ ቆሮ 12፡2 ሌሎችም መንፈሳውያን አባቶች።

ይህ ርዕስ መንፈሳችንን በቦታ ከመገደብ የምናርቅበትና ራዕይ የሆነውን ሌላውን ክፍል እንድናስብ ይመራናል።

ከፍቁረ እግዚእ በዮሐንስና በቅዱስ ጳውሎስ የሕይወት ልምድ ስለ ራዕይ ሰምተናል። አባቶቻችን ከአካባቢያቸው ርቀው በቃላት ሊነገርና ሊገለጽ ስለማይቻለው ያዩትን ለመግለጥ ጊዜው አይበቃም።

አንድ መንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ስለ ነበር ካህን ታሪክ አስታውሳለሁ። ካህኑ በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ እንዲህ ወደ ሚል ቃል ደረስ «ዐይኖቹን ወደ ላይ አንሣ» ካህኑም ዐይኖቹን ወደ ላይ ቀና አደረገ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ፍጹም ጸጥታ ሆነ። ደቂቃዎች ካለፉ በኋላም ካህኑ በተመስጦ እጅግ በመገረም በዝምታ ወደ ላይ ይመለከት ነበር። ከብዙ ጊዜ ቦኋላ ህዝቡ በትጋትና በተመስጦ ወደ ቆሙት ካህናቸው በጸጥታ ይመለከቱ ነበር። ካህኑም ዐይኖቹን መለሰና ጸሎቱን በተመስጦ ቀጠለ፤ ነገር ግን ብዙ ሰዓት በማለፉ ሳይሆን ከልብ በመነጨ ስሜት እንጂ፤ ሥርዓተ ቅዳሴውን ካጠናቀቁ በኋላ ከተከታዮቹ አንዱ ምን እንደተደረገ ጠየቀው ካህኑ ግን በሁኔታው ግራ ስለተጋባ ሊመልስ አልፈቀደም። በኋላም በመበረታታት እንዲህ አለ «ዐይኖቼን ወደ ሰማይ ባቀናሁ ጊዜ የቤተ ክርስቲያኑ ጣራና ጉልላት ሳይከልለው በመስዊያው ላይና በሰማይ መሀከል እጅግ ረጅም መሰላል ተመለከትኩ ከደቂቃዎች ቦኋላ ወደ ፍሬ ቅዳሴዬ ተመለስኩ።

ይህ አንዳንድ ሰዎች የገዳማዊ ህይወትን አማራጭ የሌለው የአገልግሎት መንገድና ወደ ሰማይ መቅረቢያ መንገድ አድርገው ማሰባቸው እውነት መሆኑን ያረጋግጥልኛል። በገዳማዊ ህይወት ውስጥ ተመስጦ፣ ብህትውናና ያላሰለሰ ጥረትና ተጋድሎ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ማድረጋችን መንፈሳችንን ከሐጢያት እንዲርቅና ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡





# ትንሹ አምላክ (አምላክ ዘበጸጋ)

*ከሰማይና ከምድር ስለሚበልጡትና አስቀድሜ ስለጀመርኩት ርዕስ ጉዳይ ለመቀጠል አሁን ደግሞ ወደ ገዳም እየሄድኩ ወይም በገዳም ደጅ ተቀምጬ ሳይሆን ከመነኩሴው አባቴ ጋር ከጸሎት ቤቱ ፊት ለፊት በሚገኘው ተራራ ላይ አብሬ ነኝ፡፡*

ውድ ወንድሜ ነፍስህ ከኃጢያት እስር ተላቅቃ በነጻነት መሆንን መፈለጓ እውነት እልሃለሁ ምን ማድረግ እንዳለባት በደንብ አውቃለች፡፡ ትልቅነቷንም በደንብ ተገንዝባለች፡፡

የእግዚአብሔር ወዳጅ! ይህን ነገር ለመገንዘብ በህብረት ልንመለከተው የግድ ነው፡፡ በውስጣችን ያላወቅነውና ያልተረዳነው ዕምቅ ችሎታ እንዳለን ካለፈው ተሞክሯችን፣ ከአሁኑ ኑሯችንና ከሚመጣው ህይወታችን ማወቅ እንችላለን፡፡ ሰው ብቻ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳያ እንደተፈጠረ ማወቅ አለብን፡፡ ዘፍ 1፡27 ስለዚህ አንተ ማነህ? ቢሉህና ራስህን እንድታስተዋውቅ በተጠየቅክ ጊዜ «የእግዚአብሔር አምሳያ ነኝ» በማለት በልበ ሙሉነትና በእርግጠኝነት መልስ፡፡

የእግዚአብሔር አምሳያ ነህ ማለት ዘላለማዊና ህያው መሆንህን ያረጋግጣል፡፡ ሰው ህያው በሆነው በእግዚአብሔር አምሳያ ከተፈጠረ በኋላ ይጠፋልን? እስኪ የሰማይን ጫፍ የነኩ ከሚመስሉ ተራሮች፣ ውቅያኖሶች፣ ባህሮች፣ ሠበማይ ላይ ካሉት ከአንጸባራቂዋ ጨረቃና ከብርሃናማዋ ፀሐይ ምን ያህል የከበርክ መሆንህን አስተውል፡፡ ዳግመኛም ጥቅጥቅ ካለው ደንና ለጥ ካለው ማራኪ ሜዳ፣ እንዲሁም አለምን ያጠፋል ከሚባለውና ከተፈጥሮ ኃይል የበላይ መሆንህን አስተውል፡፡ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ሰማይና ምድር ያልፋሉ እንዳለው እኚህ ሁሉ ያልፋሉ፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር አምሳያ የተፈጠርክ አንተ ህያውና ዘላለማዊ ነህ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



## አንተ ምድርንና በውስጧ ያሉትን የምትገዛ ነህ

ውድ ወንድሜ አንተ በምድር፣ በውስጧና በላይዋ ካሉት፣ በእግዚአብሔር ከተፈጠሩ፤ እግዚአብሔር እንዲያስቡ ጸጋውን ከሰጣቸውና እንዲናገሩ ካደረጋቸው መላእክቱ በላይ መለኮታዊ ፍጥረት አንተ ብቻ ነህ:: አንተ እግዚአብሔርን የምታመልክበትና የምታውቅበት ጸጋው የተሰጠህና እርሱም በአንተ ደስ የሚሰኝብህ ፍጡር ነህ:: አንዳንዴ ከአንተ በላይ እንደሆኑ የምታስባቸው ፍጡራን ሁሉ ከአንተ በላይ ሳይሆኑ አንተን የሚያገለግሉ ናቸው:: የተሰጠህን ኃይልና ፈቃድ በአግባቡ ከተጠቀምክ ሁሉን ማድረግ ትችላለህ::

ይኸውም እግዚአብሔር አስቀድሞ ሁሉን ከፈጠረ በኋላ በስተመጨረሻ የእነዚህ ሁሉ ፍጥረታት ገዢ እንድትሆን ፈጠረህ:: ዘፍ 1:26-28:: ስልጣንህ ምን ያህል እንደሆነ ታያለህ! አሁን ስታየው ግርማው የሚያስፈራህ አንበሳ፣ በኃይልና በጉልበት በልጠ የሚታይህ ጅብ ሌሎችም የምትፈራቸው አራዊቶች በገነት ውስጥ ሳለህ አገልጋዮችህ እንደነበሩ አታስተውልም? ይሁን እንጂ ይህ ስልጣን በገነት ውስጥ ያከተመ አይምሰልህ:: ለጻድቅ ሰው በማንኛውም ጊዜ ይህ ስልጣን ይኖረዋል ከብሉይ ኪዳን ጥቂት ምሳሌዎችን እንመልከት፣ በአንድ ወቅት ሶምሶን ወደ ተምና ወርዶ ሳለ የአንበሳ ደቦል እያገሣ ወደ እርሱ መጣ ጠቦትም እንደሚቆርጥ በእጁ ምንም ሳይኖረው ቀራረጠው መሣ 14:5-6፣ ዳንኤልም ከግርማቸው ብዛት በሚያስፈሩ በአንበሶች ጉድጓድ ተጥሎ ሳለ አንዳች የፍርሃት ስሜት አልነበረውም፣ ዮናስ በአሳ አንበሪ ሆድ ውስጥ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት ቢያድርም ለእርሱ ምንም ማለት አልነበረም፣ ሠለስቱ ደቂቅም በሚያስፈራና በሚንቀለቀል እሳት ውስጥ ተጥለው ሳለ አንዳች የፍርሃት ስሜት አልነበራቸውም:: ስለዚህ ነው ጻድቅ ሰው ዛሬ አለም እየፈራቸው ያሉትን አራዊት እንደፈለገውና እንዳሻው ማዘዝ ይችላል ያልነው:: በሐዲስ ኪዳንም ተመሳሳይ ምሳሌን እናገኛለን፣ ቅዱስ ጳውሎስ በእፉኝት በተነደፈ ጊዜ ሰዎች በእውነት ይህ ሰው አምላክ ነው በማለት ተደነቁበት:: የሐዋ.ሥ. 28: 3-7 አንተ ከሰው ውጭ ሆነው የተፈጠሩትን ሁሉ የማጥፋት ኃይል አለህ::





ውድ ወንድሜ በኃጢአትህ ምክንያት፣ በሥጋ ግዛትና በፍርሃት ውስጥ የታሰረች ነፍስህ ምን ያህል ስልጣን እንዳላት አስተዋልክ! አሁንም ከፈቀድክ ካለችበት የሥጋ ግዛት ነፃ ወጥታ ወደ ቀደመ ክብሯ ለመመለስ ትሻለች::

## አንተ መለኮታዊ ፍጥረት ነህ!

እግዚአብሔር ወልድ *«በእኔ ኑር እኔም በአንተ ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ አይችልም»* ዮሐ 15:2 ብሎ የተናገረልህ አንተ ልዩ ፍጥረት ነህ:: እግዚአብሔር በልብህ ደጅ ቆሞ ደጃፍህን የሚያንኳኳ ከዚያም ገብቶ እራቱን የሚበላና እንዲሁም መኖሪያው ያደረገህ ክቡር ፍጥረት ነህ ዮሐ.ራ. 3:20::

አንተ የእግዚአብሔር አምሳያና ከመለኮታዊ ባህርዩ ተካፋይ ነህ ክብር ምስጋና ለእርሱ ይሁንና ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ራሱ ምን እንደተናገረ እንመልከት *«እኔ የአለም ብርሃን ነኝ»* ከዚያም ለአንተ እንዲሁም ለወንድምህ *«እናንተ የአለም ብርሃን ናችሁ»* ዮሐ 5:14 ይላል::

የክብር ጌታ እንዳለው እግዚአብሔርን ለመምሰል ከፍተኛ ተጋድሎ ያስፈልጋል:: *«የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ»* ዮሐ. 5:4 መላእክቱና ሊቃነ መላእክቱ ያላገኙትን እድል ያገኘህና ልጄ ብሎ ሊጠራህ የፈቀደልህ አንተ ብቻ ነህ:: አንተም መለኮታዊ ፍጥረት ነህ::

አንተ ጌታ ውሃ እያፈሰሰ እግርህን ያጠበልህና ያበሰልህ ነህ:: ሐዋርያውም እንዳለው የሰውነትህ ብልቶች የክርቶስ ብልቶች ናቸው:: 1ኛ ቆሮ 6:15

የእግዚአብሔር ቤተመቅደስና የመንፈስ ቅዱስ ማደርያ የተባልክ አንተ ብቻ ነህ:: 1ኛ ቆሮ 3:16



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



መላእክቱ አንተን ለመምሰል የሚመኙህ የጌታን ቅዱሱን ሥጋውን ክቡሩን ደሙን የምትቀበልና ጌታም ከእርሱና ከአባቱ ጋር ህብረት እንዲኖርህ የፈቀደልህ አንተ ብቻ ነህ። ዮሐ. 17:21

### መላእክቱ እንዲያገለግሉህና እንዲጠብቁህ የተፈጠርክ አንተ ብቻ ነህ

«የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል» መዝ 34:7 ተብሎ እንደተፃፈ

ውድ ወንድሜ ጌታ ሎጥን ለማዳን ወደ ሰዶም ሁለቱን መላእክት እንደላከ አታስተውልምን? ዳንኤል ከግርማቸው ብዛት መላእክት እንደላከ... በሚያስፈሩ በአንበሶቹ ጉድጓድ ተጥሎ ሳለ በመላእክቱ ምክንያት የአንበሶች አፍ ተይዞ ከመበላት እንዴት እንደጠበቁት?፣ ኤልሳዕም በጦርነት ሳለ አጠገቡ ላለው አገልጋይ ያይ ዘንድ «ከእኛ ጋር ያሉት እነሱ ጋር ካሉት ይበልጣሉ አትፍራ... አቤቱ ያይ ዘንድ ዐይኖቹን እባክህ ግለጥ» 2ኛ ነገ 6:15-17 ብሎ እንደጸለየና በጸሎቱም ምክንያት እንዳየ አታስተውልምን? ዳግመኛስ ኤልያስ ከቁጥቋጦ ስር ተኝቶ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ እንዴት እንደመገበውና በዚህም 40 ቀንና 40 ሌሊት ያለ አንዳች እረፍት እንዴት እንደተጓዘ አታስተውልምን? ነገ 19:5-9

የባቢሎን ሰዎች ዳንኤልን ወደ አንበሶች ጉድጓድ ጣሉት በዚያም ለ7 ቀን ተቀመጠ። በዚያም ሰባት አንበሶች ነበሩ። በዚህ ጊዜ አንበሶቹ ዳንኤልን ይበሉት ዘንድ የተለመደ የምግብ ወጪያቸውን ከለከሏቸው። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ዳንኤልን እንዴት ከእነዚህ አናብስት አፍ እንደጠበቀውና በነብዩ ዕንባቆም አማካኝነት እንዴት እንደመገበው አታስተውልም።

ወዳጄ ሆይ መላእክት ስለአንተ ያላቸውን አገልግሎትና ተራዳኢነት እንዳልተርክልህ ጊዜ ያጥረኛል። በእውነት እልሃለሁ አንተ የከበርክ ፍጥረት ነህ።





### አንተ አምላክ ተብለህ የተጠራህ ነህ!

ውድ ወንድሜ አንተ በእግዚአብሔርና በህዝብ አፍ አምላክ ተብለህ የምትጠራ ነህ «እኔ ግን አማልክት ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ» መዝ 82:6 እግዚአብሔር ሙሴን አለው «እይ እኔ ለፈርኦን አምላክ አድርጌሃለሁ» ዘጸ 7:1 ነገር ግን አምላክነቱ የባህርዩ ሳይሆን የፀጋ አምላክነት ነው። የዚህ ጥቅስ ትርጉም ምንም ይሁን ምን ያንተን በእግዚአብሔር ዘንድ ያለህን ትልቅነት ያሳያል።

### አንተ በሰማይ ለማሰርና ለመፍታት ሥልጣን አለህ!

አንተ በትክክል ልዑላዊ ነህ ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንተ መልካም ሥፍራን ሊያዘጋጅልህና ተመልሶ መጥቶ ሊያከብርህ እንዲህ በማለት ወደ ሰማይ አርጓል።«እናንተ የአባቴ ቡሩካን ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግስት ውረሱ» ማቴ 25:34

እግዚአብሔር የመንግስቱን መክፈቻ ስለሰጠህ ከዚህ በላይ ልትመሰገንና ልትወደስ አይገባህምን?

«በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፣ በምድር የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል» ማቴ 18:18 ተብሎ የተነገረልህ ነህና በተጨማሪ ትፈርድና ይቅር ትል ዘንድ ሥልጣንን ሰጠህ። ይህ የሚሆነው የመቅደሱ አገልጋይ የተመረጠ ካህን ለመሆን ራስህን ለአገልግሎት ስታዘጋጅ ብቻ ነው። ይህ ሁሉ ሥልጣንና አለቅነት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠህ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



## አንተ የእግዚአብሔር ወዳጅ ነህ!

ሰዶም ከመጥፋቷ በፊት እግዚአብሔር ጥልቅ በሆነ ጥበቡ እንዴት ለአብርሃም ፈቃዱን እንደገለጸለት አስታውስ፣ «እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን? አብርሃም በእውነት ታላቅና ብርቱ ህዝብ ይሆናል፣ የምድር አህዛብ ሁሉ በእርሱ ይባረካሉ» ዘፍ 18፡ 17-16

አብርሃምም በጉዳዩ ላይ እግዚአብሔርን እየወቀሰ በወዳጅነትና በነፃነት ከእግዚአብሔር ጋር ይወያይ ዘንድ ተፈቀደለት። «በውኑ ጻድቁን ከሐጢያተኛው ጋር ታጠፋዋለህ?... እንደዚህ ያለ አድራጎት ከአንተ ይራቅ ከአንተ ይራቅ... የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን? ዘፍ 18፡ 25-26

በእርግጥም በደንብ የሚተዋወቁ ናቸው፤ ከጌታው ጋር ያደረገው እንደነበር ዓይነት ንግግር ብቻ አልነበረም ወይም የፈጣሪና የፍጡር ስሜትም አልነበረም ንግግራቸው የወዳጅነት ነበር።

እግዚአብሔር ህዝቡን ሊያጠፋ ባሰበ ጊዜ ሙሴ ስለህዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲሁ በወዳጅነት «አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው፤ ያለዚያ ግን ከጻፍከው መጽሐፍ እባክህ ደምስሰኝ አለ። ዘፍ 32፡32 እያለ ይነጋገራል።

ወዳጅ ሆይ አንተ በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ያህል ትልቅ እንደሆንክ ተረዳህ? እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ ሥልጣን ሰጥቶህ ሳለ በዚህ ክብርህ ላይ ሰይጣን እንዲጫወትበት ፈቀድክለት?

እንዲህ የምታደርግ አይመስለኝም።





## እራስህን ሁን

የመልአኩ ድምጽ በለሆሳስ ስለነበር ተኝቶ የነበረው ሰው በድምጹ አልተረበሸምና በእርጋታ እንዲህ ሲል መለሰ፣ ጌታዬ ጠባቂዬና አገልጋዬ ምን ማለትህ ነው? መልአኩም መለሰ «ይህን እልሃለሁ አሁን የአንተን ባህርይ አጥተህ የሌላን ሰው ባህርይ ተላብሰሃል። ይህ እንደ ምሳሌ የወሰድከው ሰው ራሱን ስላመጻደቀ በዐይኖችህ ፊት ከፍ ከፍ ያለ ሆነ። በማንኛው መንገድ የእርሱን አሰርና ፈለግ መከተል ጀመርክ። ይህ የምትከተለው ሰው ትልቅነትን ካገኘ እንደ ተከታይነትህ አንተም ትልቅነት ይሰማሀል፤ የወደቀና የተዋረደ ከሆነ አንተም እንዲሁ የተዋረድክና የወደክ ትሆናለህ። ፈለጉን ሁሉ የምትቀበልና የምትከተል ከመሆንህ የተነሣ ለአላማው ከእርሱ ይልቅ ትቆምለታለህ። መመሪዎቹንም እንደ እውነት ትቀበለዋለህ። የሚናገራቸውን ንግግሮች ሁሉ እንድትከተለውና እንድታመልከው ያደርግሃል።

የተኛውም ሰው መልአኩ የተናገረው ነገር እውነት እንደሆነ ቢሰማውም ይህን ሰው ያለስህተት ብከተለው መጥፎ ጎኑ ምንድነው በማለት ተናገረው መልአኩም መለሰለት። መመሪያዎቹና ሀሳቦቹ ሁሉ ጥሩ እንደሆኑ እንዴት ታውቃለህ አለቃህ እንደማይሳሳት ትገምታለህ? የሰው ልጅ ሆኖ ጥፋት ወይም ውድቀት አያገኘውም ትላለህ? እናም የእርሱን መርህ ብቻ የምትከተል ከሆነ በተሳሳተ ጊዜ እንዴት ታውቃለህ? የዚህን ሰው ሀሳብ የሚቃወም ሰው ቢመጣ እንኳን ተቃውሞውን ለመስማት አትፈቅድም። ወቀሳው የጌታህን ሀሳብ የሚጣረስ ስለሆነ ያለምንም ግንዛቤ ልትነቅፈውና ልትከለክለው ትጥራለህ።

ይህም የተኛው ሰው መልአኩ ንግግሩ በቀጠለ ጊዜ ዐይኖቹን እያሻሸ የተመለከተው በህልሙ ይሁን በውኑ እንደሆነ ለመገንዘብ ተነሣ። መንፈስህ በእስር ናት! ነፃ መሆንን ትመኛለች! ነገር ግን አትችልም ምክንያቱም በዚ ሰው የሀሳብ ተጽእኖ ታስራለችና። ይህ ሰው የሚነግርህ እሱ እንድታውቅለትና



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



እሱን መከተል እንድትችል የሚያደርግህን ነገር ብቻ ይነግርሃል:: በዚህ ሀሳብ ዘንድ ከሌላ ምንጭ ያገኘኸውን የራስህ ዕውቀት እንኳን እውነት ስለመሆኑ በዚህ ሰው መታረም አለበት:: በራስህ አንዳች ማድረግ ስለሚሳንህ አንተነትህን ታጣለህ:: ችግር በሚገጥምህ ጊዜ ለነገሮች መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ እሱ መፍትሔ እስኪሰጥህ ድረስ የእርሱን እርዳታ ትጠብቃለህ::

አንድን ነገር አስመልክቶ ውሳኔን ብታደርግም እንኳን ውሳኔህን ሊቀይርብህ ይችላል:: መቼም ከአንተ በኩል ምንም ዓይነት የተቃውሞ ድምጽ መስማትን አይፈልግም:: ማድረግ የምትችለውና በህይወት ዘመንህ የምታገኘው ነገር ቢኖር በዚህ ሰው መቀረጽን ብቻ ነው:: እግዚአብሔር ሲፈጥርህ የሰጠህን ስብእና አጣህ፤ በተመሳሳይ መልኩ የሰውየውንም ውጫዊ ገጽታ ብታገኝም እንኳን ባህርዩን ሙሉ ለሙሉ ልትወርስ አትችልም ምክንያቱም የኑሯችሁ ሥርዓትና የአስተዳደጋችሁ ሁኔታ የምትለያዩበት መሠረታዊ ነገር ነውና:: የውሃ ላይ ኩበት እንደሆንክ ይሰማኛል::

የተኛውም ሰው እነዚህ ልብ የሚነኩ ንግግሮች ሁሉ አዳመጠ፤ በእርግጥ የዚያ ሰው ሥርዓት መመሪያ እጅግ የሚያታክት እንደነበር አወቀ:: ይህም መልአኩን መፍትሔ ይፈልግለት ዘንድ ለመጠየቅ ድፍረት ሰጠው:: መልአኩም መለሰለት፣ አሁን የምነግር ታሪክ ከዚህ እንደሚለይ እልሃለሁ: እግዚአብሔር ልጆቹ በባህርያቸው ጠንካራ እንዲሆኑ ከእርሱ ጋር እንዲነጋገሩ ይፈቅዳል ኤርምያስ እግዚአብሔርን ምን እንዳለው ተመልከት: «አቤቱ ከአንተ ጋር በተሟገትኩ ጊዜ አንተ ጻድቅ ነህ ነገር ግን ከአንተ ጋር ስለፍርድ ልናገር:: የኃጢያተኞች መንገድ ስለምን ይቀናል? በደልንስ የሚያደርጉ ሁሉ ስለምን ድህነት ይሆናል?» ኤር 12:1 ለስሙ ምስጋና ይሁንና አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት እንደተነጋገረ ስማ: «እንደዚህ ያለው አድራጎት ከአንተ ይራቅ የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?» ዘፍ 18:25 በድጋሚ ሙሴን እንመልከት «ከመግባትህ ተመለስ፣ ለህዝብም በክፉታቸው ላይ ራራ» ዘጸ 32:12





ከዚያም የተኛው ሰው መልአኩን አሁን ምን እንዳደርግ ትመክረኛለህ ሲል ጠየቀው:: መልአኩም እንዲህ ሲል መለሰ፣ ራስህን ሁን! በህይወትህ ብዙዎችን አድምጥ፣ ብዙ መጻሕፍትንም አንብብ የምትፈልገውንም መርምር ነገር ግን በጥሩና በመጥፎ ሀሳቦች መካከል ያለውን ሊለይ የሚችል ማገናዘቢያ ይኑርህ:: ከመንፈሣዊ ህይወትህ፣ ከተፈጥሮህ፣ ከአካባቢህ ከሥራ ቦታህና ከዕድሜህ ተሞክሮ የሚስማማህን ቅሰም:: የተለያዩ ወደ እግዚአብሔር የምትቀርብባቸው መንገዶች እንዳሉ ዕወቅ:: ምናልባት ለሌሎች የሚስማማ መንገድ ለአንተ ላይስማማህ ይችላል:: ያንተ መንገድ የሰው መንገድ ሳይሆን ጌታ ያዘጋጀልህ መመሪያ ነው::

በዚህ ጊዜ ሰውየው ራሱን አዲስ ሰው፣ ከመጥፎ ነገር የራቀ፣ ከማንኛውም እስር ነፃ የሆነ ራሱን አዲስ ሰው ሆኖ አገኘው:: ከእርሱ በምንም የማይበልጠውን ሰው ላለመከተል ውሳኔ አደረገ::



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



# ማንነትህን ተረዳ

## ፍጹም መሆን ትፈል ጋለህ?

ነፍስህ ከእስር ተፈትታ ነጻነት ወዳለበት ቦታ እንድትሄድ ትፈልጋለህ? ከሁሉ በፊት ከአለማዊ ምኞት፣ ከአለማዊ ዕውቀት፣ ከስሜትህ ፦ጽእኖና አለም በውስጥ ከሳለችብህ ነገር ሁሉ ራቅ።

በመጀመሪያ ራስህን በእግዚአብሔር ፊት እንደ ትንሽ አቅርብ። ትክክለኛ ማንነትህን ዕወቅ። አንተ ማነህ? አንተ ከመሬት አፈር ተዘግነ የተፈጠርክ አይደለህምን? በትክክል ከመሬት የምታንስ ነህ፤ አንተ ምንም ማለት አይደለህም። ሰማይና ምድር ተፈጥረው ሳሉ ያልነበርክበት ጊዜ ነበር። ከዚያም እግዚአብሔር ከምንም ፈጠረህ። በመጀመሪያ እግዚአብሔር አፈርን ፈጠረ፤ ከዚህ ከአፈር አንተን አበጀህ። ታዲያ ለምን ራስህን ታመጻድቃለህ? የምትመጻደቅስ አንተ ማነህ? ምንም ማለት ስላልሆንክ በትህትናና በፍርሃት ራስህን ዝቅ አድርግ። የተሰበረ ልብንና የተዋረደን መንፈስ ይዘህ በእግዚአብሔር ፊት ቁም። የተዋረደን ልብና የተሰበረን መንፈስ እግዚአብሔር ይወዳልና። ከአፈር እንደተፈጠርክ አትርሳ።

አሁን ምንም እንዳልሆንክ ተረድተሃል? በተጨማሪ እልሃለሁ ከምንም ታንሳለህ። ከምንም ያነሰ መሆን ደግሞ አለመኖር ነው። በሰው ከሚፈጸም ሐጢያት አለመኖር





ይበልጣል። ምክንያቱም መጽሐፉ የልቡ ሃሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ አየካ ዘፍ 6፤5 ይላል።

መልካም ነገሮችን በውስጥህ ካገኘህ ባንተ ምክንያት ሳይሆን ከእግዚአብሔር እንደመጡ እርግጠኛ ሁን። ምክንያቱም ጌታ እንዳለው እሱ ብቻ መቼም ጥሩ፣ ፍፁምና ቅዱስ ነውና።«መልካም የሆነ አንድ ነው» ማቴ 19:17

መልካም ነገሮችን በውስጥህ ባገኘህ ጊዜ ኩራትና ትምክህት አይሰማህ። በመመጻደቅ ራስህን ከመልካም ነገር ጋር አታገዳድር፤ ለእግዚአብሔር ምስጋናን አቅርብ እንጂ በጽድቅህ አትመካ፤ ይህ ከእግዚአብሔር እንጂ ከአንተ አይደለምና። የመልካም ነገር መገኛ እሱ ብቻ ነው። እርሱ በባህርዩ መልካም ነው። አንተ ከእግዚአብሔር ውጭ ባይ ነህ። አንዳች ልትሰራም አትችልም። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ለአንተ አታድርግ አይገባህምና። ለምሳሌ ያህል አንተ እንደ ጨረቃ ብታበራ፣ ብርሃንህም አድጎ እንደ ጨረቃ ለብዙዎች ሲደርስም በእነዚህ ሁሉ ጨረቃ በጨለማው ሰማይ ላይ ነግሳ የምትሽከረከረው ብርሃኗን ቀን ከፀሐይ በመሰብሰብ እንጂ በራሷ የብርሃን ባለቤት እንዳልሆነች አስታውስ። ፀሐይ ከሌለች ጨረቃ በራሷ ልትኖር አትችልም። ስለዚህ ጨረቃ ስለ ብርሃኗ በፀሐይ ፊት መናገር ትችል ይሆን? ወዳጄ ሆይ አንተም በእግዚአብሔር ፊት ስለ ራስህ ማውራት አትችልም።

ባንፃሩ ደግሞ በውስጥህ ክፋትና መጥፎ ነገርን ካገኘህ በምኞትህ ምክንያት ከራስህ እንደተፀነሰች ዕወቅ። እንድትገዛትም



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



<u>እንድትገዛህም ኃይሉ በአንተ ሥር ነው</u>:: ዘፍ 4፤7 ለመልካም ነገር ካልሆነ በስተቀር ምንም ዓይነት መጥፎ ነገር ከእግዚአብሔር አይመጣም:: አምላካችን አለምንና በውስጧ ያሉትን ሲፈጥር በቅዱሳን እጆቹ እንደፈጠረ ስንመለከት ባህርዩ ከመጥፎ ነገር ጋር ህብረት እንደሌለው እንረዳለን::

እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበር ዘፍ 1፤31

ውድ ወንድሜ አሁን ማን መሆንህን አወክ? ራስህን መካድህ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነት የሚመራ ህግ መሆን እንዳለበት ተረድተሃልን? አንተ የምታስፈልግ ነህ አልልህም፤ አስቀድመን እንዳየነው አንተ ምንም አይደለህምን? ራስህን ዝቅ አድርግ የሚለውን ቃል መጠቀም አልፈልግም:: ምክንያቱም አንድ ፍጡር ራሱን ከታላቅ ማዕረግ ወደ ዝቅተኛ ክብር ቢያመጣና ሰማያዊ ሆኖ ምድራዊ ፍጡር ቢሆን ይህ ሰው ራሱን ትሁት አደረገ ይባላል አልያም ትሁት ሆነ ልንለው እንችላለን እንጂ አስቀድመን ከአፈር ያልተፈጠርንና ከአፈር በላይ ሥልጣን የሌለን እኔና አንተ ትሁት ሆኑ ቢባል ወይም ስለ ትህትና ሊነገርልን አይገባም:: ውድ ወንድሜ ራስህን ስለመካድ ያልኩህ ሁሉ ራስህን እንድታውቅ ነው:: ከዚያም ምን ማድረግና በራስህ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖር እንደማትችል ትረዳለህ:: ትህትናንና ይቅር ባይነትን ከራስህ የምታገኘው ሳይሆን ከእግዚአብሔር የምታገኘው ነው::

ይህን ቃል እንመልከት እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የአለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ ብርቱንም ነገር





እንዲያሳፍር የአለምን ደካማ ነገር መረጠ፤ እግዚአብሔርም የሆነውን ነገር እንዲያጠፉ የአለምን ምናምንቴ ነገር የተናቀውን ነገር ያልሆነውን ነገር መረጠ::: 1ኛ ቆሮ 1፤27-29 ይህ ምን ማለት ነው? የእግዚአብሔር መንግሥት ለሞኞች፣ ለደካሞች ለተናቁትና ለተዋረዱት ነው? አስቀድሞ እግዚአብሔር የተማሩ ሰዎችን እንደነ ሙሴ፣ ቅ.ጳውሎስና አርሳንዮስ፤ ሌሎቹም እንደ ፈላስፎቹ Athenagorus and pentinus የመሳሰሉትን ቅዱሳን፣ ከጀግኖችም እንዳነ ሶምሶን፣ እንደ ኃያሉ ሙሴ ያሉትን ክብርና ሞገስ ያለውን ዳዊትን ሲመርጥ እናያለን::

<u>*እነዚህ ሁለት ነገሮች እንዴት ህብረት ይኖራቸዋል?*</u>

እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የአለምን ሞኝ ነገር መረጠ፣ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የአለምን ደካማ ነገር መረጠ፣ እግዚአብሔርም የሆነውን ነገር እንዲያጠፉ የአለምን ምናምንቴ ነገር የተናቀውን ነገር ያልሆነውን ነገር መረጠ 1ኛ ቆሮ1፤27-29:: ማለቱ ደካሞችን፣ የተናቁትንና የተዋረዱተን ብቻ ይመርጣል ማለት ሳይሆን የአምላካችን ስሙ ይባረክና ዕውቀት ኖሯቸው ራሳቸውን እንደአላዋቂ የቆጠሩትን፣ ኃያል ሆነው ደካሞች የመሰሉትን ባለጠጎች ሆነው ድህነታቸውን የሚያሳዩትን እና የመሳሰሉ ሰዎችንም ሲያጠይቅ ነው::

ለዚህ አብነት ሙሴን ስንመለከት ሙሴ የግብጻውያንን ጥበብ ጠንቅቆ የተማረ ነበር፤ ይሁን እንጂ በዕውቀቱ በሚኮራበትና በኃይሉ በሚመካበት ጊዜ እግዚአብሔር አልጠራውም:: ነገር ግን ሙሴ ወደ ፈርኦን የምሄድ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



የእስራኤልንም ልጆች ከግብጽ የማወጣ እኔ ማንኝ? ዘጸ.3፤11 እኔ አፌ ኮልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ፤ ትናንት ከትናንት ወዲያ ባሪያህም ከተናገርከው ጀምሮ አፌ ትብ ሰው አይደለሁምን? ዘጸ 4፤10 ባለ ጊዜ ግን እግዚአብሔር ጠራው።

በድጋሚ ቅ.ጳውሎስ የኦሪትን ህግ በመምህሩ በገማልያል እግር ስር እየተማረ ያደገና የአይሁድን ህግና ሥርዓት ጠንቅቆ ያወቀ ነበር። ነገር ግን ለተማረው ህግ ጠበቃና ለቆመለት ሥርዓት ቀናተኛ በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር አልጠራውም። የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ የአስተዋዮችንም ማስተዋል እጥላለሁ ጥበበኛ የት አለ? ፀሐፊስ የት አለ የዚህች አለም መርማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚህችን አለም ጥበብ ሞኝነት እንደሆነ አላደረገምን 1ኛ ቆሮ 1፤19 እኔም በድካምና በፍርሃት በብዙ መንቀጥቀጥም በእናንተ ዘንድ ነበርኩ እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን ለመግለጥ ነበር እንጂ 1ኛ ቆሮ 2፤3-4። ብሎ ዕውቀቱ እንደማያድነውና እንደማያስመካው በጻፈ ጊዜ እግዚአብሔር መረጠው እንጂ ለተማረው ህግ ጠበቃና ለቆመለት ሥርዓት ቀናተኛ በሆነ ጊዘ እግዚአብሔር አልጠራውም።

ወዳጅ ሆይ በራስህ ዕውቀትና ባህል እግዚአብሔርን ማገልገል የምትችል ይመስልሃልን? አንተ ምስኪን! እውነት እልሃለሁ ከራስህ ዕውቀት ልማድ እስካልተላቀቅህ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ልትቀርብ አትችልም። ሥራህን በራስህ ለመተግበር የምትሮጥ ከሆነ እግዚአብሔር ስራህን አይባርክልህም ሥራህም





ውጤታማ አይሆንም። ምናልባት ህዝቡ አለም ያዘጋጀልህን የምሥክር ወረቀትና በሳይንስ የተደገፈ ካርድ ሊያቀርብልህ ይችላል ነገር ግን ከእግዚአብሔር ማግኘት የሚገባህን አይሰጥህም።

ውድ አዋቂ ወንድሜ እግዚአብሔር አሁንም በዚህ ባለንበት ዘመን ወደ ባህር በመሄድ ያልተማረውን አሳ አጥማጅ ሰው ሊጠራው ይችላል። ከዚያም ወንጌላዊና ሐዋርያ ያደርገዋል፤ አንተም ከምትሰራውና ከምታስተምረው በላይ የማስተማር ችሎታን ይሰጠዋል። እግዚአብሔር እኮ ቀይ ባህርን የከፈለው በከበረ የወርቅ ዘንግ ሳይሆን በተናቀ እንጨት ነበር።

እናም ጥንቁቅ ሁን ራስህን እንደ ትልቅ አትመልከት፣ በአለምም አትመካ፣ በመንፈሳዊ ህይወትህ፣ መንፈሳዊ የሆኑ መጻሕፍትን በማገላበጥህ ወይም ባለፈው የህይወት ተሞክሮህ አትመጻደቅ። ምንም እንኳን በዕድሜ የገፋህ በዕውቀት የበሰልክ ብትሆንም እንደ ትንሽና ጀማሪ የሆንክና እሱ እንዲመራህ ከመጥፎ ነገር እንዲጠብቅህ አካሄድህን ከእርሱ ጋር አድርግ።

ይህ ያንተ አሳብ ይሁን፤ ብዙ ያነበቡ፣ ስለመንፈሳዊ ነገሮች ብዙ የጻፉ ሰዎችን አይቻለሁ ነገር ግን በጥቃቅን ኃጢያት ይወድቃሉ። መጽሐፍ ቅዱስም በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹንም ክንድ የሚያደርግ ሰው ርጉም ይሁን ኤር 17፤5። እንዳለ አንተም በመንፋሳዊ ዕውቀትህ ና ህይወትህ እንዳትመካ በአጽንኦት እልሃለሁ።

ውድ ወንድሜ ማንኛውም መንፈሳዊ ሆነ ዓለማዊ ዕውቀት ወደ ትህትና አይመራም፤ የአላዋቂነት ስሜትም



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



እንዲሰማህ አያደርግህም ነገር ግን አታላይ ዕውቀት እንደሆነ እወቅ ይህም አንተን ከፍ ብለህ እንዳትጠየቅ ዝቅም ብለህ እንዳትጠይቅ እንዲሁ መንፈሳዊ ህይወትህን በአግባቡ እንዳትመራ ከሰይጣን በኩል የሚወረወርብህ ፈለጻ ነው:: ውድ ወንድሜ መጽሐፍ ከእናንተ ማንም በዚህች ዓለም ጥበበኛ የሆነ ቢመስለው ጥበበኛ ይሆን ዘንድ ሞኝ ይሁን 1ኛ ቆሮ 3፤18:: እንዳለው አንተም ጥበበኛ ትሆን ዘንድ አላዋቂ ሁን::

በእግዚአብሔር ፊት ጠቢብም አላዋቂም እኩል ነው:: ምክንያቱም ጥበበኛው በጥበቡ አላዋቂውም በድንቁርናው ከሞት የማያመልጥ ነው:: በእግዚአብሔር ፊት ኃያሉና ደካማው እኩል ነው:: በፊቱ ማንም ኃያል የለምና::

<u>ውድ ወንደሜ ኃያል እንደሆንክ ታስባለህ?</u>

ለመሆኑ ይህን ኃይል ከየት አገኘሽው? በትክክል የአንተ አይደለም:: አንተ አፈርና ትቢያ ነህና ባዶ ነህ:: ይህን ኃይል ከእግዚአብሔር በስተቀር ከሌላ ማግኘት አትችልም:: ምክንያቱም ስሙ የተመሰገነ ይሁንና እሱ ብቻ ኃያል ስለሆነ ሁሉን ቻይ ነው፤ ዕውቀት የባህርዩ ስለሆነ ሁሉን አዋቂ ነው:: ታዲያ የአንተ ኃይል ከእግዚአብሔር ነውን? ከእግዚአብሔር ከሆነ ለምን በራስህ ትመካለህ:: ለምንስ ኃይሉን ከእግዚአብሔር እንዳላገኘሽው ታስባለህ? ዕውቀት የሰጠህንና ኃያል ያደረገህ እግዚአብሔርን ልታመሰግነው ይገባሃል:: እሱም የጥበብ ሁሉ መገኛና የዕውቀት ሁሉ ምንጭ ነው::





ነገር ግን በተፈጥሮ ደካማ ብትሆንም በእግዚአብሔር ኃያል ከሆንክ ከቅ.ጳውሎስ ጋር በህብረት የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ:: ስለዚህ ስለክርስቶስ በድካም በመንገላታትም በችግርም በስደትም በቅንነትም ደስ ይለኛል ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና 2ኛ ቆሮ12፤9-10 ልትል ይገባሃል::

ራሱን ኃያል እንደሆነ የሚያስብ ሰው ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ እድል ፈንታ የለውም:: ምክንያቱም እግዚአብሔር የአለምን ትልቅ ነገር ለማዋረድና ለመጣል የአለምን ደካማ ነገር መርጧልና:: እና በራስህ መመካትህ ኃጢያት ስለሆነ ባለህ እውቀትና ኃይል አትመካ:: ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸውና እርሷም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው:: ቤትዋ የሲኦል መንገድ ነው ወደ ሞት ማጅት የሚወርድ ነው:: ምሳ. 7፤26-27 ደካማነትህን እኔ ስለነገርኩህ ሳይሆን ግልፅ የሆነ እውነታ ስለሆነ እርግጠኛ ሁን:: ዛሬ በኃጢያት አልወደክም? ትላትናስ? ከትላንት በስቲያስ? ስለዚህ ጠንካራ አይደለህም፤ የድክመትህም ማስረጃ ነው:: ድክመትህን እስካላመንክ ድረስ በኃጢያት ትኖራለህ፤ ከእግዚአብሔርም ጋር ህብረት አይኖርህም::

ሌላ ምክር ልለግስህ:- ራስህን ከሌሎች ኃያል አድርገህ በማንኛውም ሥራና ሁኔታ ፊተኛ አትሁን:: ይህ የበላይ የመሆን ጥማትህ ምናባዊ ቅዠት ነው:: አንተ ከሰው ሁሉ በላይ እየበደልክ ሰዎችን በትንሽ ኃጢአት ትወነጅላለህ:: ከእነሱም የበለጠ ደካማነት ይታይብሃል:: ለብዙ ዘመናት ነገሮችን ሁሉ በማሸነፍ ከነበርክ የእግዚአብሔር እጅ ከአንተ ጋር ስላለች እንጂ በአንተ ኃይል



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



አይደለም። አካሄድህን ከእርሱ ጋር አድርግ። እግዚአብሔርና አንተ በአንድ ቦታ ሆናችሁ ልትመለከ አትችሉም።

እንዳችሁ ብቻ ትሠራላችሁ። እግዚአብሔር ወይም አንተ፤ ሁሉን ነገር እግዚአብሔር እንደሚሰራ ካሰብክ፣ በፊቱ ባዶነት ከተሰማህና ሥራዎቹን በመደነቅ ለማየት ከቆምክ እጅግ ግሩም ነው። ማንኛውንም ነገር የምታከናውንና ሁሉን ለማድረግ ኃይሉ ያለህ መስሎ ከታየህ ከንቱ እንደሚሆንብህና መጥፊያህ ሊሆን እንደሚችል እርግጠኛ ሁን።

ይህም አገልግሎትህንና ውጫዊ እንቅስቃሴህን የሚመለከት አይደለም። ነገር ግን የውስጥ መንፈሳዊ ህይወትህንም ጭምር እንጂ። በድጋሚ የዘላለም ህይወትን በራስህ ጥረት እንደምታገኝ ካሳብክ ለተመሳሳይ ኃጢአት ትጋለጣለህ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሞትን ያስከትልብሃል።

መሠረታዊው ነገር ደካማ መሆንህን ማወቅ ነው። በምድር ላይ እንደሚበቅሉ አሜኬላና እሾህ ነህ። በማንኛውም ፈተናና ኃጢአት ፊት እጅግ ደካማ ነህ። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ፣ ቁጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ ቢዚያን ጊዜ ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር ። መዝ 124፤ 2-4 በማለት ከዳዊት ጋር ጸልይ። ከዚያም ወደ ጌታ ጩህ እንዴት ታግሎ እንደሚያሸንፍልህም ተመልከት፤ ድል የእርሱ የሆነ ከአንተ ይልቅ ድል የእርሱ ለሆነ ካስብሐት ለእግዚአብሔር ይሁን በል።

በመጨራሻም ራሳችንን አስመልክቶ ብዙ ሊባል እንደሚችል አስባለሁ፤ ውድ ወንድሜ በድጋሚ ተገናኝተን እስከንነጋገር ድረስ በጸሎትህ አስበኝ እስካሁን ያቆየን የጌታ ፈቃድ ከሆነ ጥናታችንን እንቀጥላለን።





# ውዳሴ ከንቱ

ባለፈው ርዕሳችን ራስን ስለመካድ ተነጋግረን ነበር። ነገር ግን ይህን ርዕስ አስመልክቶ ብዙ የሚባል ስላለ ከዚህኛው ጋር በጋራ እንመለከተዋለን።

ውድ ወንድሜ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ትፈልጋለህ? ከቅ.ጳውሎስ ጋር ልሂድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነው ፊል 1፤23 ማለትን ትወዳለህ። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ይልቅ ከምታመልከው፤ ምንግዜም ከሌሎች ይልቅ ውዳሴ ከንቱንና ክብረ ከንቱ ከሚፈልገው ከአንተነትህ የራቅህ ሁን።

ውድ ወንድሜ አለም አንተን ታከብርሃለች? ይህንስ ትቀበላታለህ? እንዴት ጨቋኝ ነህ! ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔር ብቻ እንዲገባ አታውቅምን? የፍጥረት ሁሉ አስገኚና ፈጣሪ ነው ሁሉን ቻይ ዘላለማዊ ምሉዕ በኩለሄ፣ ሁሉን አዋቂና ፈጣሪ እርሱ ብቻ። ነው ራስህን ስታከብርና ስታመሰግን፣ ሌሎችም እንዲያውቁልህ በምትፈልግበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ክብር ቀምተህ ለራስህ ማድረግህ ይገባሃልን? አባትህ አዳምም የወደቀበት ፈተና ይህ ነበር። አዳም የተሰጠው ጸጋ አርኪ መስሎ ስላልታየው ከፍ ይል ዘንድና እግዚአብሔርን መሆንን ፈለገ።

ውድ ወንድሜ የእግዚአበሔርንስ ክብር የምትጋፋ አንተ ማነህ? አፈርና አመድ ምንዓይነት ክብር አላቸው? ወይስ ምንም



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



አለመሆን ምን ዓይነት ክብር አለው አንተ እንደ እኔ ኃጢአተኛ አይደለህምን? ነገር ግን በሁሉ ነገር እርሱ ይጠብቅሃል ኃጢአትህን ከሰው ፊት ይሰውርልሃል። ኃጢያተኛ ሳለህ የሚያጸድቅህ፣ ደካማ ሳለህ ኃያል የሚያደርግህ ታገኛለህን? ተፈጥሮህ፣ ኃጢያትህንና ደካማነትህን እያወክ ታዲያ ለምን ራስህን ታመጻድቃለህ?

ሰዎች የሚያመሰግኑህ ከአፈር መፈጠርህንና ማንነትህን ባለመረዳታቸው ነው? የሚያመሰግኑህ ማንነትህን ስላላወቁ አይደለምን? ታዲያ ይህን ካወቅህ ለምን ታታልላቸዋለህ? አንዳች ነገር ላታገኝ ለምን ራስህ'ን ታታልላለህ? የእግዚአበሔርን ጥበቃና የኃጢያትህን ስርየት በራስህ እንዳመጣሽው ታስባለህ?

**እግዚአብሔር ኃጢያትህን፣ ሀሳብህን፣ ጭንቀትህንና ምኞትህን በህዝብ ፊት ገልጾ እንዳያዋርድህ ትፈልጋለህ?**

በሞትህ ጊዜ የማይከተልህንና በጽድቅ ፍርድ ቀንም ጠበቃ የማይሆንልህን ከንቱ ውዳሴ ለምን ትሻለህ? ምክንያቱም በፍርድ ቀን ፈራጁ የተሰወረና የተደበቀ ለፊቱ ግልጽ የሆነው እሱ ይህን እንድታደርግ አይፈልግም። ዋጋህንም እንደ ሥራህ ይከፍልሃል፣ እንጂ በሰዎች ምስክርነት ምንም ልታገኝ አትችልም።

አሁንም የሰዎች ምስጋና በአንተ ዘንድ ቦታ አለው? ስህተት እንደሆነ ዕወቅ። ምስጋናቸው ከይሉኝታ አልያም ከአንተ ዘንድ ጥቅም ፈልገው ሊሆን ይችላል። ምንም እንኳን ሰዎች እዉነተኛና ታማኝ የሚሆኑበት አጋጣሚ ቢኖርም ፊትህን





አይተው ይፈርዳሉ። ማንም የልብህን ሊመረምርና ሊያውቅ አይችልም

ወዳጄ ሆይ በብዙ ነገር እንደረበሸኩህ ይሰማኛል። አንድ ታሪክ ልንገርህ የናቡከደነጾር ታሪክ ነው። ዳን 4÷29-33 ምን ያህል ከንቱ ውዳሴ እንደሚፈልግ ታውቃለህ? ከእርሱ የህይወት ታሪክ ትምህርት እንደምታገኝ እርግጠኛ ነህ።

ኦ! አስቆጣሁህ መሰለኝ? ስለ ጸያፍ ቃላቴና ስለድክመቴ ይቅርልትለኝ ይገባል። ግን ሰዎች ሲያነጋግሩህ ስላላሞካሹህና ስላላወደሱህ የመቆጣት ልምድ አለህ? ምናልባት አም ልትለኝ ትችላለህ ግን ለምን? ወዳጄ ሆይ አሁን የምነግርህን የንግግር ዘይቤ ብትቀበለው መልካም ነው ምክንያቱም የአንተን ማንነት ይገልጽልሃል። ለድሕነትህ አጅግ አሰፈላጊ ስለሆነ ይህን ለማወቅ ትልቅ ፍላጎት ይኑርህ።

አንድ ታሪክ ላውጋህ፡- በአንድ ወቅት አንድ ታዋቂ ሰው መልኩ እጅግ አስቀያሚ ነበር። ሰዎች ግን ሥልጣኑን ስለሚፈሩ መልከመልካም እንደሆነ ይነግሩት ነበር። በአንድ ወቅት ግን በአንድ አካባቢ ሰዎች ተሰብስበው ስለነበር በዚያ መሐከል አንዲት ህፃን ታየውና እጅግ በመገረም "እንዴት ያስጠላል" ትለዋለች በዚህ ጊዜ ይህ ሰው ብስጭት ሳይገጥመው ትክክለኛ ማንነቱን ስለነገረችው እጅግ ወደዳት ከህብቱም አካፈላት።

ለምን በሌሎች ፊት ትልቅ ሆኖ መታየትን ትፈልጋለህ? ባመሰገኑህ ጊዜ ደስተኛ ትሆናለህ፣ በተቃወሙህ ጊዜ እንከን እንደሌለበት በፊታቸው ለመቆም ራስህን ንጹሕ ታደርጋለህ እነዚህ ሰዎች ቢያመሰግኑህም ባያመሰግኑህም ደስተኛ አትሆንም ነገር ግን



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



መልካምነትህን በማውራት እንዲያመሰግኑህ ትለምናቸዋለህ ስለዚህም ሊያመሰግኑህና ሊያደንቁህ ይችላሉ።

ይህ እውነት አይደለም? ከሆነ ስለ ነገሩ በጥልቀትና በጋራ እንመልከት።

ውድ ወንድሜ ፍጹም እንዳልሆንክ፣ ደካማና ኃጢአተኛ ከሰው ሁሉ የበታች እንደሆንክ ብታስብ ለአንተ መልካም ነው። የዚህ መፍትሔ ግን ባለፉት ችግሮች ላይ አዳዲስ ተግባሮችን መጨመር ሳይሆን የከበቡህን ችግሮች ማስወገድና ራስህን ማጽዳት ነው።

ለምን ሰዎች ስለአንተ ስላላቸው ሀሳብ ለማወቅ ወይም ከእነሱ ምስጋና ለማግኘት ለምን ታስባለህ? ሰዎች ስለ አንተ መልካምነት ካልመሰከሩልህ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አትገባምን? መጽሐፍ ቅዱስ "ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ ወዮላችሁ ለሐሰተኞች ነቢያት እንደዚሁ ያደርጉላቸው ነበር። ሉቃ 6÷26 ስለሚለን ብዙ ጊዜ ከሰዎች ውዳሴ ከንቱን የሚሹ ሰዎች በእሳት ባህር ውስጥ ከመጣል አይድኑም"።

ውድ ወንድሜ ሰዎች ብርቱ ስላልሆኑ ያልፋሉ፣ምስጋናቸውም ጊዜያዊ ነው ህዝብ ማለት ልክ እንደ ጌታ በዕለተ ሆሳዕና ይንገሥ፣ ይንገሥ ብለው እንዳልነበር ኋላ ስቀለው፣ ስቀለው የሚሉናቸውና የሰዎች ምስጋና አጠራጣሪ ነው።

ከአንተ መልስ የምፈልግለት ጥያቄ አለኝ። የተደበቁና አሳፋሪ ሥራህን እያወቅህ ሰዎች ሳያውቁህ በሚያመሰግኑህ ጊዜ





ምን ይሰማሀል? እያመሰገኑህ ሳለ ኃጢአትህን ቢያውቁ ኖሮ በምስጋና ፈንታ ዘለፋን በሰጡህ ነበር። ይህን ትረሳለህ? ሰዎች በፈጠሩልህ ውዳሴ ከንቱ በምታገኘው ሐሴት እነዚህ ኃጢአቶችህን እንደሚረብሹህ ትገምታለህ? ስለውጫዊው ማንነትህ ብቻ ትጨነቃለህ ልክ ላዩ አምሮ ውስጡ እንደሚከረፋ መቃብር ስለ ምድራዊ ህይወትህ ብቻ እንጂ ሌላ ስለሚመጣ አዲስ ህይወት አትጨነቅም።

ትክክለኛ ስሜትህን ለራስህ ስትገልጽ በግልጽ ይሁን። በመጀመሪያ ለራስህ ተናዘዝ፣ ከዚያም ራስህን ወደ ንስሐ አባትህ አቅርብ።

አሁን ከዚህ በታች ሰዎች በሚያመሰግኑህ ጊዜ ምን እንደሚሰማህ አንድ በአንድ ተመልከት።

1. በመጀመሪያ ግብዝ እንደሆንክና ውጫዊው ማንነትህ ከውስጣዊ ማንነትህ እንደሚለይ አሰብ ለራስህም በግልጽ "እኔ ሐጢአተኛና በደለኛ ነኝ" በል በንስሐ አባቴ ፊት ስቀርብና ኃጢአቴን ስቆጥር ወራዳ፣ ትንሽና ከፀጋህ ረድኤት እንደራቁ ይሰማኛል ለጸሎት በምነሣ ጉዜ ዓይኖቼን ወደ ሰማይ ለማንጋጠጥ እሰቀቃለሁ። ታዲያ ሰዎች ለምን ያመሰግኑኛል ምናልባትም እኔ ግብዝ ነኝ በሰዎች ፊት ሁለት ስብእና ያለኝ።
2. ሰው በሚያመሰግንህ ጊዜ ምድራዊ ዋጋህን እያገኘህ ሰማያዊውን ዋጋህን እያጣህ መሆኑን አስብ። ከዚያም በማይረባ ነገር የጽድቅ አክሊልህን ታጣለህ። ሰዎች ባመሰገኑህ ጊዜ ስለምታጣው የጽድቅ አክሊል ሀዘን



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ሲሰማህ ይገባል። ይህም ሀዘንህ የሚያነጻህና መንፈስህን ነጻ የሚያደርግ ይሆናል።

3. ሰዎች በሚያመሰግኑህ ጊዜ እያጭበረበሩህ እንደሆነ ዕወቅ የእግዚአብሔር ክብርንም በመቀማት ለራስህ እያደረግ መሆንክን ተረዳ ክርስቶስ "መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለው አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።" ማቴ 5፥16 እንዳለ፣ ስለዚህ ክብር ለእግዚአብሔር ከመገባቱ ይልቅ ለአንተ ካደረከው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እግዚአብሔርን ሰርቀሃል። ስለዚህ በጸሎትህ ጊዜ "መንግሥቱም፣ ክብሩም ኃይሉም የአንተ ነው።" እያልክ ጸልይ። የእግዚአብሔርን ኃይል በመቀናቀን እንድትከብር መፈለግህን ከአንተ አስወግድ። "ለእኛ አይደለም፣ አቤቱ ለእኛ አይደለም ነገር ግን ለስምህ፣ ስለምህረትህ ስለ እውነትህም ምስጋና ስጥ" መዝ 115፥1

4. ሰዎች በሚያመሰግኑህ ጊዜ ማንነትህን ተረዳ የሀሳባቸውንም አቅጣጫ ወደ እግዚአብሔር አድርግ። ያለግብዝነት በትህትና ኃጢያተኛና ደካማ እንደሆንክ ንገራቸው። በምንም ነገር ምስጋና የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ይህን ቃል አንተም ተጠቀምበት ከዚያም በኩራት መታበይን ታቆማለህ።

5. ስለ አንተ ክብር የሚያወሳ ታሪክ ከሰማህ ርዕሱን ለመቀየር ምክር፣ ቢያንስ በነገሩ ደስተኛ አትሁን፣ ነገር ግን በደስታ ክብርን ለእግዚአብሔር አቅርብ።





6. እነዚህን ጥቅሶች በቃልህ አጥንተህ ዘወተር ድገማቸው። "ከሰው ክብርን አልቀበልም፣ አሁን አባት ሆይ አለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ" ዮሐ 5፥41=17፥5

7. ሰዎች በሚያመሰግኑህ ጊዜ ኃጢያትህን አስታውስ፣ ህሊናህም ይውቀስህ ስለዚህ በዚያ በአንተና በሰዎች ምስጋና መካከል መመዘኛ ሊሆን ይችላል በመጨረሻም ሰዎች በሚያመሰግኑህ ጊዜ መልስህ ይህ ከሆነ ምስጋናን ከሰዎች የማትሻው ለዚህ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



# ነቀፌታ

ውድ ወንድሜ በእግዚአብሔር ቦታ ከምታመልከው በሰዎች ፊት ከፍ ከፍ ከምታደርገውና ከምታወድሰው ከአንተነትህ ካልራቅህ በስተቀር ለዚህ ነገር መራቅ አትችልም::?

ምናልባት ብዙ ጊዜ በሰዎች እንድትመሰገን ትወድ ይሆናል፤ በዚህ ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብህ ባለፈው ርዕስ ተመልክተናል::

አሁን ደግሞ ሰዎች በሚያስቆጡህና በሚያስቀይሙህ ጊዜ ምን ይሰማሃል አድራጎትህስ ምንድን ነው::

ምናልባት የተዋረድክና የተሰደብክ መስሎ ሊሰማህ ይችላላ፤ ለክብርህ ሟች ለስልጣንህ ተሟጋች ልትሆን ትችላለህ:: ይህ ደግሞ ተናዳጅና ብስጩ እንድትሆን ያደርግሃል:: ነገር ግን ና! ነገሩን በህብረት እንመልከት

ምን ለመጠቀም ትቆጣለህ? ይህም አጅግ ይረብሽሃል ወይም ህዋሳዊ መታወክ ያስከትልብሃል:: ከሰላማዊ ህይወት ያርቅሃል:: የሐዋሪያውን ቃል አስታውስ::

"የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ፅድቅ አይሰራም" ያዕ 1-20

በራስህ ጉዳይ ላይ መበሳጨትህ ያዕቆብ ያለው ቁጣ እንደሆነ ጥርጥር የለውም:: ሀዘንህን ለማቃለል፣ ከተረበሸክበት ነገር መንፈስህን ነጻ ለማድረግ ይህን ቁጣህን ስትቆጣ እስማሃለሁ:: እንዲለቅህ የሚፈለገው ይህ የመንፈስ መረበሽ ለምን ይኖርሃል በእርግጥ ምክንያቱ ግልጽ ነው በጣም ራስ ወደድ ስለሆንክ ነው:: ውድ ወንድሜ ከዚህ ነገር ራቅ መንፈስህም ደስተኛ ትሆናለች::

ማንም ቢሰድብህ ራሱን እንደሰደበ እንጂ አንተ እንደተሰደብክ አታስብ:: ይህ ሰው ወንድምህ ነው:: አንተ በፍቅር የተሞላህ መንፈሳዊ ነህ ለዚህ በአንተ ምክንያት ኃጢያት ለሰራው ሰው ምን ታደርግ ይሆን?

በእርግጥ ቅድስት የሆነች ነፍሱ ሲኦል ትወርድ ዘንድ ፈቃድህ አይደለም ስለዚህ እግዚአብሔር በዚህ ምክንያት እንዳይቀጣው ብትጸልይለት መልካም ነው:: ዳግም በአንተና በሰዎች ላይ ይህን ኃጢያት እንዳያደርግ እግዚአብሔርም ልቡና ይሰጠው ዘንድ ጸልይለት::





ስለሰደበህ ወንድምህ በምታስብለት ጊዜ የስድቡ መንስኤ ምን እንደሆነ ለማወቅ ሞክር:: ምናልባት ታሞና ታውኮ ተበሳጭቶ በስራ ደክሞ ወይም የገንዘብ እጥረት አጋጥሞት ሊሆን ይችላል:: ምን እንደምታደርግለትም መርምር ምናልባት ጥሩ ሽርሽርና ደስታን የሚፈጥሩለት ነገሮች ልታዘጋጅለት ይገባሃል ምንም ልታደርግለት ካልቻልክ ግን በመጨረሻም ከፍ ያለ ርህራሄ አሳየው:: እግዚአብሔርም በረድኤት እንዲጠብቀው ጸልይለት::

ውድ ወንድሜ ሰዎች በተፈጥሯቸው ደካሞች አይደሉም ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረው በኋላ የእጆቹን ስራ ሲያደንቅ "እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበር" ዘፍ 1-31 ብሏልና ክፋት ከሰዎች ባህሪ የመጣ ሳይሆን ከባህሪያቸው ውጪ የሚለማመዱት ነው::

ይህ ሰው እንዲሰድብህ ያስገደደው ሌላ ምክንያት ሊኖረው ይችላል:: አንተን ካለመረዳት ሊሆን ይችላል:: በዚህ ጊዜ በፍቅርና በትህትና በመወያየት ልታነጋግረው ትችላለህ::

ይሁንና አንዳዶቹ መሳደብ ስለፈለጉ ብቻ፤ የሰዎችንም ትዕግስት በመመልከት፣ አቃቂር በማውጣት፣ በመተቸት ዋዛና ፌዝ መፍጠሪያ ያደርጓቸዋል::

በክርክርና በጥብቅ ከእነዚህ ሰዎች ጋር በመነጋገር ልትመልስላቸው ስለማትችል ከንግግርህ ተቆጠብ:: ነገር ግን በዚህ ስህተታቸው እንዳይወድቁ የትህትና ባህርይህንና መንገድህን አሳያቸው::

ይህን የምታደርገው ክብርህን ለማንጸባረቅና መብትህን ለማስከበር ሳይሆን ትህትናን በማስተማርና ፍቅርን በመግለጽ ከስህተታቸው እንዲታረሙ ይሁን:: በድጋሚ በተመሳሳይ ኃጢአትና ስህተት እንዳይወድቁ ትምህርት ይሆናቸዋል::

በቁጣ በመገሰፅና በፍቅር በመምከር መሀከል ትልቅ ልዩነት አለ:: ምክንያቱም ሰውን በቁጣ በገሰጽከው ጊዜ ጠላትህ ታደርገዋለህ፤ በፍቅር ስትመክረው ግን ወዳጅህ ታደርገዋለህ::

ይህ ርዕስ ለነቀፌህ ሰው ያለህን ዝንባሌና ውስጣዊ ስሜትህን የምትመለከትበት ነው:: ስለዚህም አሁን በስፋትና በጥልቀት ስለውስጣዊ ስሜትህና ስለሚኖርህ ዝንባሌ እንመልከት::

1. ለምን የሰዎችን የነቀፌታ ቃል በብዙ ዓይነት ትመነዝረዋለህ? ለምን ትምህርት እንደሚሰጥህና እንደሚጠቅምህ አትቆጥረውም በዚህ ምክንያት



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ከተበሳጨህ በሰዎች እንድትመሰገን ሰዎች ስለአንተ መልካም እንዲያወሩ የምትሻ ነህ:: ሰዎች ሲተቹህና ሲሳለቁብህ ደስ ይበልህ:: ምክንያቱም ይህ ለአንተ መልካም ነው:: ይህ አንተን የሚያነጻህና በሚመጣውም ህይወት የሚጠቅምህ ነው::

ሰው በሚነቅፍህ ጊዜ ያ ድምጽ የእግዚአብሔር ድምጽ ሊሆን ስለሚችል አመስግነው::

የሚወድህ እግዚአብሔር አንተን እንዲመክሩህ፣ ከምትፈጽማቸው ስህተቶች እንድትታረም፣ ስህተትህን እንዲገልጽብህ እንደዚህ ዓይነት ሰዎችን ሊልክብህ ይችላል::

2. ምናልባት እግዚአብሔር ቀድሞ ስለፈጸምካቸው ኃጢያቶች በእነዚህ ነቀፌታዎች እያዋረዱህ ይሆናል:: ንጉሥ ዳዊት ከሳሚ የእርግማንን ቃል በሰማ ጊዜ ካእግዚአብሔር:- ዳዊትን ስደበው ብሎ አዝዞታልና ስደበኝ 2ኛ ሳሙ 16፤10 አለ::
ወንድሜ ሰዎች በሚሰድቡህ ጊዜ ያለፈ ኃጢአትህን አስብ:: ፍጹም እንዳልሆንክም ዕወቅ::
3. ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር መልካም ሥራዎችን በአንተ አማካይነት ያከናውናል፤ ነገር ግን ይህን ሥራ በራስህ ጽድቅና ቅድስና እንዳገኘህ ትቆጥራለህ:: ስለዚህ እግዚአብሔር በመታበይ እንዳትወድቅ ስለሚፈልግ ሰዎች እንዲገስጹህ ያደርጋል:: ይህ ስብእናህን ሊያስተካክልልህ ይችላል፤ ትምክህትህንም በጥቂቱ ያስወግድልሃል ብዙ ሰዎች በሌሎች በሚነቅፉ ጊዜ ኩራት ይሰማቸዋል:: መጽሐፍ ቅዱስም እግዚአብሔር የዋሖንን ከዝቃጭነት አንስቶ ከህዝባቸው መሪዎች ጋር ያስቀምጣቸዋል መዝ 113፤8:: ይላል
4. ምናልባት ከሰዎች ጋር ባለህ ማህበራዊ ግንኙነት ባለማወቅ በጸባይህ አበሳጭተኃቸው ይሆናል፤ እነሱም ይሰድቡሃል:: ስለዚህ ይህ ያበሳጨህ ሰው ትክክል ሊሆን ስለሚችል በምን ምክንያት እንደሰደበህ መርምር::
5. ይህ ስድብ አንተን ፍቅርን፤ መከራንና መታገስን ማስተማሪያ ሊሆን ይችላል? አንድ [illegible]
በብቸኝነት [illegible]
ለመነኩሳት ከወንደሞች ጋር መሰባሰብ እጅግ አስፈላጊ





ነው፤ ምክንያቱም በወንድሞች መካከል የሚፈጠረውን ጥል ካልተቋቋሙ በብቸኝነት ህይወት ውስጥ እንዴት ሰይጣንን ሊቋቋሙ ይችላል::

6. ሰዎች በስህተት ቢወነጅሉህና እንደ ስህተተኛ ቢመለከቱህ ምን ጉዳት ይደርስብሃል? ይህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ከማግኘት ያስተጓጉልብሃል? ወይስ እንደሰዎች እግዚአብሔርም ይፈርድብሃል?
7. ወይስ እንደ አንተ ከአፈር ከተፈጠሩ ሰዎች ውዳሴ ከንቱንና ተወዳጅነት ማግኘትን ትሻለህ? ወንድሜ ጌታህን አስታውስ "ተጨነቀ ተሰቃየም አፉን አልከፈተም ከአመጸኞች ጋር ተቆጠረ" ኢሳ 53፤7-12 እጅግ መልካምና ንጹህም ሆኖ ያን መከራ ተቀበለ::
8. በመጨረሻም ውድ ወንድሜ ኃጢአተኛ ሆነህ ሳለ በምትነቀፍበት ጊዜ ለምን ትበሳጫለህ? ንጹሐ ባህርይ የሆነው እግዚአብሔር እንኳን ስንነቅፈው እንዴት እንደሚታገሰን፣ ስንጠላው እንዴት እንደሚወደን፣ ስንርቀው እንዴት እንደሚቀርበን እስኪ ተመልከት::



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



# እኔነትን ከውስጥህ አስወግድ

ሰዎች እንዴት እንደሚኮንኑህ ስትረዳ ጥፋትህን ባለማመን ይህ መጥፎ ሀሳባቸውን በመቀየር በእነርሱ እንድትመሰገን ብቻ ደፋ ቀና የምትል ከሆነ ነፍስህ ቅድስናን ለማግኘት ትቸገራለች።

ብዙ ጊዜ ሰዎች ከአንተ ይልቅ ሌሎችን በይበልጥ ያወድሳሉ። የውዳሴ ከንቱ መንፈስ ስለተጸናወተህ ከመደሰት ይልቅ ስትታወክ ትስተዋላለህ።

ውድ ወንድሜ ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው ይህንንም በግልፅና በጥልቀት እንይ፡-

1. ለምን ስለመልካምነት ለሌሎች ታወራለህ እንዲያደንቁህ ትፈልጋለህ? እስኪ በግልፅ ንገረኝ፤ በውስጥህ ራስህን ታደንቃለህን? በእርግጥ በውስጥህ የምትጨነቅባቸውና ብዙ ግራ የምትጋባባቸው እንከኖች እንዳሉ ጥርጥር የለውም። ታዲያ እንዲህ ሆነህ ሳለህ ራስህም ባላመንክበት ባህሪ ሰዎች እንዲያወድሱህና እንዲያሞካሹህ ለምን ትወዳለህ?
2. አንድ ሰው ሲናገር ሊከተል የሚገባው ትክክለኛው መስፈርት ምን መሆን እንዳለበት እስኪ ልጠይቅህ፡- ስለ ራስህ ትክክለኛ መግለጫ ልታቀርብ ትችላለህ? ወይስ ሰዎች እንዲጠሉህ የሚያደርጉህን፣ አሳፋሪና መጥፎ ነገሮችን በመተው ስለ ጥሩ ጎንህ ብቻ ትገልጻለህ? ወንድሜ ውሸት የታከለበት እውነት እውነት ሊኖረው አይችልም። ስለ ራስህ ስትናገር ውሸት ትጨምራለህ? አንተና የንስሐ አባትህ ብቻ በምስጢር የምታውቁትን እንከኖች ለሰው ትናገራለህ?
3. ስለ መልካም ባህሪ ማውራት ስትጀምር ማግኘት ያለብህን የክብር አክሊል እንደምታጣ ጥርጥር የለው። በእርግጥ የተራራውን ስብከት አንብበሃል፤ ጌታ ምን እንዳለም አይተሃል፤ "ቀኝህ የምትሰራውን ግራህ አትወቅ።" በስውር የሚያይ አባትህ በግልጽ ያስረክብሃል ማቴ 6፤3-4። በአንተ ሐዘን ይሰማኛል፤ ምክንያቱም የራስህን ከንቱ ጽድቅ ለምንታጸባርቅበት ስነምግባር ብቻ ትታገላለህ፤ ከዚህም ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሠይጣን ትቀርባለህ። እናም ጥርጥርህና ትጋትህ ከንቱ ሆኖ ይቀራል።





ስለ ራስህ ስትናገር በማይህ ጊዜ እንዲህ አድርጌ እመለከትሃለሁ፡- አንድ አትክልተኛ እግዚአብሔር ፍሬን በሰጠው ጊዜ በማምረቱና በምርቱ በመደሰት ፋንታ ያጎረሰህን ነካሽ ነህ።

ውድ ወንድሜ መቼም ስለራስህ መናገርን በምትፈልግበት ጊዜ እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል ማቴ 6 2 የሚለውን መለኮታዊ ቃል ተመልከት።

4. ሌላው ሥለራስህ በማውራት የሚመጡ መጥፎ ነገር በሚከተለው ታሪክ ውስጥ ግልጽ ነው። በአንድ አጋጣሚ ላይ አንድ እኔ ስለምወደውና ስለማከብረው ሰው በአድናቆት ስሜት አወራ ነበር። ነገር ግን አንድ መንፈሳዊ አባት ይህን ንግግሬን እንዳቆም ጠየቁኝ፤ ምክንያቱም በዚህ ምክንያት ርኩሳን መናፍስት እንዲዋጉት ትሰበስብበታለህ። ጀማሪ ስለሆነና ብዙ መጸለይ ስለሚጠበቅበት በእርጋታ እንዲኖር ተወው አለኝ። ከዚያም በኃላ በዚህ ሰው ላይ ስህተት እንዳደረኩ በማሰብ ውዳሴዬን አቆምኩ።

   ሰይጣን የአንድን ሰው መልካም ነገር ሰምቶ መታገስ አይችልም። ስለዚህ እግዚአብሔር በአንተ ውስጥ ታላቅ መልካም ነገር ካደረገ ይህም በአንተና በእግዚአብሔር መካከል በምስጢር ይሁን። ሰይጣን እንዳይዋጋህና እንዳይመቀኝህ አታውራው። በዚህ ምክንያት ዋጋህን ብቻ ማጣት አይደለም ለሌላ ውጤቱን ለማታውቀው መከራ ተገዢ ያደርግሃል።
5. ስለ ራሱ የሚያወራ ሰው የሚያጋጥሙት መጥፎ ውጤቶች እነሀ ናቸው። ነገር ግን በሌላ መልኩ ራስህን በማመስገንህ የምታገኘውን ጥቅም ልትነግረኝ ትችላለህ። በእርግጥ የኃጢያተኛ ሰው ስሜት ሰዎች በእርሱ ላይ ያላቸውን አድናቆት በተመለከቱ ጊዜ የሚሰማቸው ስሜት እውነተኛ አይደለም። ይህ ጥቅም ሳይሆን ሊተው የሚገባ ኃጢአት ነው። ነገር ግን እኔ በሚያስረዳህ መልኩ የምታገኘው ጥቅም ሊኖርህ ይችላል፤ ያም ስለ ራስህ የማውራቱ ፍላጎት አይሎ መቋቋም ካልቻልክ ስለደካማነትህና ስለጉድለትህ ለሌሎች አስታውቃቸው በኃጢአት በወደክ ጊዜም መፍትሄ ለማግኘት እንዲጸልዩልህና ወደ እግዚአብሔር እንዲያማልዱህ ለምናቸው።
6. ሌላ ልነግርህ የምፈልገው ነገር ሰዎች አንድ ሰው ስለራሱ በሚያወራ ጊዜ ያናንቁታል፤ ትዝህርተኛ ይሉታል። ይሁንና



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ይህ ሰው የምድርንም በረከት አይበላም የሰማያዊውንም ሀብት አይቀዳጅም።

7. በመጨረሻም ትክክለኛ ለመሆን የምታደርገው ጥረት ሁሉ ያንተ ጥረት ብቻ እንዳልሆነ እንድትረዳ እፈልጋለሁ። ይህኑ ነገር እንድታከናውን በአካባቢህ የሚረዱህ ሰው ሰራሽም ይሁን ተፈጥሯዊ ሁኔታዎች አሉ። ይኸውም በሌሎች ሰዎች ልትታገዝ ትችላለህ፤ እግዚአብሔርም ክሂሎቱንና ተስጥኦውን ይለግስሃል።
   እግዚአብሔር በአንተ ውስጥ ያደረገውን ዘንግተህ ሁሉን በራስህ እንዳደረክ ካሰብክ ለውድቀት ትዳረጋለህ።

ውድ ወንድሜ በግልጽነቴ ያስቀየምኩ ስለመሰለኝ እፈራለሁ፤ ይሁን እንጂ ይቅርታ የማይሸረው ነገር የለምና ይቅር በለኝ።





# ራስን መካድ

ውድ ወንድሜ ብዙ ጊዜ ከእግዚአብሔር በላይ ስለምትወደውና ስለምታምነው አንተነትህ ላወሳህ እወዳለሁ። ማንነትህን ካልተረዳህ በስተቀር ነፍስህ ቅድስናን ታጣለች አንተም የመንፈስ ነፃነት አይኖርህም።

ፍቅር በክርስትና ውስጥ የመጀመሪያው ትዕዛዝ እንደሆነ ሁሉ ራስን መካድ ደግሞ ወደ ፍቅር የሚያደርስ ዋነኛ መንገድ ነው። ስለግል ጥቅምህና ስለራስህ ደስታ ብቻ የምታስብ ከሆነ እግዚአብሔርና ሰዎች በአንተ እይታ ቦታ የላቸውም። ስለዚህ በመጀመሪያ ከዚህ ከራስ ወዳድነትህ ራቅ። ጌታ ስለቃሉ ምስጋና ለእርሱ ይሁንና "በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ" ማቴ 34- ብሏል

ስለዚህ ጌታም ራስን መካድ የመጀመሪያ መጠይቅ አደርጓል ውድ ወንድሜ ህይወትህ ከእግዚአብሔር የራቀ እንዳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋና ረድዔት የታገዘ ህይወት ይኑርህ። ከኃዋርያው ጋርም "እኔም አሁን ህያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ዬደራል" ገላ 2-20 በል

ክብር እንዲኖርህ ብትመኝ እንኳን ክብርህ ከእግዚአብሔርና በእርሱ ፊት ይሁን። "አባት ሆይ ከአንተ ጋር አክብረኝ" ዮሐ 175 የሚለውን ቃል ምንጊዜም ድገመው። በአለም ነገር ክብር አትፈልግ ምክንያቱም አለሙም ምኞቱም ያልፋሉ 1ኛ ዮሐ2-17 ግን አንተ የእግዚአብሔር ልጅ የሆንክ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሆንክ መንፈሱ የሚኖርብህ ነህ" 1ኛ ቆሮ 3፤16 እነርሱም ከእግዚአብሔር የተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከስጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም ዮሐ 1፤13 ይህች ነፍስህ "የእግዚአብሔር የአፉ እስትንፋስ ነች። በቅዳሴ ሁሉ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



በእርሱ ፈቃድ ከእርሱ ጋር ህብረት እንዲኖርህ በእርሱ እንድትታመን ከቅዱስ ስጋውና ከክቡር ደሙ ትቀበላለህ ክብርህ እንደዚህ ሆኖ ሳሳ ለምን ከአፈር ሌላ ክብርን በመፈለግ ይህን ክብር ችላ ትላለለህ?

ስለምን ሰዎች ሲዘልፉህ ትጨነቃለህ? ለምንስ በምስጋናቸው ጊዜ ደስተኛ ትሆናለህ? በሚያጠቁህስ ጊዜ ለምን ራስህን ትከላከላለህ? ውድ ወንድሜ አሁንም ስጋህንና የስጋህን ስሜት በማድመጥህ አዝናለሁ:: ውድ ወንድሜ ራስህን ካድ ፍቅርህም ለእግዚአብሔር ብቻ ይሁን:: ከሐዋሪያው ዮሐንስ ጋር "እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ይገባል" ዮሐ 3-30 በል:: ማን ከማን ያንሳል እያልክ ስትፎክር እሰማሃለሁ ንፅህናህን ለሚያሳጣህ ከዝቃጩ ነገር አንተን ከሚጎዳህ ከአለም ክብር በስተቀር ምንም የምታጣው ነገር እንደሌለ እወቅ:: እግዚአብሔር ሲፈጥርህ የነበረህን ክብር ለመመኘትና በእርሱ ፈቃድ ለመኖር ከእንደዚህ ዓይነቱ ኃላፊ ክብር ራስህን አግልል ሁል ጊዜ ከእርሱም ጋር እንድትሆን ይፈልጋል::

ያም አንተ ከሌሎች ጋር ያለህን ግንኙነት ይመለከታል:: ግን አንተን አስመልክቶና በእግዚአብሔር ፊት እንዴት እንደምትቆም መናገር እፈልጋለሁ:: መንፈስህ ከዚህ ነገር እንድትርቅ ከፈለክ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ባዶ ሆነህ ቅረብ ምንም ዓይነት ጥበብ ዕውቀት የስራ ልምድ ችሎታ እንዳለህ አትሁን:: በፊቱም ምንም እንደማያውቅ ሁን:: ይህን ስል አዋቂ ሆነህ ሳለ እውቀት ሁሉ የእግዚአብሔር እንጂ የባህሪ አለመሆኑን እንድትገነዘብ ነው::





ማለት የፈለኩት ነገር አንተ የሸሸከው ማንነትህን እንድታምን ለማድረግነው:: ይህን ኋላ ኢየሱስ ክርስቶስ ይገልጠዋል:: ይህ የተደበቀ ማንነትህ የሚገለጠው በሰዎች ፊት ብቻ ሳይሆን አንተም በም ትረዳው ዓይነት ነው:: "ጌታ ሆይ እኔ ፊትህን ለማየት እፈልጋለሁ የሰይጣንን ኃይል የማልችል ደካማ ነኝ የማገኛውም ስራ ውጤት በእጅህ ነው" በል እግዚአብሔርም እንዲመራህ፣ በህይወትህም ጣልቃ እንዲገባና በአንተ ላይ ስራውን እንዲሰራ ጠይቀው:: ከዚያም ሳትለምነው የምትሻውን አውቆ የሚሰጥህ አምላክህን አመስግነው:: እናም ሰዎች ሲያመሰግኑህ በመጡ ጊዜ አትኩራራ፣ አይምሰልህ ወይም በሀሰት ትሁት አትሁን አጋጣሚን ተጠቅመህ ዳዊት እንዳለው አንተም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን ሰዎች በእኛላይ በተነሱ ጊዜ ቁጣቸው በላያችን በነደደች ጊዜ በዚያን ጊዜ ህያዋን ሳለን በዋጡን ነበር በዚያን ጊዜ ውሃ ባሰጠሙን ነበር በነፍሳችን ላይ ፈሳሽ ባለፈ ነበር መዝ 124-1-4 እያልክ ዘምር::

ከኃጢአት ጋር በታገልክ ጊዜ ሥጋዊ ኃይልህን አትመነው ወይም ባለፈው አሸናፊነትህ አትመካ ምክንያቱም ኃጢያት "ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸውና እሷም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው" ምሳ7-26 ነገር ግን አሸናፊነት የጌታ እንደሆነ እርግጠኛ ሁን ለትንሽ ኃጢአት ላይ ከተወህ እንደሰዶም ህዝብ ትሆናለህ::

ይህን መዝሙር ዘምር "ነፍሴ በውስጤ ባለቀች ጊዜ መንገዱን አውቀው በምሄድበት በዚያች መንገድ ወጥመድን ሰወሩብኝ ወደ ቀኝ ተመለከትኩ አየሁ የሚያውቀኝ አጣሁ መሸሸጊያም የለኝም ስለነፍሴም የሚመራመር የለም:: አቤቱ ወደ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



አንተ ጨኸሁ አንተ ተስፋዬ ነህ በህያዋን ምድር አንተ እድል ፈንታዬ ነህ አልሁ። እጅግ ተቸግሬአለሁና ወደ ልመናዬ አድምጥ፤በርትተውብኛልና ከሚያሳድዱኝ አድነኝ መዝ 142-3-6።

ውድ ወንድሜ አንተ ምንም አይደለህም ይህን በአንተና በእግዚአብሔር ፊት ማመን አለብህ ማንኛውንም ነገርማድረግ እንደምትችል ስታስብ ወደ ልመናህ ተመለስና "ወደ ፈርኦን የምሄድ የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ ማነኝ" ዘ 3-11 በል።

ይሁንና እግዚአብሔር ይህን ካሳወቀህ በምትናገርበት ጊዜ እርሱ አፍህ ይሆናል በምላስህም ውስጥ ይናገራል አንተም ልክ እንደመሳሪያ ትሆናለህ ከዚያም በመንገድህ ስኬታማ ትሆናለህ እንደዚህ ከሆነ በሞት ጥላ ስር ብትገዝም ሰይጣንን አትፈራም ጠላትህም ሊወጋህ ሲነሳ በዚህ ትመካለህ።





# ከምድራዊ ምኞቶች ነፃ መውጣት

ከምድራዊ ምኞትህ ተላቀቅ ከምን ዓይነት ነገር መራቅ እንዳለብህ ታውቃለህ? ከምድራዊ ፍላጎትህ ከመሳሰሉት ራቅ ፍፁም የመንፈስ ነፃነት እንዲኖርህ ከፈለክ ከምድራዊ ምኞቶችህ ተላቀቅ።

ውድ ወንድሜ በእርጋታና በግልጽነት ላውጋህ እጅግ አብዝተህ የምትጨነቅባቸው ልብህን የተቆጣጠሩት ታላላቅ ምድራዊ ተስፋዎች አሉህ። እነኚህም ሀሳብህን ሁሉ ይቆጣጠሩታል ብቻህን በምትሆንበት ጊዜ በምናብ ይመጡብሃል በምትተኛ ጊዜ ህልምህ ሁሉ ይህ ይሆናል ልትከዳቸው የማትችለው ነገር ግን የምታውቃቸው ምድራዊ ዓላማዎች አሉህ። ተፈላጊነት እንዲኖርህ ትመኛለህ ስልጣን እንዲኖርና ኃያል እንድትሆን ዕውቅና እንዲኖርህና ስምህ ከጽንፍ እስከ አጽናፍ እንዲናኝ ትፈልጋለህ። በሀብት፣ በማህበራዊ ስልጣን በእውቀት በማዕረግና በመልክ ዝነኝ የመሆን ተሳፋ አለህ፤ በመኖሪያ ቤት፣ በምግብ በልብስና በሰውነት ደስታን በሚሰጡ ነገሮችም ተስፋ አለህ። አለም በአንተ እንጂ አንተ በአለም እየኖርክ አይደለም። ስለዚህ አንተነትህ በዚህ ምድራዊ ተስፋ የታጠረ ነው። መንፈስህም ከስጋ ፍላጎቶች መራቅን ትመኛለች ስጋ በመንፈስ ላይ መንፈስ በስጋ ላይ ይመኛልና" ገላ5-17



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ውድ ወንድሜ እነዚህ ሥጋዊ ተስፋዎችና ፍላጎቶች ስኬታማ ስለማይሆኑ ግራ ትጋባለህ፡፡

ይህም በእርግጥ ቅሬታን ያመጣብሃል፡፡ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ትናፍቃለህ ነገር ግን ናፍቆትህ አያስደስትህም፡፡ ስለዚህ ለምኞትህ ሁሉ ማስተካከያ ታበጅለት ይሆናል ምናልባትም ይጠቅሙኛል የምትላቸውን ሰዎች ማግኘት፣ በምኞትህ ዙሪያ የተሟፈ መዛግብት ማገላበጥ ትፈልግ ይሆናል በዚህም ላይ ታች ስትል ምኞትህን ለማሳካት ትታገላለህ እንዲሆን ሌላ ዘዴ ልትፈጥር ትችላለህ ይሁን እንጂ ሳይሳካልህ ቀርቶ በሃሳብና በጥረት ትታክታለህ ከዚያም ትበሳጫለህ፡፡

ከዚህ የከፋው ነገር በእነዚህ ምኞቶችና ተስፋዎች ስኬታማ አለመሆን ምክንያት ለመጥፎ ህይወት መዳረግህ ነው፡፡

እንደምትሰለች አውቃለሁ አዘንኩልህ እስከ መቼ ድረስ በምኞት ማዕበል ውስጥ ትኖራለህ? የምትመኘውን ባገኘህ ጊዜ ደስተኛ ትሆናለህ ይህ ደስታ ስለማያረካህ ሌላ አዲስ ደስታን እንድትመኝ ያደርግሃል፡፡ ልክ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "ከዚህ ውሃ የሚጠጣ ሁሉ እንደገና ይጠማል" ዮሐ 4-13 እንዳለው እርካታ አይኖርህም፡፡

ስለዚህ ውድ ወንድሜ ነገሩን በእርጋታ ከአንተ ጋር ለመነጋገር እፈልጋለሁ፡፡ "አለሙም ምኞቱም ያልፋል" 1ኛ ዮሐ 2-17 ታዲያ ይህን ቃል ካወክ ለምን አለማዊ ፍላጎቶችን ለማግኘት ትታክታለህ? አንተ ልክ እንደ እኔ ለመሬት እንግዳ ነህ፡፡አለም የሚያልፈበት አንተም የምትጠፋበት ጊዜ ይመጣል ልክ ከእናትህ ማህጸን ራቁትህን እንደመጣህ እንደዚሁ ራቁትህን ትመለሳለህ





ኢዮ1-21 አለምን ከነክብሯ ከነሀብቷና ከነስሟ ለቀሃት እንድትሄድ በመገደድ እንደማንኛውም ሰው ወደ መሬት ትወርዳለህ፡፡ ከዚያም ከአለም ያገኘሸው ስልጣን ደስታ ታዋቂነት ወይም ምንም ይሁን ምን ስጋህን ከሞት ሊከላከልልህ አልያም ስጋህን ከሚበሉት ትል ሊከላከልልህ አይችልም፡፡ በፍርድም ቀን ከአለም ሀብትና ንብረት ውጭ በእግዚአብሔር ፊት ትቆማለህ፡፡ መልካምም ይሁን ክፉ የስራኸው ስራ እንጂ የአለም ቁሳዊ ነገር አይከተልህም

ስለዚህ ውድ ወንድሜ ምኞትህንና ተስፋህን በአለም ላይ በማድረግ መታወክህ ለአንተ ጥሩ አይደለም ይህች ምድር እሾህንና አሜኬላን እንዳበቀለችልህ ትዘነጋለህ!

ከእኛ በፊት የነበሩና ምድርን ሊረግጧት የማይገባት የቅ.አባቶችን አሰርና ፈልግ ተከተል ቅድስናቸውን ያገኙት ይህችን አለም በመውደድ ሳይሆን በመናቅ ነበር ሁኔታዎች ሁሉ ተመቻችተውላቸው ሳለ በአለም ስላሉ ነገሮች ለማንኛውም ለአለም ምኞት ጉጉት አልነበራቸውም፡፡

ውድ ወንድሜ አሁንም የአለም ምኞቶች አሉህ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና" ማቴ 6-21 ልብህ የስጋን ምኞቶችን ስለተቆራኘ መንፈሳዊ ነገሮች በአንተ አመለካከት ዋጋቸውን ያጣሉ ይህ የክብር ጌታ እንደተፈተነው ዓይነት ፈተና ነው፡፡ ማቴ4-8-9

አሁን አስተውል እነዚህ ነገሮችን ብትይዝ በጥሩ ምኞት ያሰርካት ነፍስህን ብታጣ ጥቅሙ ምንድን ነው? ነፍስህ ነጻነትን ትሻለች፡፡



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



# ከስሜት ህዋሳት ተጽእኖ ነፃ መውጣት

በስሜት ህዋሳትህ ለብዙ ጊዜ ትመራለህ፣ መንፈስህ እነዚህን ስሜቶችህን በተቃወመች ጊዜ አጅግ ትቃወማታለህ:: ከዚህ ከስሜትህ ተጽእኖ መቼ ትላቀቅ ይሆን::

በዐይንህ ያየኸውን፣ በጆሮህ የሰማኸውንና በእጅ የዳሰስከውን ብቻ ታምናልህ:: በዓይንህ ካላየህ በጆሮህ ካልሰማህ ሁሉንም ነገር ትጠራጠራለህ ለጥርጣሬህ ምክንያቱ ምን ይሆን ለዚህ መንስኤ ምላሹ ያንተ በስጋ መኖርና በስሜትህ መመራትህ ነው::

ወዳህና ወዲያ ታማትራለህ፣ ማንም እንዳያይህና እንደይመሰክርብህ አጸያፊ ነገሮችን በድብቅ ታደርጋለህ:: ነገር ግን ማንም አንዳላየህ ታስብ ይሆናል:: ነገር ግን በርህራሄና በተግሳጽ የሚመለከቱህ ብዙ ዓይኖች አሉ:: አሁንም በስጋ ስላለህ እነዚያን ዓይኖች አታያቸውም:: ይኸውም አንተ የማታየው እርሱ የሚያይህ አምላክ እግዚአብሔር ነው:: በመንፈስ በምትሆንበት ጊዜ ከስሜትህ ተጽእኖ ትላቀቃለህ ከነቢዩ ከኤልያስ ጋር "በፊቱ የቆምኩ የሠራዊት ጌታ ህያው እግዚአብሔርን" 10 ዳገ 10: 15 ማለት ትችላለህ::

መከራ በሚገጥምህ ጊዜ ወደ ቀኝ ወደ ግራ ብታማትርም ራስህን ብቻውን ታገኘዋለህ፣ በጣም ትፈራለህ ትደነግጥማለህ::





በእርግጥ እንዳትደነግጥ እግዚአብሔር በቀኝህ ነው፡ ዐይኖችህ ሁሉን ነገር ማየት ስለማይችሉና ግዑዝ ስለሆኑ መንፈሣዊን ነገር ማየት አይችሉም:: ውድ ወንድሜ ከእነዚህ ከስጋዊ ስሜቶችህ መንፈስህን እንድታርቅ እመኛለሁ::

ይህ መንፈስ የአንተ ነው:: "መንፈስ የእግዚአብሔር ጥልቅ ነገር እንኳን ይመረምራል" 10 ቆሮ2:10 በነፃነት እግዚአብሔርን ለማየት ክፍ በል፣ በደስታም "በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም" መዝ 23÷4 ትላለህ::

የኤልሳዕ አገልጋይ የነበረው ምስኪኑ ግያዝ የጠላቶቹ ትልቅ ጦር ወደ እርሱ እየቀረበ ሳለ በጣም ፈርቶ ነበር፣ ምንም ዓይነት ተስፋ አልነበረውም ነገር ግን በመንፈስ ይኖር የነበረው ኤልሳዕ በልበ ሙሉነት ነበር:: የሰው ልጅ ዐይን ሊያየው የማይችለውን፣ ጆሮ ሊሰማው የማይችለውን በመንፈሣዊ ዓይን ተመለከተ:: በአገልጋዩም ሀዘን ተሰማው ወደ ጌታም የዚህ ሰው ዐይን ይከፈትለት ዘንድ ጸለየ "እግዚአብሔርም የብላቴናውን ዐይነ ገለጠ፣ አየም እነሆም በኤልሳዕ ዙሪያ ያሉትን የእሳት ፈረሶችንና ሰረገሎች ተራራውን ሞልተው ነበር" 2ኛ ነገ6÷17 ስለዚህ ተደሰተ::

ደካማ በሆኑና መንፈ.ሣዊ ነገር ሊረዱ በማይቻላቸው በስሜት ህዋሶችህ አትታመን:: የስራጵታዋ መበለት በስጋዊ ዐይኖቿ እፍኝ የምታህል ዱቄትና ጥቂት ዘይት በቆርቆሮው ውስጥ ተመለከተች እሷም ትንሽ ቂጣ ለእርሷና ለልጇ ከጋገረች በኋላ እርሷን በልተው እንደሚሞቱ አሰበች:: ነገር ግን ኤልያስ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



በመንፈሱ ከዚህ የበለጠ ታላቅ ነገር ተመለከተ "ዱቄቱም ሆነ ዘይቱ እንደማያልቅ ተመለከተ፡፡ 10 ነገ 17÷14-16"

ኤልሳዕ በዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ ቆሞ ነበር፣ በሥጋዊ ዐይኖቹም አንድ ሰው ወደ ውስጥ ቢገባ እንደሚያሰጥመው ተመለከተ፡፡ ነገር ግን መንፈሣዊ ዐይኖቹ ሥጋዊ ዐይኖቹ በተመለከቱት ነገር አልተወሰኑም፤ ዮርዳኖስ ተከፍላ ማለፊያ መንገድ እንደተፈጠረ አየ፣ ነገር ግን ኤልሳዕ ኤልያስ በእሳት ሠረገላ ሲያርግ ከኤልያሰ በተቀበለው መጐናጸፊያ ውሃውን መታው፣ ውሃውም ተከፈተ በዙያም መንገድ ተከፈተለት፡፡ 20 ነገ 2÷14፡፡

ሥጋዊ ዐይኖች የኤልያስን መጐናጸፊያ እንደተራ ጨርቅ ያዩታል፤ ኤልሳዕ ግን በመንፈሣዊ ዐይኖቹ ጨርቅ ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም መለኮታዊ ኃይል እዳለበት ተመለከተ፡፡

ወንድሜ ዐይኖችህ ግዑዝ የሆኑ ነገሮችን እንኳን ለማየት በቂ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከዐይን እይታ ውጭ በአጉሊ መነጽር ብቻ የሚታዩ ነገሮች ብቻ አሉና፡፡

የአጉሊ መነጽር ካልተጠቀምክ ጥቃቅን ህዋሳትን በዐይነ ሥጋህ ማየት ካልቻልክ ስላላየሃቸው መኖራቸውን ትጠራጠራለህ፡፡ ግዑዝን ነገር አስመልክቶ እንዲህ ከሆነ ስለመንፈስና ስለመንፈሣዊ ነገር አስመልክቶ ምን ትላለህ?

ለመንፈሣዊ ነገር ቀዳሚነትን በመስጠት መንፈስህ ይምራህ "ሳያዩህ የሚያምኑ ብፁዐን ናቸው" ዩሐ 20፥29 እንደተባለ መንፈስህ ወደ ሰማይ ይወጣ ዘንድ፣ የእግዚአብሔር





በሆነው ዓለም ውስጥም ይዋኝ ዘንድ ፍቀድለት መንፈስህም ህዋሶችህን ይመሩ ዘንድ ፍቀድ፡፡

አንድ ቀን አንድ ሰው ቅ.ጊዩርጊስ በቤተ ክርስቲያን እንደተገለጸ ነገር ግን እሱ ይህን እንዳላመነ ነገረኝ፡፡ በራሱ ለማየትና ምትሃት አንደሆነ ለማረጋገጥ ሄደ ነገር ግን ምንም አልተመለከተም፡፡

ስለዚህ ታሪክ ምንም ዓይነት ማብራሪያ መስጠት አልፈልግም፡፡ ነገር ግን ዋናውን ነጥብ ላቅርብ፡፡ ይህ ሰውና እርሱን መሰሎቹ በደካማ እምነታቸው ምክንያት ማንኛውንም ራዕይ ማየት አይችሉም፡፡ እግዚአብሔር እራሱንና የመንግሥቱን ክብር በገለጠላቸው ጊዜ እነሱ መንፈሣዊ የሆኑ ነገሮችን በስጋዊ ስሜቶቻቸው ማሸነፍ ይፈልጋሉ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



# ከዓለም አንዳች አልሻም

**አንድ ሰው የመንፈስ ነፃነት ከፈለገ ከአለም አንዳች አይሻም**

ዓለምን የሚመኟት ስላልሆነች ከአለም ምንም አልፈልግም ነገር ግን ይህ ለወጣንያን እንቅፋት ነው።

ዓለም ችግር የበዛባትና ምንም ልትሰጠኝ ስለማትችል ከእርሷ ምንም አልሻም። በዓለም ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ እኔን የሚማርክና የሚያረካ ቢሆንም እንኳን ይህ ዓለም መንግሥተ ሰማይ አይደለም። ከሚታዩና ከሚያስደስቱ ነገሮቿ በስተቀር ምንም የላትም። በእርግጥም ስለ ሰማያዊው ነገር፣ ስለ እግዚአብሔር ህልውናና ስለመንፈስ ቅዱስ እንረዳበታለን።

የዓለም ስላልሆንኩ ከአለም ምንም አልሻም። እንደሚያስቡኝ አፈር አይደለሁም፣ መለኮታዊ እስትንፋስ እንጂ፣ በዘላለማዊ ህይወት ከእግዚአብሔር ጋር ነኝ። ነገር ግን እግዚአብሔር በምድር ላይ አስቀመጠኝ። ትቼው ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለብኝ፣ ስለዚህ ከዚህች ምድር ምንም አልሻም "ከአብ ወጥቼ ወደ አለም መጥቻለሁ፣ ደግሞ አለምን እተዋለሁ ወደ አለም እሄዳለሁ ዮሐ 16:28"

ከአለም ለማግኘት የምመኛቸው ሁሉ የሚጠፉ ናቸው። ከሥጋና ከምድራዊ ህይወት መራቅን እፈልጋለሁ። በአለም ሊረክስ እንዳማይችለው እንደቀድሞው እስትንፋስ መሆን እፈልጋለሁ። ህያውነትንና ዘላለማዊነትን ስለምፈልግ ከአለም ምንም አልሻም። አለም ዘላለማዊ የሆነ ነገር የላትም። በአለም ውስጥ ያሉ ሁሉ





ጠፊና ረጋፊ ናቸው፣ አለም ራሷ ቀልጣ ትጠፋለች ስለዚህ የሚጠፋን ነገር አልሻም።

ሁሉን ቻይና ስጦታው የማያልቅበት አምላክ ስላለኝ ከዚህች ዓለም የምሻው አንዳች ነገር የለም። ምክንያቱም እርሱ ሳለምነው የምፈልገውን አውቆ የሚሰጠኝ አምላክ ነውና።

እኔን ለመጣል ካልሆነ በቀር ለእኔ የሚጠቅም ነገርን ስለማትሰጠኝ ከአለም ምንም አልሻም። አለም የምትሰጣቸውን የሚቀበሉ እነሱ የአለም ባሪያዎች ናቸው። ለሥጋቸው ደስታን በመስጠት የነፍሳቸውን ቅድስናና ንጽህና ትወስዳለች፣ የራሷን ደስታ በመስጠት ሰማያዊውን መንግሥት ትነጥቃለች። ሰይጣን ክብራቸውን በማሳጣት እርሱን እንዲያመልኩት ለማድረግ የዚህን ዓለም መንግሥታት ክብር ሰጣቸው ሰይጣን ለሰዎች ነፍሳቸውን እንዲያጡ የሚያደረጋቸውን ነገር ብቻ ይሰጣቸዋል። "ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቆጥራለሁ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ" ፊል 3:8

ይህች ዓለም ከምትሰጠኝ ይልቅ የሚበልጠውን ትወስድብኛለች ስለዚህ የሚያምኗት ተገዢዎቿ ናቸው። ከዓለም አንዳች ነገር አልፈልግም የምለው ለዚህ ነው።

እኔ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠርኩ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የመንፈሱም ማደሪያ ነኝ። ቅዱስ ስጋውን ክቡር ደሙን የምቀበል ብቸኛ ፍጡር ነኝ። የሰማይና የምድር መክፈቻ የተሰጠኝ ባለስልጣን ነኝ። በእርሱም ፈቃድ የአለም ብርሃን የምድር ጨው ነህ ተብሉ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



የተነገረልኝ ነኝ። ማቴ 5:13 በዚህ ሁሉ ከአለም በላይ ስለሆንኩ ከአለም አንዳች አልፈልግም።

ምድርን ሊረግጧት ያልተገባቸው የቀደሙ ቅ.አባቶች ከአለም ምንም ሳይወስዱ በዚህች ዓለም ኖሩ። እነርሱም በምድር ላይ በመኖር ለምድር በረከትና ለዚህች አለም አለመጥፋት ምልክቶች ሆኑ ምክንያቱም እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቶ ለምድር ዝናምን ሰጠ፣ በጸሎታቸውም ህዝቡን ይጠብቅ ነበር እኔም አባቶቼን መምሰል ስለምሻ ምንም እንኳን በዓለም ውስጥ ብኖርም ከአለም አንዳች ነገር አልሻም።

በስነ ፍጥረት ታሪክ ውስጥ እንደምረዳው ኃጢያት ከመታወቁና ሞት ወደዚህች ዓለም ከመግባቱ በፊት በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ተመለከተ እነሆም መልካም ነበር። የአለም ፍጥረታት እንኳን ሳይቀር እንዲያፈሩና እንዲበዙ እግዚአብሔር የተባረኩ ነበሩ። እግዚአብሔር ግሩም አድርጐ ያከናወናቸው ሥራዎቹ አሁን ታውከዋል። ስለዚህ ከብርሃን ይልቅ ጨለማ ከህይወት ይልቅ ሞትን ከመረጠች ዓለም አንዳች አልሻም።

አምላኬ ሆይ እስከ መጨረሻ የወደድከኝና ቤዛ የሆንከልኝ አንተ ብቻ ነህ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣኸኝና ዳግመኛም ስምህን እንድቀድስና ክብርህን እንድወርስ የፈጠርከኝ አንተ እንጂ ለመፈጠሬ የእኔ ጣልቃ ገብነት የለም።

ስለዚህ ከአለም የራኩና ይልቁንም አንተን እንዳውቅህ የሚያደርገኝን ጸጋ ከምትሠጠኝ ከአንተ ጋር አንድ መሆንን ስለምፈልግ ከአለም አንዳች አልሻም።





# አስተማሪ እግዚአብሔር ነው

ከትምህርት ዓለም የራቁም ከሰው የተማሩም እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት አላዋቂዎች ናቸው። ነገር ግን የተማሩ /ምሁራን/ የሚባሉት በእግዚአብሔር የተማሩ ናቸው።

እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረው ጊዜ እጅግ አዋቂ አድርጎት ነበር። አንደ አላዋቂ ሌላ እውቀት በፈለገ ጊዜ በእግዚአብሔር የተማረ ነበር። ሰውም በዚህ የዕውቀት መንገድ ቢጓዝ ኖሮ አዋቂ ይሆን ነበር፣ ዕፀ ህይወትን በልቶ ለዘላለም በኖረ ነበር። ነገር ግን ሰው ዕውቀትን ከእግዚአብሔር ውጭ ከሌላ ምንጭ በተቀበለ ጊዜ አላዋቂ ሆነ። የመጀመሪያውን ትምህርት ከእባብ ወስዶ የዕውቀትን ዛፍ በበላ ጊዜ አላዋቂ ሆነ። ሰው አሁንም ዕውቀትን ከእግዚአብሔር ውጭ ይመኛል ነገር ግን የማያገኘው በድንቁርና ላይ ድንቁርና ነው።

ሰው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስና የመንፈሱ ማደሪያ ነው መንፈስ ቅዱስን ኢየሱስ ክርስቶስ "ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል" ዮሐ 16:13 ብሏል። ቅዱስ ጳውሎስም "መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል" 1ቆሮ 2:10 ይላል።

ይሁንና ሰው ካለማወቁ የተነሣ ከባህርዩ ዕውቀት ውጭ ከሰዎችና ከመጽሐፍት ማግኘትን ይሻል። ስለዚህ የዚህ ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነው።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ውድ ወንድሜ ሰው አዋቂ ነው ሊባል የሚችለው በክርስቶስ ሞት ባገኘው ህይወት አዳም በተፈጠረ ጊዜ ከነበረው ዕውቀት በላይ ዕውቀትን በሚያስገኘው ህይወት መኖር ሲችል ነው፡፡

ውድ ወንድሜ ማንም እግዚአብሔርን ከእርሱ ውጭ ለማግኘት ከጣሩ መንገዱን ይስታል፡፡ ነገር ግን ብቻህን ሁን፣ አገናዝብ፣ አስብ በውስጥህም እግዚአብሔርን ፈልግ፡፡ ከዚያም ከጥልቁ ልብህ ውስጥ ታገኘዋለህ፡፡ ፊት ለፊትም ታየዋለህ፡፡ ፍቅሩም ማለቂያ እንደሌለው እንደ ክረምት ውሃ እንደሆነ አስብ፡፡ በዚያም እጅግ ትደነቃለህ እግዚአብሔርን አየሁት እያልክ በፍፁም ደስታ ትሞላለህ፡፡

ቅዱሳን አባቶችን የተጓዙበትም ዋናው መንገድ ይህ ነበር፡፡ አለምን ናቁት፣ እግዚአብሔርን በውስጣቸው ፈለጉት፡፡ ሁሉንም ነገር ስለሰሙ ተው፣ በማያቋርጥ ምስጋናና በተመስጦ ሊያዩት ቻሉ፡፡ ነገር ግን ብዙ በአለም አዋቂዎች ነን ባዮች እግዚአብሔርን ከመጽሐፍ ከሰዎች ፈለጉት ያተረፉት ነገር አላዋቂነትን ነበር፡፡

ይህን ሳወሳ ለእነሱ ሀዘን ይሰማኛል ነገር ግን ስለዚህ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ፍለጋ አለምን ትተው ወደ ገዳም ከገቡ በኃላ እግዚአብሔርን ከመጽሐፍ ለማግኘት የሚያስቡትን ሳስብ እጅግ አዝናለሁ፡፡ በእርግጥ እግዚአብሔር በልቡናቸው ሲኖርም ከእርሱ ጋር ያላቸው ህብረት እንዲጸናና ይህን ሀሳባቸውን እንዲተው ይፈልጋል፡፡ እንጂ በደካማ ሀሳባቸው ሲተዋቸው አልወደደም፡፡ የሰው ልብ ያላሰበውንና የሰው ዐይን ያላየውን ምሥጢር ሊገልጽላቸው ወደደ፡፡





ይህ ትምህርት ሁላችንንም የሚመለከት እንጂ ለገዳማውያን ብቻ የሚተው አይደለም፡፡ ውድ ወንድሜ ለመንፈሣዊው ትምህርት ትክክለኛው መንገድ ምን እንደሆነ ታውቃለህ? በእርግጥ ዕውን አዲስ ነገር ለማስተማር አይደለም፡፡ በውስጡ ብዙ ነገር ስለያዘ አንተ ከምታስተምረው በላይ ያውቅ ይሆናል ስለዚህ ተፈጥሮው አንተ ከምታስተምረው በላይ ሊያሳውቀው ይችላል፡፡ ነገር ግን ትክክለኛው የማስተማር መንገድ ሰውን ከስህተት ጐዳና መመለስ ነው፡፡

አንድ ሕጻን በአእምሮው፣ በሐሳቡ፣ በልቡ ስለ እግዚአብሔር እጅግ ትልቅ ዕውቀት ይዞ ይወለዳል፡፡ ከዚያም ህብረተሰቡ ይህን ሕፃን እንደራሱ ባህልና ልማድ እግዚአብሔር እንዲህ ነው ይለዋል በዚህ ጊዜ እግዚአብሔርን የማወቂያው መንገድ ይዘጋል፡፡ እናም ይህን ሕፃን አባቱ አዳም መልካሙንና ክፉውን ከሚያሳውቀው ፍሬ በልቶ ዕውቀትን እንደፈለገ ሁሉ የዚህም ሕጻን ዕውቀት በአካባቢው የዕውቀት ተጽእኖ ተሰውጧል፡፡ ነገር ግን መንፈሱ ከእነዚህ ነገሮች በራቀ ጊዜ ዕውነተኛውን ዕውቀት እግዚአብሔርን ያውቃል ምክንያቱም ሰዎች እንደሚያስቡት እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያለ እንጂ የራቀ አይደለም፡፡

ትክክለኛው ትምህርት ስለ እግዚአብሔር የሚያውቀውን ማስጣል ሳይሆን ከመጥፎ ልማድ፣ ከባህል የቀሰመውን ዕውቀት ማስጣል ወይም ማስተው ነው፡፡ እርሱም ከዚህ ዕውቀት ከተላቀቀ እግዚአብሔርን ያውቃል ትክክለኛም ዕውቀት ይኖረዋል ምክንያቱም በእርሱ ውስጥ ያለ እንጂ ከእርሱ የራቀ አይደለም፡፡



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



# አለማወቅህን እወቅ

አስተማሪ የመሆን ምኞት በጣም ትልቅ አደጋ ያስከትላል። እና ውድ ወንድሜ እስከቻልክ ድረስ ከዚህ ነገር ለመራቅና ምኞቱን ለማስወገድ ሞክር።

ሰዎችን ለማስተማር ትፈልጋለህ? መልካም ግንምንዓይነት ትምህርት ልታስተምር ትወዳለህ?

ውድ ወንድሜ አሁን ስለ እያንዳንዱ ነገር በቂ ዕውቀት የለንም ይህን ሀሳቤን እንደምትጋራልኝ አስባለሁ። የተረዳናቸው ወይም ያወቅናቸው የሚመስሉን ነገር ግን ብዙ ያልተረዳናቸውና ያላወቅናቸው ነገሮች አሉ። ለምሳሌ የሃይማኖት ትምህርትን ሌሎች በምናስተምርበት ጊዜ እኛ እንደተገነዘብነው እንጂ እንደ እግዚአብሔር አናስተምርም። የኋላ ኋላ በመንፈሳዊ ህይወታችን አድገንና በመንፈሳዊ ዕውቀታችን መጥቀን ማንነታችንን ስናውቅ ትናንት የነበረንና ዛሬ ያለን የሃይማኖት ትምህርት ይለያያል። እንዲህ ከሆነ ታዲያ አስቀድሞ ከእኛ ሃይማኖትን የተማሩት እነኛ ሰዎች ለምን ዓይነት ሁኔታ ይሆኑ ይሆን?!

ይህን አስመልክቶ በተጨማሪ ሐዋርያው ያዕቆብ ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ፣ የባሰውን ፍርድ እንድንቀበል ታውቃላችሁና። ሁላችንም በብዙ ነገር እንሰናከላለንና ያዕ 3:1-2 ይላል።

ነቢዩ ኤርምያስ ለእግዚአብሔር እነሆ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም ኤር 1:6 ይላል።





ነብዩ ኢሳዪያስ ስለራሱ «እኔም ከንፈሮቼ ረከሱብኝ ሰው ነኝ» ኢሳ 6:5 ይላል። ብዙ አባቶችም ብዙ ጊዜ ራሳቸውን እንደ አላዋቂ ያደርጋሉ እንጂ በኩራትና በትዕቢት አዋቂ ነኝ አይሉም።

አንድ ወጣት መነኩሴ ወደ አንድ አባት ለትምህርት በመጣ ጊዘ በበዓትህ ቆይ በዚያም ብዙነገር ትማራለህ አለው። ያም መነኩሴ ምክሩን በመቀበል ወደ በዓቱ ተመለሰ።

ብዙ በማንበብ እግዚአብሔር በሚሰጥህ ዕውቀት እንድትጠቀም የተውኩልህ ብዙ ታሪኮች አሉ። ወደ ሌላ ርዕስ ከማለፌ በፊት አንድ ነገር ላስገነዝብህ እወዳለሁ። የብዙ አባቶቻችን ጽሑፍ የደረሰን በአንድ መንገድ ብቻ አይደለም። ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች አባቶች በሚያወሩበት ጊዜ ብሂሎችን ይጽፋሉ ወይም እኒህ አባቶች ለመንፈሳዊ ጥቅማቸው ሲሉ የዕለት ተለት ውሏቸውን ጽፈው ያስቀምጣሉ። እነኚህ ጽሑፎች እኒህ አባቶች በሞት በተለዩ ጊዜ ለሚመጣው ትውልድ መማሪያ ይሆናሉ።

ውድ ወንድሜ መጽሐፍ ቅዱስ ለማስተማር አደራ በተሰጣቸው በጥቂት ሰዎችና መምህር በመሆን መካከል ልዩነት አለው። መምህር ለመሆን ማሰብ መጨረሻው አደገኛ ነው። መምህር ለመሆን መፈለጋችን ምናልባትም የመጥፎ ነገር መደበቂያ ይሆናል። የማስተማር ጥማት የሚመነጨው ምንጊዜም በተደበቁ ነገሮች የታጀበና ግልፅ በሆነ ስሜት ራሱን ለመጥቀምና ከሰዎች የበላይ ለመሆን ነው። ይህ ሰው አስተማሪ እንዲሆን እድሉ በተሰጠው ጊዜ ይህ ስሜት በውስጡ ይጎለብታል። ወደ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ቤተክርስቲያን ሲገባ እንኳን ለአምልኮና ለመጠቀም ሳይሆን፣ መምህራንን ለማረምና ለመተቸት ይሆናል። ምንግዜም ተናጋሪ እንጂ አድማጭ መሆንን አይሻም። ይህም ሰው ያለው ዕውቀት ወቅታዊ ስለሚሆን የሚናገረውን የሚያጣበት ጊዜ ይመጣል።

ቅ.መቃርዮስ በቪኒት በረሃ ብዙ ነገር የሚያውቅ ሰው ሆኖ ከአንድ ህፃን ሲማር እንመለከታለን። ብዙ አባቶቻችን ብዙ የሚያውቁ ሆነው ሳሉ የዕውቀት ምንጩን አይንቁም ነበር። እነዚህ ቅዱሳን ከሁሉም አበቦች ማርን ለመቅሰም እንደምትበር ንብ ነበሩ።

ማስተማርን ከመውደድ የሚመጣ ሌላኛው መጥፎ ገጽታ። አንድ ሰው አስታውሳለሁ፣ ይህም ሰው ዕለት ተለት መጽሐፍ ቅዱስ ያነብ ነበር፤ ነገር ግን በዚህ ጊዜ ከዚህ መጽሐፍ ለመጠቀም ሳይሆን ትምህርትን ለማዘጋጀት ነበር። ምጽዋት በሚሰጥበት ጊዜ ድሃውን በመውደድና ለድሃው በማዘን ሳይሆን ሌሎች እንዳይሰናከሉበት በመጠንቀቅ ነው። ከሰዎች ጋር በሚቀመጥበት ጊዜ ከእነሱ ምንም ለመማር አይጥርም ነገር ግን እንደ መምህር ያሉትን ለመመርመር ይወዳል። አንድ ጊዜ ይህ ሰው ለመጸለይ ቆሞ ሳለ መንፈሰ እግዚአብሔር ሲቀርበው ባየ ጊዜ ጸሎቱን ሳይጨርስ ጸሎቱን ሊያቋርጥ አላመነታም፤ ይህን ነገር ለሰዎች ለማስተማር ተቀምጦ መጻፍ ጀመረ። ስለዚህ በዚህ ሰው ህይወት የተነሳ የብዙ ሰዎች አላማ መንገዱን ይስታል። ማስተማር ለዚህ ሰው ሁሉ ነገሩ ነው። የእግዚአብሔር ጸጋና መለኮታዊ ምሪት በዚህ ሰው ውስጥ ቦታ የለውም።





አንድ ነገር ልነግርህ እወዳለሁ። ሰዎችን ምን ማስተማር ትፈልጋለህ? ሐይማኖት ነው? ሐይማኖት በሰዎች ዕውቀት እንዲወሰን ታስባለህ? ውድ ወንድሜ ሃይማኖትን ልክ የቀለም ትምህርት እንደምታስተምረውና እንደምታጠናው

ከሆነ እጅግ እፈራልሃለሁ። በእርግጥ ሃይማኖት ህይወትና መንፈስ ነው።

ከዚያም ይህ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መምህር ነኝ ታዲያ ምን ማድረግ ይጠበቅብኛል ሲል የጠየቀኝ፤ እንዲሁም መለስኩለት ውድ ወንድሜ መንፋሳዊ ኑሮ ትኖር ዘንድ እመኝልሃለሁ። እውነት እልሃለሁ የምታስተምራቸው ግዴታ ወይም አደራ ስላለብህ ሳይሆን ስለወደድካቸው ይሁን። እነዚህ በአካባቢህ የምታስተምራቸው ሰዎች በትምህርትህ ዕውቀት ሳይሆን በፍቅርህ የሚማረኩ ይሁኑ። በእውነተኛ ፍቅር ትርጉም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



# አንዳች የሌለህ ስትሆን ሁሉ የእኔ ነው አትበል

ብዙ ሰዎች ራሳቸውን እንደ ባለጸጋና ብዙ የዓለም የሆኑ ነገሮችን ገንዘብ ያደረጉ ይመስላቸዋል። ነገር ግን ውድ ወንድሜ የባለጸግነት ስሜት ነፍስህ ማድረግ የሚገባትን እንዳታደርግ መሰናክል እንዳይሆንባት ስለተገነዘብክ ከዚህ ምኞት የተከለከልክ ሁን።

በእርግጥ ወደዚህች ዓለም ልክ እንደ እኔ ከውስጧ ምንም ሳታገኝ ባዶ እጅህን መጥተሃል። ከእናትህ ማህጸን እንኳን ራቁትህን ነው የመጣኸው። ከጊዜ በኋላ ያገኘኸው ማንኛውም ነገር ከእግዚአብሔር ለአንተ የተሰጠ ጸጋ ነው። ይህም የራስህ ንብረት ሳይሆን ለምድራዊ ህይወትህ ብቻ የሚያስፈልግህ ኃላፊና ጠፊ ነው። ከዚህች ዓለም በምትለይበት ጊዜ ልክ እንደአመጣጥህ ባዶ እጅህን ትመለሳለህ።

ታዲያ አንተም ራስህ በራስህ ኃይል የተገኘህ አይደለህም። ምክንያቱም አስቀድመህ ከመፈጠርህ በፊት በራስህ ህልውና አልነበረህም። እግዚአብሔር ግን ካለመኖር ወደ መኖር አመጣህ። ይህን አንተነትህንም በጣልከው ጊዜ በሞትና በሲኦል ተያዝክ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ውድ በሆነ ደሙ ዋጅቶ የራሱ አደረገህ።

ስለዚህ አንተ ራስህ በራስህ ላይ ማዘዝ እንደማትችልና በአንተ ላይ እግዚአብሔር ብቻ እንደሚያዝ ተገንዘብ። አንድ ሰው ራሱን በመቃወም ኃጢያት ሲሰራ የእግዚአብሔር የሆነ ማንነቱን በመቃወም እግዚአብሔርን ያሳዝናል። ምክንያቱም ንብረትነቱ





የእግዚአብሔር የሆነችው ነፍሱንና ለመንፈሱ ማደሪያ ይሆን ዘንድ ያዘጋጀውን ስጋውን ያረክሳልና።

በተመሳሳይ መልኩ ሰው በሌሎች ላይ ወንጀል ሲፈጽምና ኃጢያት ሲያደርግ እንደዚሁ ነፍሱን ያረክሳል። በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ ኃጢያት መስራት እግዚአብሔርን መቃወም ነው። ዳዊትም ኦርዮንና ሚስቱን ቤርሳቤህን በበደለ ጊዜ ኃጢያቱን ሲናዘዝ አንተን ብቻ በደልኩ መዝ 51፤4 ብሎ ወደ እግዚአብሔር የጮኸው ለዚህ ነበር። ዳዊት ይህን የተናገረው እግዚአብሔርን መበደሉን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር የሆኑትን ሁለቱን ሰዎች መበደሉንም ጭምር ነበር።

ሀብትንና ንብረትን አስመልክቶ እኛ ምንም እንደሌለን ገልጸናል።፤ ነገር ግን ሁሉም ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ጸጋ ነው። እንደ መልካም አስተዳዳሪ ያለህን ንብረት በትህትና ለመምራት ያስቀመጠህ እንጂ የአንተ አይደለም። እግዚአብሔር የመጋቢነትህን ሒሳብ አስረክበኝ ሉቃ 16፤2 ባለህ ጊዜ ተጠያቂ ትሆናለህ።

እንዲሁም ከሆነ ልክ እንደ ዳዊት፤ ንጉሥ ሆኖ ሳለ ትሁት የሚሆን፤ ሁሉ የእርሱ ሆኖ ሳለ እኔ ችግረኛና መስኪን ነኝ መዝ 70:5 የሚል አንዳች እንደ ሌለው ይናገራል። ነገር ግን ሰዎች ዳዊት ንጉሥና ባለጸጋ ሳለ እንዲህ ማለቱን አይቀበሉትም ግን በመንፈሳዊ ህይወት ለሚኖሩት የዳዊት ንግሥናና ሀብት ከእግዚአብሔት የተሰጠው ጸጋ እንጂ የራሱ እንዳልሆነ ያውቃሉ።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ቅዱሳን አባቶቻችን ሃብት ንብረታቸውን ትተው ለድሃ መጽውተው ወደ ገዳም በመሄድ በጾምና በጸሎት ተወስነው የዚህችን ዓለም ሀብትና ንብረት ንቀው ይኖራሉ።

ይህም ትክክለኛውን የትሩፋትን ሥራ ትርጉም ይሰጥሃል። እግዚአብሔር ከሰጠህ ጸጋ እንጂ ራሴ አለኝ ብለህ ከምታስበው ሀብትህ እንደማትሰጥ ዕወቅ። ይህን ካወክ ለመመጻደቅና ለመታበይ ምክንያት አይኖርህም ሰዎችም እንደ ጥሩ ሰራተኛ እንዲያመሰግኑህ ለመፈለግ ምክንያት አይኖርህም።

ካለው ላይ ሳይቀነስበት መስጠት የሚችል አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው። በእርግጥ የትሩፋት ሥራ ከመልካም ሥነ ምግባር አይመደብም፤ ምክንያቱም በሚሰጠው ሰው የሚደረግ ሥጦታ አይደለምና። እርሱ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለሌሎች የማስተላለፊያ መንገድ ነው።

ሌላው ነጥብ ከበጎ አድራጎት ጋር የሚመሳሰል፤ ምሥጋናን መቀበል ነው። ውድ ወንድሜ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ፤ አንተ የራስህ ካልሆነ ሃብት ስለምትሰጠው ነገር ምሥጋና መቀበልን እንዴት ታየዋለህ? የእግዚአብሔር ሀብት ስለሆነ እንዴት በእግዚአብሔት ፈንታ ምስጋናን ትቀበልበታለህ? ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ፤ እግዚአብሔር የሠራኸውን ሁሉ ስለሚገልጥብህ በራስህ አትመጻደቅ።

የባለጠግነት ምኞት ነፍስህ ማድረግ የሚገባትን ከማድረግ ያግዳታል። ምንም እንደሌለህ እንድታስብ ያደርጋታል።

ስለዚህ ከዚህ ሀሳብ ለማምለጥ ስለ ራስህ ማንነት እንድትረዳ እንጂ ራስህንመካድ አለብህ ማለት አይደለም።





# የልብ ቅድስና ይኑርህ

ውድ ወንድሜ ከራስህ ተጽዕኖ ተላቀቅ። በዚህ ጊዜ ከራስህ ጋር መግባባት እንደምትችልና የውስጥህን ሰላም ካረጋገጥህ ውጫዊ ሁኔታዎች ተጽዕኖ እንደማያደርጉብህ ተረዳ። በተጨማሪም አንተነትህ ከራስ ወዳድነት እንደተላቀቀ መናገር ትችላለህ።

ውድ ወንድሜ ዓለም በአንተ ላይ ኃይል እንዳለው ታስባለህ? ወይስ መሰናክሎችና ፈተናዎች ለውድቀትህ መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ? እንዲህ የምታስብ ከሆነ እጅግ የተሳሳትክ ነህ። ዓለም ወይም ምኞቷ ተጽዕኖ ሊኖራቸው ይችላል ነገር ግን ለውድቀትህ ምክንያት ዋናው መንስኤ የውስጥ ማንነትህ ነው።

### የኃጢያት ተገዢና የዓለም ወዳጅ ካልሆንክ በስተቀር ፈጽሞ አትወድቅም

ምንም እንኳን ጻድቁ ዮሴፍ ኃጢአት በበዛበትና በሚከናወንበት አካባቢ ቢኖርም ራሱን በኃጢአት አላረከሰም። ለምን ቢባል ዮሴፍ ከልቡ ንጽሕና የተነሣ በኃጢአት ላይ ኃይልና ጉልበት ነበረው። አፍአዊ ኃጢአትን ለማሸነፍ ውስጡን ያነፃ ቅዱስ ነበር።

ዓለም መሰናክል ወይም ጥፋት የበዛባት ስለሆነች እስነካከላለሁ አትበል ይልቁንም የልብህ ርኩሰት መሰናክል እንደሚሆንብህ ተረዳ።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ሁለት ሰዎችን እንደምሳሌ እንመልከት ሁለቱም በመሸታ ቤት አጠገብ እያለፉ ሳለ አንደኛው በወይን የተሞላውን ጠርሙስ ተመልክቶ ማለፍ ስላልቻለ ወደ ውስጥ በመግባት እኪሰክር ጠጣ። ነገር ግን ሁለተኛው ሰው ልቡ ንጹህ ስለ ነበር ይህ ነገር ተጽእኖ ሊያደርግበት አልቻለም። ልቡ ንጽህ ስለነበር ከውጭ የሚመጡ ነገሮች ሊጎዱት አልቻሉም።

የመንፈሳዊ ህይወትህ አሸናፊነት በአንተነትህና በአንተ መካከል ማቆራኘት ካልቻልክ በሚፈጠረው ትግል ላይ የሚመሰረት ይሆናል። ምኞትህን በውስጥህ ከቸነከርክ በዚህ አለም የምትጠቀም እንጂ የምትሰነካከል አትሆንም።

አንዳንድ ሰዎች የአካባቢያቸውን መሰናክል ያስወግዳሉ። ይህ መልካም ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር በኃጢያተኞች መንገድ እንዳንሄድና በዋዘኞች ወንበር ላይ ከመቀመጥ ይጠብቀናልና። መዝ1፤1። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ውስጣቸውን ሳያነጹ መሰናክሎችንና ተጽእኖዎችን ብቻ የሚያስወግድ ከሆነ ይህ ትክክል አይደለም። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ላልተወሰነ ጊዜ ብቻ ውጤታማ ይሆናሉ፤ ይሁን እንጂ በራሳቸው ምኞትና በሥጋዊ ፍላጎታቸው ተሰነካክለው ይወድቃሉ። ምክንያቱም ኃጢያትን ባይሰሩም ኃጢያትን ይወዳሉና።

እንደዚህ ዓይነት ሰዎች በአካባቢያቸው ያለውን የኃጢአት ተጽእኖ ማስወገዳቸውን ለእግዚአብሔር ፍቅር ሲሉ ራሳቸውን መስዋዕት ያደረጉ ያህል ይሰማቸዋል። በእርግጥ እነዚህ ሰዎች ክፋት ከሚያስደስታቸው የዓለም ምኞት ካስከራቸው ኃጢአት ያስደስተናል ብለው ከሚያስቡት ጋር ተመሳሳይ ናቸው። እስካሁን እንደ ሔዋን ያችን ዛፍ ለመብላት መልካም እንደሆነች ለዐይን ማራኪና ደስታ የምትሰጥ እንደሆነች እያዩ ነው። ዘፍ3-6 ነገር





ግን ከሔዋን በአንድ ነገር ይለያሉ ከዛፉ ፍሬዋን ቀጥፈው ባለመብላታቸው ውስጣቸውን አላሸነፉም እግዚአብሔር በልባቸው ጽላት የለም። ስለዚህ በአለም ውስጥ የሚፈትናቸውንና የሚያሰነካክላቸውን ይፈልጋሉ። ምንም እንኳን በኃጢአት መውደቅ ቢያሳፍራቸውም በዓይናቸው አምሮትና በልባቸው ምኞት ይወድቃሉ።

ለእግዚአብሔር ህግ በዘልማድ ለሚታዘዙ ነገር ግን ህጉን ለማያፈቅሩና የህጉን ባለቤት ለማያውቁ ሰዎች መነገር የሚችል ቃል ነው።

እነዚህ ሰዎች በትልቅ ትግል አይጸኑም እንጂ የሚጸኑ ከሆነ ከተወረወረባቸው ከእሳት ነበልባል ተነጥቀው መዳን ይችላሉ 1ኛ ቆሮ 3-15 ነገር ግን በዚህ ትግል ካልዳኑ ቤታቸው በአለት ላይ አልታነፀምና በትልቅ አወዳደቅ ይወድቃሉ።

ታዲያ መንፈሳችንን ነፃ ለማድረግ እውነተኛው ነገር ምንድነው ቢባል ከኃጢአት እስራትና ኃጢአትን ከመውደድ መላቀቅ መቻል ነው። አንድ ሰው እንደዚ ከኃጢአት እስራት የተፈታ ከሆነ ሌሎች በሚፈተኑበት ነገር አይፈተንም። ቅዱሱ ተፈጥሮውም እነዚህን ነገሮች አይቀበላቸውም ስለዚህ ምላሽ አይኖረውም። በሌላ መልኩ ይህ ሰው ከእርሱ በኩል ምንም ዓይነት ጥረት ሳያስፈልገው ከእነዚህ ነገሮች መራቅ ይቻላል። በእግዚአብሔር አጋችነትና ለመንፈስ ቅዱስ ጥበቃ ህይወቱን ዕለት ተለት በቅዱስና መንገድ ይመራታል።

ይሁንና አስቀድመን እንደተናገርነው አንድ ሰው ውስጡን ካላነፃ በውስጡ ያሉትን የስጋ ምኞቶችና የዓይን አምሮት ካላሸነፈና ካላስወገደ በስተቀር እንዲህ ዕይነቱን የቅድስና ህይወት መኖር አይችልም። አንድ ሰው ኃጢአት እንዴት አሰቃቂና



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ውጤቷም ሞት እንደሆነ መመስከር አለበት፡፡ እግዚአብሔር መልካም ነው፡፡ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግና- ህይወትን በእግዚአብሔር ህግ መምራት እጅግ ያስደስታል፡፡

በዚህ በውስጣዊ ውጊያ ስጋውን እየጎሰመ ራሱን ለእግዚአብሔር ማስገዛት አለበት፡፡ 1ኛ ቆሮ9-27 ይልቁንም የልቡን ምኞትና የዓይኑን አምሮት በውስጡ ሊቸነክር ያስፈልጋል፡፡ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይህ ሰው ህይወቱን ከመራ የስጋውን ምኞት የሚያርቅና የሚገቅ ይሆናል፡፡ ለዚህም ነው በማርቆስ ወንጌል "ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ያጠፋታልና ስለ እኔና ስለወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን ያድናታል ማር8-35 ብሎ ያስተማረን፡፡

ሆኖም ይህ በረድኤተ እግዚአብሔር፣ ጸጋና በረከት መታገዝ አለበት፡፡ ወንድሜ ሆይ ከጻድቁ ከያዕቆብ ጋር "ካልባረከኝ አለቅህም" ዘፍ 32፤26 እያልክ ትግልህን ቀጥል፡፡ ዳግመኛም "በሂሶጵ እርጨኝ እነጻማለሁ አጠበኝ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ" መዝ 50፤7 ስትል ዘምር፡፡ በዚህ ፉጊያ ውስጥ የስጋህ ምኞትህን ድል ከነሳህ የሰይጣን ኃይል በአንተ ላይ ቢሰለጥንብህም እንደማትሸነፍ እርግጠኛ ሁን፡፡

ስለዚህ ውድ ወንድሜ ይህን ለማድረግ በእግዚአብሔር ህይወት ውስጥ አስፈላጊ የሆነውን የጽሞና ጊዜ ያስፈልግሃል፡፡ በጽሞና ጊዜ የእግዚአብሔር ሰዎች ከራሳቸውና ከፈጣሪያቸው ብቻ ጋር መቆየት ይችላሉ፡፡ ለመንፈሳዊ ህይወታቸው ደህንነትን ለስጋዊ ህይወታቸው ጤንነትን የሚያገኙበትን አዲሱን ትጥቅ





ይታጠቃሉ፡፡ ህይወትህን መርምር በጥንቃቄ እስከ የጽሞና ጊዜ መፈለግህ ምናልባት ለውድቀትህ እንዳይዳርግህ ተጠንቀቅ፡፡

የጽሞና የህይወት ልምድ የሌለው ሰው ማንነቱን አያውቅም ይህ ዓይነቱ ሰው በራሱ ሳይሆን በሰዎች አስተሳሰብና ልማድ ስለሚገዝ ምን እንደሚሰራና የት እንደሚሄድ አያውቅም ወደራሱ እስኪመለስና ራሱን እስከሚያውቅ ድረስ በውድቀቱ ይቀጥላል፡፡

አንተ ግን እንደዚህ ዓይነት ሰው አትሁን ነገር ግን አካሄድህን የምትመረምርበት ለራስህ የተወሰነ ጊዜ ይኑርህ፣ ከዚህ በፊት ያሳለፍካቸው የመንፈሳዊ ህይወት ልምድህን አስታውስ፡፡ ዳግመኛም የቅዱሳን አባቶችን ህይወት በማሰብ ለእግዚአብሔር ቃልን በቅዱሳን አባቶች ህይወት ታሪክና አባባል እንተነትህን ልታንጽ ትችላለህ፡፡

እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን ቅድስናውን ይስጥህ ኃጢያታችንን ይቅር ይበለን፡፡



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



# ደሙን ከእጅህ እፈልጋለሁ

ለኃጢአቴ እኔ ብቻ የምኮነን ይመስልሃል? አይምሰልህ አንተም ከእኔ ጋር ትኮነናለህ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ለእኔ ጥበቃን አድርጋ ቢሆን ኖሮ እንዲህ ዓይነት ውድቀት አይደርስብኝም ነበር።

የሲጋራውን ጢስ በፊቴ ላይ እያበነነ "ምናልባት አሁን ባለሁበት ሁኔታ እጅግ ትደነቅ ይሆናል" ሲል ንግግሩን ቀጠለ እኔም ደማቅ ሆኖ በረጅም የተሰራ ፀጉሩን የሰረጎዱ ዓይኖቹን የወየቡ ጥርሶቹንና በጭንቅ የሚንዘፈዘፉ እጆቹን ተመለከትኩ ይህ ሲሆን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ ካዋጃቸው መካከል አንዱ በመሆኑ እጅግ አዘንኩለት።

ምላሽ ከመስጠቴ በፊት ንግግሩን በምሬት ቀጠለ እንደምታውቀው ከዚህ በፊት እንዲህ አልነበርኩም መንፈስ ጠንካራ ጥሩ ስነ ምግባር፣ ነጋ ለኪዳን መሸ ለጸሎት ወደ ቤተ እግዚአብሔር እገሰግስ ነበር ከዚያም ቀስ በቀስ ቤተ ክርስቲያን መካፈል እስከቆም ድረስ በመንፈሳዊ ህይወቴ ተዳከምኩ ነገር ግን ከቤተ ክርስቲያን ምን ሆነ የት ደረሰ ሲለኝ ማንም አልመጣም ከቤተ ክርስቲያንም በእጅጉ እየራኩ መጣሁ መንፈሳዊነቴም ተሚጠጠ ደረጃ በደረጃም ከነበረኝ ቅድስና ማዕረጌ ዝቅ አልኩ። አሁንም ቢሆን በዚህ ውድቀቴ ጊዜ አስታዋሽ አልነበረኝም። ጸላየ ሰናያት ወደ እኔም በቀረበ ጊዜ ልቦናዬ ከእግዚአብሔር ጸጋ እንደተራቆተ ተመለከተ ድክመቴንም አጠናው በውስጤም የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሌለ ህይወቴም በጸሎት እንዳልተደገፈ





መንፈሳዊ አባቶችም ከአጠገቤ እንደሌሉ ተመለከተ ስለዚህ ባጠመደው ወጥመድ ውስጥ ወደኩ ለእርሱም ሚች ሆንኩ በጨለማም መጓዝ ጀመርኩ ሰዎች ከብርሃን ይልቅ የመረጡት እጅግ ድቅድቅ ጨለማ ዮሐ 3፤19 ራሱን በዝግታ እየወዘወዘ እንዲህ አለኝ በቀን 4 ፓኬት ሲጋራ አጨሳለሁ።

በመገረም ጮኾ ሁኔታውም ሰቀጠጠኝ በሳምንት ሦስት ጊዜ ወደ ሲኒማ ቤት እሄዳለሁ አጸያፊ የሆኑ ታሪኮችን አነባለሁ በሙዚቃ ራሴን አስደስታለሁ ወደ ሲኦል እንደተጣሉት እንደ ዲያቢሎስ ሠራዊት በኃጢአት የሚጋሩኝ ጓደኞቼ ብዙ ናቸው። "ለመውደቅ በምዳዳበት ጊዜ ለመቋቋም እሞክር ነበር ነገር ግን መንፈሴ ደካማ ስለነበረ መቋቋም አልቻልኩም" ሲል ተናገረ። በመቀጠልም የምጸት ሳቅ እየሳቀ እንዲህ አለኝ አሁን ግን ኃጢአት እየተቆጣጠረኝ ነው ብሎ ይሻለኛል።

በዚህ ጊዜ እጅግ አዘንኩ ነገር ግን እርሱ በጭካኔና በደም ፍላት እያየኝ እንዲህ አለኝ "በኃጢያት እኔ ብቻ የምኮነን ይመስልሃል" አይምሰልህ አንተም ከእኔ ጋር ትኮነናለህ ቤተ ክርስቲያን ጥበቃ አድርጋልኝ ቢሆን ኖሮ እንዲህ ዓይነት ውድቀት አይደርስብኝም ነበር።

ውድ አንባብያን የዚህን የወጣት ታሪክ ማውራቱ አስፈላጊ አይደለም ብዙ ይህን መሳይ ታሪኮችን ማውራት ስለሚቻል። ነገር ግን ከዚህች ቁጽንት ጀምሮ በእኔ ማንነትና በእርሱ ሁኔታ እጅግ አያዘንኩ ወደ ቤቴ እንደተመለስኩ ልነግርህ እወዳለሁ። ራሴንም በዝግታ መጠየቅ ጀመርኩ። በእኔ ቸልተኛ ነትና ንዝህላልነት ስለ እነርሱ ጥንቃቄ ባለማድረግ ስንት ሰው



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ለውድቀት ዳርጌኋለሁ ለብዙ ጊዜ ያላየኋቸውን ሰዎች ማሰላሰል ጀመርኩ እጅግ ፍርሃትና ጭንቀት ተሰማኝ ህይወታቸውም በቀላሉ እንዳማይታይ ተሰማኝ ምናልባት በአገልግሎት መጠመድ ብዙዎችን እንዳላገለግል አድርጎኝ ይሆን ስል ራሴን ጠየኩ "አንተም ከእኔ ጋር ትኮነናለህ ሲል የወጣቱ ድምጽ በጆሮዬ አ ቃጨለ የሐዋሪያውን የያዕቆብን ቃል አስታውሳለሁ ወንድሞቼ ሆይ ከእናንተ ብዙዎቹ አስተማሪ አይሁኑ የባሰውን ፍርድ እንድንቀበል ታውቃላችሁና፡፡ ሁላችን በብዙ ነገር እንሰነካከላለን ያዕ 3፤1

በዚህ መረበሽ ጥቂት እንደቆየሁ አገልግሎቴን ለማቆም ጥያቄ አቀረብኩ ነገር ግን እንደከለከሉኝ ባየሁ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ለኃጢአቴ ስርየት ሱባኤ ገባሁ ምክንያቲም ምን ያህል ቸልተኛ እንደሆንኩ ተረድቻለሁና፡፡

አገልጋይ ለመሆን በመመኘቴ ደፋር ነኝ እንደ ነብዩ ኤርምያስ "እነሆ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አለውቅም ኤር 1፤6 አላልኩም አሁንም እጅግ ደፋር ነኝ በሰንበት ት/ቤት ውስጥ በማስተምርበት ጊዜ ትምህር ታዊ ገለጻ እንጂ በፍቅር የታጀበ አልነበረም፡፡

ውድ አንባቢያን ፀሎታችሁ በእኔና በአገልግሎት ላይ ላሉት ሁሉ ይሁን፡፡ ምክንያቱም እጅግ ቸልተኞንንና፡፡ እነሱም ልክ እንደኔው ደፋርና ምስኪን ናቸውና፡፡

ውድ ውንድሜ ይህችን ትንሽ ማዕረግ ይዤ ስቃይ እየተሰማኝ ስለ ካህናት አባቶች ምን እልለሁ እነሱ ከእኛ የባሱ ጨካኞች ነበሩ? አንድ ካህን ለ5ወይም ለ10 ሽህ ለሚሆን ልጆች ምን





ማድግ ይችላል እግዘአብሔር "የመጋቢነቱን ሒሳብ አስረክበኝ" ሉቃ 16-2 ብሎ ሲጠራው ካህኑ ምን ዓይነት ምላሽ ሊመልስ ይችላል፡፡

እናም እርስዎ አባቴ የክህነት አገልግሎት እንዲሹ ያደረገዎ ምንድ ነው ታላቅነትንና የበላይነትን ፈልገው ነበር ለመንጋው ሁሉ ተጠያቂ እንደሆኑ ያውቃሉ ኃላፊነቱም በኃጢያት ለረከሱ በጥፋት ጎዳና ለወደቁ ለጠጪዎችና ለበደለኞች ጭምር እንጂ ቤተክርስቲያን ለሚከተታሉ ብቻና ለባለደጎች አይደለም፡፡

አዎን አባቴ ይህን ነገር ካልተረዱ አዎን ጨካኝ ኖት አሁን ሊያሲቡበት ይገባል፤ ወደቤቶ ይግቡና ስለኃጢያቶ በምሬት ያልቅሱ፡፡ ሁኔታዎችን ሁሉ ለእግዚአብሔር አሳልፈው ይስጡ፡፡ ደካማ እንደሆኑና ቀንበሩ የከበደዎ መሆኑን ይንገሩት ሃይማኖትና ምግባርን ይዘው ይጠብቁ "ድንገት መጥቶ ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ" ማር13-36

ይህ የቀሳውስትና የካህናት አገልግሎት እንዲህ ከሆነ፤ እግዚአብሔር ስለብዙ ሕዝቡ ስለካህናቱም ህይወት ሳይቀር ስለሚጠይቃቸው ጳጳሳት ምን ማለት እንችላለን? በጣም ቸልተኞች አይደሉምን? እግዚአብሔር ስራቸውን እንዲያከናውኑ ይረዳቸው ዘንድ ፀልይላቸው፡፡ እናንተ ጳጳሳት ይህን ስልጣን እንድትመኙ ምን አነሳሳችሁ? ወይስ ነፍሳትን ከኃጢያት ለመንጻት በመመኘት ነው?፡

ብፁዕነቶ ለተጨማሪ ስላሉበት ኃላፊነት አንድ ነገር ልጠይቆ አሁን ካሉበት ሁኔታ ሀገረ ስብከቱ አስቀድሞ ከነበረው ሁኔታ ጋር ሲያነጻጽሩት ምን ዓይነት ለውጥ አለው? እስካሁን ያው ባለበት ያለምንም ለውጥ ነው? እንዲህ ከሆነ ብፁዕነቶ ወደ በአቶ ይግቡና እርሶም በምሬት ያልቅሱ፡፡ ብዙ ንፁሐን መነኮሳት ከማዕረጉ ከፍተኛ ተጠያቂነት የተነሳ ከዚህ ማዕረግ በግዳጅ በተቀበሉም ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት እያለቀሱ እንዲህ ይሉ ነበር "ጌታ ሆይ አለምን ንቄ የራሴን ድህነት ፈልጌ ወደ ገዳም እንዳሄድኩ ታውቃለህ፤ ይሁን እንጂ ደኅንነቴን ሳላረጋግጥ ወደ አለም ተመልሼ ሌሎችን ለማዳን እንደተጠየኩ ተውቃለህ፡፡ ጌታ ሆይ ችሎታውና ብቃቱ የለኝም፡፡ አንተስ በኃይልህ ሁሉን አከናውን ይሉ ነበር እግዚአብሔር እንደ ቃላቸው ያደርግላቸውም ነበር፡፡



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ስለጳጳሳት ይህን ካልን ስለ ሊቃነጳጳሳቱ አባቶችስ ምን እንላለን? እነሱ ደግሞ ስለ ዓለም ሁሉ የሚጠየቁ ናቸው። እነሱም እንዲሁ ቸልተኞች አይደሉምን? ውድ ወንድሜ እነሱ ግን ለእያንዳንዱ ሊቃነ ጳጳሳት (ፓትሪያርክ) ስራቸውን በአግባቡ እንዲፈፅሙ እግዚአብሔርም ስለ አለም ነፍሳትና ስለራሳቸው ነፍስ በጠየቃቸው ጊዜ መልካም መልስ እንዲመልሱላቸው የቤተክርስቲያንን ህግጋት እንዲጠብቁ እንዲያደርጋቸውና ኃይማኖቻቸውን በዓለም ዙሪያ እንዲያስፋፉ እንዲረዳቸው ልትጸልዩላቸው ይገባል።

አንተም አንድ ቀን ለዚህ ማዕረግ ልትታጭ ትችላለህ ነገር ግን እምቢ ልትል ያስፈልጋል። ለህይወትህ ስትል ራቅ ነገር ግን ጥሪው ከእግዚአብሔር ከሆነ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ፊት አልቅስ።

ውድ አንባቢ አንተ ግን እነዚህን ኃላፊነት ያለባቸውን ሰዎች መልካም በሰሩ ጊዜ ምስጋናን የሚሹና ባጠፉ ጊዜ የሚከሰሱበትን ካህናትን አትመልከት። የእግዚአብሔርን ስራ በእነሱ ውስጥ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ይጸለይላቸው።

እናንተም የእግዚአብሔር አገልጋዮች ኃላፊነቱን እንደ ስልጣ ን የምታሰቡ አትሁኑ ቀንበሩ የከበደ መስሎ ከተሰማችሁ "ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል እርሱም ይደግፍሃል" መዝ 55-22





# የአገልግሎት ህይወት

እነዚያ ህይወታቸውን በሙሉ ለእግዚአብሔር የሰጡ ሰዎች ለአገልግሎት ጊዜአቸውን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር አሳለፉ። መንፈሣዊ አገልግሎታቸውን ተቀዳሚ ሥራ አደረጉና የዚህን ዓለም ጉዳይ እንደ ሁለተኛ ቆጠሩ።

እንዲህ በሆነ ጊዜ በጸሎት ቤቴ ብቻዬን እግሮቼን ዘርግቼ ወደ ላይ አንጋጥጬ ሳለ በዚያች ምሽት አንድ ክስተት ተፈጠረ... ይህም እጅግ እንግዳ ነበር። ራሴን አጨናንቄ ይሆን፣ ወይስ ወደ ምናብ ዓለም ውስጥ ገብቼ በቅዠት ባህር ውስጥ እየዋኘሁ ይሆን፣ አልያም እግዚአብሔር ራዕይ ገልጾልኝ ይሆን... ብቻ አላውቅም። የማውቀው በፊቴ የብርሃን መላእክት ማህበር በክንፋቸው ተሸክመው ወደ ላይ ሲነጥቁኝ ብቻ ነው።

ከበታቼ ያለችውን ምድር ስመለከት ቀስ በቀስ ክበቧ እየጠበበ እያነሰ ከዐይኔ ተሰወረች። ዳግኛም የዓለም ሀብት እየቀነሰ መጣና ፍፁም ዝምታ ሆነ። ያለምንም ውሱን አካል መንፈስ የሆንኩ ያህል እስኪሰማኝ ድረስ ሰውነቴበብርሃን ተሞላ። ዙሪያዬን ግራ የሚያጋቡ ነገሮች ተመለከትኩ፤ ብዙ መናፍስት ልክ እንደእኔ አንዳች ነገር ሳይገድባቸው ከአጽናፍእስከ አጽናፍ፤ እልፍ አእላፍ መላእክት፣ ክንፋቸው ስድስት (፮) የሚሆኑ ኪሩቤል፣ ዓይኖቻቸው ብዙኀን የሚሆኑ ሱራፌልንም ተመለከትኩ። በሚያስገርም ሕብረት ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ይላሉ። ባለማወቅ እኔም ከእነሱ ጋር አሐዱ አብ ቅዱስ፣ አሐዱ ወልድ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ቅዱስ፣ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ በማለት አመሰገንኩ።

ከዚህ በፊት ጆሮ ሰምቶት የማያውቀውን ነፍስን የሚመስጥ ዜማ በሰማሁ ጊዜ ዝማሬዬን አቋረጥኩ። ወደ ድምፁ ምንጭ እዚያም ምን እንዳለ ለማወቅ በመጓጓት ሄድኩ። ከእኔ በቅርብ ርቀት ከሠማያት ጋር የተያያዘች ልብን የሚመስጥ ዝማሬን የምታስተጋባዋን ብርሃናዊዋን ከተማ አገኘኋት። የዝማሬው ቅላፄ ልቤን በሀሴት፣ ነፍሴንም በናፍቆት መሏት። ከዚች ከተማ ትንሽ ከፍ ብሎ ከመላእክት ማህበር ይልቅ አምረው የሚታዩ ማህበራት ይታያሉ። ከዚያም እነ ሙሴ፣ እነ ኤልያስ ሌሎችም ነቢያት፣ ቅዱሳን፣ ጳጳሳት፣ ካህናት፣ የንሰሀ አባቴም፣ የሥራ ባልደረቦቼም ነበሩ ነገር ግን ከዚህ በላይ ማየት አልቻልኩም ወዲያው ቀድሞ ወደነበርኩበት ወደ መላእክቱ ማህበር አዘቀዘኩ

በእኔ መገረም ቀጥዬ መራመድ አልቻልኩም ምክንያቱም በዚያ ቁም! ወዴትስ ነው የምትሄደው እያለ የሚያስጠነቅቀኝ ብርሃናዊ መልአክ በመንገዴ ነበር። እኔም የእኔ ጌታ ወደዚያች ትልቅ ከተማ የሥራ ባልደረቦቼን ቀ.ወንድሞቼንና አባቶቼን ወደማይበት ነው አልኩት።

ነገር ግን መልአኩ በአድናቆት እየተመለከተኝ "በእርግጥ ይህ የአገልጋዮች መንደር ነው፤ አንተ ከእነሱ አንዱ ነህ?"አለኝ





ትክክል እንደሆነ ስመልስለት "ተሳስተሃል ወንድሜ ስምህ ከእነሱ ጋር በአንድ መዝገብ አልሰፈረም" አለኝ።

በድንገት በመገረም ከተማዋን በሚጠብቀው መልአክ ፊት ጮህኩ፤ እንዴት ይሆናል? ምናልባት እኔን አታውቀኝም ይሆናል? ስለ እኔ በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ፣ በቤተክርስቲያን ጉባዔያት ጠይቅ ። ብዙዎች የሥራ ባልደረቦቼ ሁሉ በደንብ ያውቁኛል። ስል ጠየቅኩት።

በደንብ አውቅሃለሁ፤ እነሱም በደንብ ያውቁሃል። ሆኖም በእግዚአብሔር ፍትህ አንተ አገልጋይ አይደለህም። ሲል መለሰልኝ።

እነዚህን ቃላት ለመስማት ትዕግስት አልነበረኝም። በጉልበቴም ተንበርክኬ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ። ሌላኛው መልአክ በመጣ ጊዜ እንባዬን እያበሰ በጽሞና "ወንድሜ አንተ ከሚያሳዝን ቦታ የመጣህ ነህ? አለኝ። ታዲያ ለምን ታዝናለህ? ና እስኪ ብቻችንን እንወያይ።" ከዚያም በጽሞና ተወያየን። እነዚያ በዚያች ብርሃናዊ ከተማ ውስጥ ያየሃቸው አገልጋዮች ህይወታቸውን ሁሉ ለእግዚአብሔር አስገዝተው ጊዜያቸውን ሁሉ በአገልግሎት አሳለፉ። አለኝ። አንተስ የሐዋርያቱን የካህናቱንና የቅዱሳኑን ህይወት ኖረህ ነበር? ወንድሜ አንተ ግን አለምን አገለገልክ እንጂ ለአገልግሎትህ ልክ እንደነሱ ቀናኢ አልነበርክም። መንፈሣዊ አገልግሎትህ በሳምንት አንድ ቀን የተገደበና በሰዓት የተወሰነ ነበር። በዚህች ዕለትና ሰዓት በምትሰጠው አገልግሎት ብቻ ከሐዋርያቱ፣ ከነቢያቱና ከካህናቱ ጋር መሆንን ትፈልጋለህ?



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



በዚህ ንግግራችን ውስጥ ራሴን በእፍረት አዘቀዘኩ ነገር ግን እፍረቴን ለማስወገድ እየሞከርኩ መላኩን ለመጠየቅ ፈለኩ::

ነገር ግን በዚህች ከተማ ውስጥ በሰንበት ትምህርት ቤት ልክ እንደ እኔው ይሰሩ የነበሩት የሥራ ባልደረቦቼን ተመለከትኩ አልኩት::

እነሱ እንደ አንተ አይደሉም:: እነሱ በሳምንት አንድ ቀን ለአንድ ሰዓት ልክ እንደ አንተ ቢያገለግሉም እንኳን ይህችን ዕለትና ሰዓት ለማገልገል ሳምንቱን ሙሉ በዝግጅት ላይ ነበሩ:: ብዙ ጊዜያቸውን ሥርዓተ ትምህርት በማቀናበር፣ ሥዕላዊ መግለጫዎችን በማዘጋጀት፣ ሰዎቹም ትምህርቱን በጉጉትና በናፍቆት እንዲጠባበቁት ለማድረግ የተለያዩ መንገዶችን ይቀይሱ ነበር::

ከዚህ በተጨማሪም በጸሎት ብዙ ጊዜ ይተጉ ነበር:: ዳግመኛ የእያንዳንዱን ተማሪ ግንዘቤ በመጠየቅ ብዙ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር:: የእያንዳንዱንም ተማሪ ህይወት ለማደስ የተሻለ ዘዴ ይቀይሱ ነበር:: ከዚህ በተጨማሪ አንተ የማታውቀው ብዙ ለተማሪዎቻቸው የሚያደርጉት ጥንቃቄ ነበራቸው:: መንፈሣዊ አገልግሎታቸውን ተቀዳሚ አገልግሎት አድርገው የአለምን ነገር ደግሞ እንደ ሁለተኛ ተመልክተዋል:: ይህም ኃላፊነታቸውንና የአለም ተግባራቸውን ችላ ብለዋል ማለት አይደለም:: በአለም ሥራቸው ሳይቀር ታማኝና ታታሪ ነበሩ:: ይህ የአለም የሥራ መስክ ራሱን የቻለ የአገልግሎት ሥፍራ ነው:: ስለዚህም እግዚአብሔር ይህን ሥራ ፍሬማ አደረገላቸው::





በእነዚህ ቃላት ተደንቄ "ታዲያ በአለም ሥራ ባተሌ ሆኜ እንዴት አገልጋይ መሆን እችላለሁ?" ብዬ ጠየቅኩት::

መልአኩም ወንድሜ ምናልባት የአገልግሎቱን አብዛኛውን ድርሻ ዘንግተኸዋል:: በቤተክርስትያን አካባቢም ቢሆን፣ በምትሔድበት በምትቀመጥበት ሰዓትና ቦታ ልታገለግለው ይገባሃል

በአንድ ሰው አገልግሎትና አገልጋይነት መሀከል አንዳች ልዩነት ሊኖር አይገባም:: በዚያች በአገልጋዮች ከተማ መንፈሣዊ ተማሪዎቻቸውን በህይወታቸው ማርከው፣ ህይወታቸውን የሚያሻሽሉና ዘላቂ እንክብካቤ የሚያደርጉ መምህራን አሉን:: ዳግመኛም ለጥቅማቸው ሳይሆን በመጀመሪያ ለበሽተኞቻቸው ደኅንነት የሚጨነቁ፣ ብዙ ጊዜ ለበሽተኞቻቸው ህክምና የሚሰጡ ሐኪሞች አሉን:: እነዚህም ሐኪሞች በሽተኞቻቸውን በነፃ ያክማሉ:: በራሳቸው ወጪና ጉልበት ሳይቀር የህክምና ጣቢዎችን ያቋቁማሉ::

የሥራ ባልደረቦቻቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄዱና ሥጋና ደሙን እንዲቀበሉ የሚያበረታቱ ሠራተኞች አሉን:: በአለም ሥራቸው ውስጥ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ መሀንዲሶች፣ ህግ አዋቂዎች፣ ነጋዴዎችና ገበሬዎች አሉ:: አንተስ እንደ እነሱ ነበርክ?

እፍረት ስለተሰማኝ አንዳች ምላሽ አልነበረኝም ይሁን እንጂ መልአኩ ያለ ማቋረጥ ደግሞ ደጋግሞ ወቀሳውን ቀጠለ::



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



በሥራህ መስክህ ውስጥ ይህ አገልግሎትህን ይመለከት ነበር:: ቤተሰብህን እንዴት ታገለግላቸዋለህ በዚህች ብርሃናዊ ከተማ የተመለከትከው ኢያሱ "እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን " ኢያ 24:5:: ይላል:: አንተስ? ቤተሰብህን በማገልገል ፈንታ ከራስህ ጋር ትሟገታለህ:: ይከተሉህ ዘንድ አርአያ አልሆንካቸውም: ለወዳጆችህ፣ ለጓደኞችህና በአካባቢህ ስለሚገኙ ማህበረሰብ ምን አድርገህ ታውቃለህ? በየዓመታዊና ወርኀዊ በዓላት በመሄድ ትጎበኛቸው ነበር፤ ነገር ግን ስለ እለቱ ክብረ በዓል እንኳን አውስተህላቸው አታውቅም:: በሌላ አገላለጽ ስለዚህ ዓለም ጣጣ ስለ ዕድር፣ ስለ ዕቁብ፣ ስለ ማኅበር... ስለመሳሰሉት ታወራቸዋለህ:: እነሱን እንድታገለግል ከእግዚአብሔር የተሰጠህን አጋጣሚ በከንቱ ታባክናለህ:: ታዲያ በእንዲህ ያለ ሁኔታ ውስጥ ሆነህ ራስህን እንደ አገልጋይ ትቆጥራለህ?

ደግም ለሦስተኛ ጊዜ ራሴን አቀረቀርኩ፤ ነገር ግን መልስ ለመስጠት እየሞከርኩ "ጌታዬ ስጦታዬ ትንሽ እንደሆነ ታውቃለህ፤ በእኔ ዘንድ እኚህን ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ አቅሙ የለኝም::" ብዬ መለስኩለት::

መልአኩም ይህን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማ ያህል እስኪመስለው ድረስ በመደነቅና በመገረም እንዲህ አለኝ:-

ስጦታ! ያለ ተሰጥኦ ማገልገል እንደማትችል ማን ነገረህ? ውድ ወንድሜ ሰውን በስብከት ለማገልገል የግድ ልብሰ ተክህኖ ተለብሶ መድረክ ላይ በመቆም ብቻ አይደለም፤ ትልቁና ዋነኛው ሰውን በራሱ ህይወት መለወጥ ነው:: ስለዚህ በህይወትህ





ለብዙዎች አብነት እንድትሆን እንጂ የግድ ስብከት አዘጋጅተህ መድረክ ላይ መቆም ብቻ አይጠበቅብህም:: እንዲህ ዓይነት ሰው ከሆንክ ሰዎች ፊትህን ባዩት ጊዜ የዋህነትን፣ ሩህሩህነትን ይማራሉ፤ ንግግርህን በሰሙ ጊዜ መንፈስ ጠንካራነት ፤ ታማኝነትን ፤ ፍፁምነትንና ፍቅርን ያገኛሉ:: ደግሞ ትምህርት አዘጋጅተህ በአውደ ምህረት ላይ ቆመህ ስትሰብክ ሲያዩህ ሰውነትህን እስኪጠራጠሩት ድረስ ያደንቁሃል፤ በሥራህም አብነት ትሆናቸዋለህ እጅግም ይወዱሃል:: ነገር ግን ከዚህ ሁሉ በጸለይክላቸውና ጸሎትህም ከትምህርትህ ይልቅ በጠቀማቸው ነበር::

ለአራተኛ ጊዜ እፍረት ተሰማኝ፤ ግራም ተጋባሁ:: መልስም ለመስጠት አቅሙ አነሰኝ:: መልአኩ ግን ንግግሩን ቀጠለ::

በህይወት ስብከትህ እነዚህን ነገሮች ማስወገድ ነበረብህ:: ከእንዲህ ዓይነቱ ከንቱ ጸባይ ተቆጠብ፤ ይህ ባህሪህ መልካም መስሎ ቢታይህም ብዙዎችን ለውድቀት ዳርጓልና ልታስወግደው ይገባህ ነበረ:: ስለዚህ ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚለን በእግዚአብሔርና በሰዎች ዘንድ ተወቃሽ አትሁን:: የሐዋርያውን የቅዱሰ ጳውሎስን "ሁሉ ተፈቅዶልኛል ሁሉ ግን አይጠቅምም" 1ኛ ቆሮ 6÷12 የሚለውን ቃል አስብ ::

በህይወቴ ላይ ሐዘን ገባኝ:: ለካ ብዙዎችን ሳላውቅ ወደ ኃጢአት መርቻቸዋለሁ:: መልአኩም ትካዜዬን (ቁዘማዬን) በማቋረጥ በለሰለሰ አነጋገር እንዲህ አለኝ::



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ውድ ወንድሜ ሌላም ተጨማሪ ነገር ልነግርህ እወዳለሁ በአለም በነበርኩበት ጊዜ፤ በተለይም ስትመጻደቅና በራስህ ስትመካ ባየሁ ጊዜ እጅግ አዘንኩልህ:: የአገልግሎትህን ይዘትና ስፋት ባየህ ጊዜ አገልጋይ የሆንክ ያህል እየተሰማህ አገልጋይ ነኝ አልክ:: ምናልባት ብዙ የሰራኃቸው ጥፋቶችን ልታስታውስ ትችላህ::

ለምሳሌ አንተ መደበኛ አገልጋይ ነህ:: በሳምንቱ ልምድህ መረሐ ግብሩን በጸሎት ለመጀመር፣ የተማሪዎችህን መገኘት ለማረጋገጥ፣ ያለማቋረጥ በመደበኛነት የተገኙትን ፅማበረታቻ ሽልማት ለመስጠት፣ የቀረውንም በዚያው ልክ በአንተ ትዕዛዝ ካልተጓዘና መመሪያህን የማይቀበል ከመሰለህ ችላ ትለዋለህ:: ስለዚህ አገልግሎትህ በፍቅርና በመንፈሣዊነት የተሞላ አልነበረም:: አገልግሎትህም የተማሪዎችህን ልብ ሊመስጥ አልቻለም:: የቃልህ አጣጣልና ተግባርህ ከተሰበረ ልብ የመነጨ አልነበረም:: በቤተ ክርስቲያን በምትሰብክበት ጊዜ እንኳን በዕለት ተረኛነት ስለተገደድክ ብቻ ለማስተማር ቃል ትገባለህ፤ ቃልህንም ለመፈፀም ስትል ትሰብካለህ:: አገልግሎትህም ብዙ ነፍሳትን ለድኅነት ከማዘጋጀት ይልቅ አድናቆት ለማግኘት ነበር:: ድምጽህ ማራኪ፣ ግርማ ሞገስ ያለውና ግልጽ ቢሆንም የዐ.ነገር ቅንብረ እንጂ በውስጡ ህይወት አልነበረም::

በአገልግሎትህ ስኬታማ ሳትሆን ሰዎች በሚያወድሱህ ጊዜ እንደ ጥሩ አገልጋይ ልብህ ሐሴትን ታደርጋለች:: ነገር ግን ትምህርትህ የሰዎችን ህይወት ይለውጥ አይለውጥ ግድ የለህም::





ውድ ወንድሜ እግርዚአብሔርንና ህዝቡን ከማገልገል ይልቅ ራስህን እንዴት እንደምታገለግል ታያለህ? ብዙ ነፍሳት ከሚድኑባት ነገር ግን ጥቂት ህዝብ ከሚኖርባት ከገጠሪቱ ቤ ተክርስቲያን ይልቅ በብዙ ህዝብ በተጨናነቀችና ታዋቂነትን ባተረፈች ቤተክርስያን ዘንድ ሄደህ ማገልገል እጅግ ደስ ያሰኝሃል! ይህም አገልግሎትህን የሚቃወም ሌላኛው ማስረጃ አይደለምን?

ያም ሆነ ይህ አገልግትህ ሁለት ነገር ይጎድለዋል:: እነርሱም:-

አገልግቱን መውደድና የምታገለግለውን ህዝብ መውደድ ይቀረዋል::

<u>አገልግሎቱን ስለመውደድ:-</u> "ስለ ጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው" ማቴ 5÷6 ሲል ጌታ ተናገረው ቃል አገልግሎትን ስለመውደድ ማስረጃ ነው:: ስለ ብዙ ነፍሳት ድኅነት ተጠምተህ ወይስ ተርበህ ታውቃለህ? ከተማሪዎችህ ጋር ስለምታሳልፈው ሳምንታዊ ጉባኤ ዕለት ዕለት አስበኸው ታውቃለህ? ከጉባኤው ለቀረው ሰው አዝነህለት ታውቃለህ? እስክታገኘው ድረስ ትናፍቃለህ? ካገኘኸው በኋላስ በዕለቱ ያመለጠውን ትምህርት ለብቻ እንደገና ታስረዳዋለህ?

<u>ሌላኛውና ሁለተኛው የምታገለግለውን ህዝብ መውደድ እንደሆነ ተነጋግረናል::</u> በእርግጥ ትወዳቸዋለህ፤ ነገር ግን ልክ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን እስከመጨረሻይቱ ሰዓት ድረስ እንደወደዳቸው በውኑ አንተም እነርሱን ትወዳቸዋለህ? ብዙ ርኅራሄና ትህትና ታሳያቸዋለህ? ተማሪዎችህስ እንዲሁ አንተን ይወዱሃል?:: ወይስ ሽልማት ባለመስጠት ትገስጻቸውና ትቆጣቸው ነበረ? ኧረ ለመሆኑ የዚህ ዓይነቱ የአገልግሎትህ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ተግባር ተማሪዎችህን እንደሚያሻሽላቸው ማን ነገረህ፡ ውድ ወንድሜ ፍቅር በአገልግሎትህ ውስጥ የአገልግሎትህ መነሻና መድረሻ ነው። የምታገለግላቸውን ካልወደድክ በቀር ልታገለግላቸው አትችልም፤ እነሱም የማይወዱህ ከሆነ ሊጠቀሙብህ አይችሉም።

በዚህ ጊዜ እኔነቴ ተገለጸልኝ። በጣምም አፈርኩ፤ መልአኩ ግን በፍቅርና በርኅራሄ እየተመለከተኝ እንዲህ አለኝ፡-

"አሁን ጠቃሚ የሆነ ስለ አገልግሎት ቅድመ ሁኔታ ልነግርህ እወዳለሁ። ከዚህ በፊት ለአገልግሎትህ ቅድመ ሁኔታና በቂ መንፈሣዊ ልምምድ ሳይኖርህ በብዙ ስህተት ውስጥ ወድቀሃል። አሁን ግን ጠቃሚ የሆነ ለአገልግሎትህ ቅድመ ሁኔታ አድርግ።

የራሴን ስህተት ሳላውቅ የሌሎችን ስህተት ሳርም መኖሬን ሳስብ ራሴን ከባድ ውድቀት ላይ አገኘሁት። በዚህም ውስጤን እየጠየኩት መልአኩም በመገረም ተመለከትኩት። መልአኩም አስተያየቴን በመመልከት እንዲህ አለኝ፡-

ባለመታዘዙና መመሪየዎችህን ባለመከተሉ ከክፍልህ ያስወገድከው ልጅ ነበረ። ነገር ግን ይህ አድራጎትህ ይህን ልጅ እልህ እንዲይዘው፣ ወደ አለም እንዲገፈተርና መጥፎ ልማድን እንዲቆራኝ አደረገው። ስለዚህም ይህ ልጅ እጅግ የባሰበት ሆነ፤ በአንተም ምክንያት ብዙ መከራዎች ደረሱበት። በተለይም እንዳልፈለከው እንዳልተከታተልከው ባየጊዜው እጅግ እየከፋ ሄደ ብዙም መከራ ደረሰበት።





እኔም እንዲህ ስል መለስኩለት፡- በትምህርት ሰዓት እጅግ ይረብሸኝ ነበረ፤ ለተማሪዎቹም መጥፎ አርአያ ነበር።መልአኩም ዳግመኛ ምላሽ ሰጠኝ፡- ስለዚህ በዚህ ምክንያት ከጉባኤው አስወገድከው? አ! ደካማ ነህ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርትህ ኃጥአንን ለንስሐ እንድታበቃ ላከህ እንጂ ጻድቃንማ በሥራቸው ይድናሉ። እነዚህ በትምህርታቸው ውጤት የሚያስደስቱህና በተግባራቸው የተመሰገኑ የምትላቸው ተማሪዎችህ እንዲህ ያደረጋቸውና የባረካቸው እግዚአብሔር እንጂ አንተ አይደለህም። እግዚአብሐርም በእነርሱ ውስጥ ይሰራል። ነገር ግን ይህ ትምህርቴን ይረብሸኛል ብለህ ከእግዚአብሔር ቤት ያስወገድከው ተማሪህ አንተ ከሌሎቹ በተለየ ልዩ ጥበቃ ልታደርግለት ይገባ ነበር። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእንዲህ ዓይነቱ አገልግሎት ጠርቷሃልና። የአገልግሎትህን ድርሻ በግልጽ እነግርሀ ለሁሉ ከሌሎቹ ይልቅ ጊዜህን ሁሉ መስዋዕት አድርገህ ይህን ልጅ መመለስ ከአንተ ይጠበቅ ነበር። እንዲህ ዓይነቱ ጥረት ብቻ ከእነዚህ አገልጋዮች ጋር በዚህች ብርሃናዊ ከተማ በደመረህ ነበር። ለዚህች ነፍስ መዳን ብዙ መከራና ችግር ማየት እንዳለብህ ልታውቅ ይገባሃል።

በአጠቃላይ አንድ በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ በአገልግሎት ላይ ያለ ሰው እስካሁን የተነጋገርንባቸውን እነዚህ ሁለት መስፈርቶች ሊኖሩት የግድ ነው። አለበለዚያ አገልጋይ ሊሆን አይችልም። አለኝ።

መልአኩንም በልምምጥ አነጋገር ታዲያ ለዚህ ልጅ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ምን ትላለህ? አልኩት። እርሱም መለሰልኝ።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



አቅምህ በፈቀደ መጠን እንደ እሱ ችግርና ሁኔታ ከእርሱ ጋር ልትወያይና ልትመረምረው በተገባህ ነበር። ብዙ ልትከታተለው ይገባሃል በተጨማሪም ዕለት ዕለት እግአዚአብሔር እንዲያስበው በጸሎትህ ልታስበው ይገባሃል። ነገር ግን ይህን ሁሉ አድርገህ የማይጠቀም ከሆነ ከትምህርቱ ማስወገድ ሳይሆን እርሱን ይመጥነዋል ወደምትለው ወደ ሌላኛው ክፍል ልታዘዋውረው ይገባህ ነበር። ምናልባትም ሌላው አገልጋይ የአንተ አቅም ያልፈቀደውን ሊፈጽምለት ይችል ነበር።

ይህ ሁሉ የማይጠቅመው ቢሆን እንኳን እንደየ ባህሪያቸው ልዩ ጥበቃ ለሚደረግላቸው ልጆች ሌላ ክፍል ማዘጋጀት ይገባህ ነበር። እነዚህ ልጆች በተደጋጋሚ ሊጎበኙ ይገባል፤ በመለየታቸው እንዳይቀጥሉ ከልብ የመነጨ ፍቅርና ርኅራኄ ሊያሳዩዋቸው ይገባል፤ እንጂ በማናቸውም መንገድ እነሱን ማስወገድ መፍትሄ አይሆንም። እነዚህ ተማሪዎችህ ቀራጭ ከነበረው ከዘኪዎስ፣ ከሳምራዊቷ ሴት ወይስ በኃጢያት ረክሰው በመጥፎ ከተማ ይኖሩ ከነበሩ ከነነዌ ሰዎች አሊያስ በሰዶም ገሞራ ይኖሩ ከነበሩት አመንዝራ ትውልድ የከፉ ነበሩ?። እግዚአብሔርን የሚያገለግል ሰው ተስፋ መቁረጥ አያውቀውም፤ በጸሎትም ጊዜ የትህትናና የፍቅር ልብ አላቸው።

ባለፈው ክፉ ተግባሬ እየተቆጨሁ ሳለሁ መልአኩ ንግግሩን ቀጠለ። ሌላ ከሳምንት በላይ የቀረ የክፍልህ ተማሪ አለ። አንተም እገሌ ወዬት ደረሰ ብለህ አልጎበኘኸውም፡፤ ልክ እንደ ቢሮ ሰራተኛ የቀሪ መዝገብ አዘጋጅተህ የመጣውን ስታጸድቅ





የቀረውን ስታገል ትታያለህ። ህፃኑም እንዳልጎበኘኸው ባየ ጊዜ ለመመለስ አልፈለገም። ስሙን በዚህ በቀሪ መዝገብ ላይ ስላሰፈርከው የድኅነት መንገዱን ዘጋህበት።

በዚህ ጊዜ መልአኩ በቁጣ አስተያየት እየተመለከተኝ፦ ለምን አልጎበኘኸውም! ሲል በታላቅ ድምጽ ጠየቀኝ ከፊቱ ገጽታና ከድምጹ ግርማ ሞገስ የተነሣ ብርክ ያዘኝ፤ ስለዚህ ከፍርሃቴ የተነሣ ጸጥታን መረጥኩ። ነገር ግን አሁን ደግሞ ደጋግሞ ለምን አልጎበኘኸውም? አለኝ። አውሎ ነፋስ ጭንቅላቴን የወዘወዘኝያህል ተሰማኝ። መልአኩም በቁጣና በኃይል ሲናገረኝ አንዳች አልመለስኩለትም።

መንፈሣዊው ሁኔታ በህዘኔታ ተቀሰቀሰ፤ በዚህ ከቀጠለ መጥፎ ነው። የመልአኩም ድምጽ ተንቀጠቀጠ፤ ከዚያም ዝግ እያለ እንዲህ አለኝ፦

እግዚአብሔር የጠፋውን ሰው ያድነው ዘንድ እኔና ሌሎች ብርሃናዊ መላእክትም እንጸልይለታለን። ይሁንና እግዚአብሔር ለጸሎታችን ምላሽ ከሰጠንና ወደ ሌላ ታማኝ ወደ ሆነ አገልጋይ ሰውዬውን ከላከው፤ ሰውዬውም ይድናል አንተም ከተከሳሽነት ትድናለህ።

ድምጹ የዛለችና የተጨነቀች ነበረች። መስማትም አልቻልኩም። ከዚያም በፊቴ የሚመላለሱትን እያንዳንዱን ነገሮች አሰብኳቸው፤ ከዚያም ራሴን ስቼ በፊቱ ወደኩ።

ወደ እራሴ በተመለስኩ ጊዜ መልአኩ በርህራሄ እየተመለከተኝ አገኘሁት። ይህም እኔ እንድናገር አበረታታኝ፤ እንዲህም አልኩት፦ ጌታዬ ይቅር በለኝ 30 የሚያህሉ ልጆች በእኔ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ክፍል ውስጥ ይማሩ ነበረ። እያንዳንዱን ለመጎብኘት አልቻልኩም ነበረ

ነገር ግን መልአኩ እንዲህ መለሰልኝ፤ ይህ ለአንተ ፈተና ነበር። የምታገለግላቸው የተማሪዎችህ ብዛት እኚህ ነበሩ። እግዚአብሔር ማንኛውንም አገልግሎት የሚለካው በሰዎች ብዛት አይደለም። በዳኑትና በተተኪዎች ጥራት ነው እንጂ። 30 ልጆችን ለመንከባከብ፣ ለመጎብኘትና ለማስተማር አስቸጋሪ እንደሚሆንብህ አውቃለሁ፤ ከዚህም አልፎ ስማቸውን በቃል ለመያዝ ትቸገራለህ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ "በጎቼን አውቃቸዋለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል" ዮሐ 10፥14። እንዳለው ማለት አትችልምና።

ለጥያቄው መልስ በማጣት ዝምታን መረጥኩ። ይሁን እንጂ ዋናው መንስኤ ምን እንደሆነ ታውቃለህ? በራስህ መመካትህ ነው። ስለአገልግሎትህ መጾምንና መጸለይ ረስተሃል። አሁን በአገልጋዮች ከተማ የተመለከትካቸው የሥራ ባልደረቦችህ ስለ አገልግሎታቸው በጾም የበረቱና በጸሎት የተጉ ነበሩ። ስለ እያንዳንዱ ልጆቻቸው ለመለመን ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት ያቀርቧቸው ነበር። ለአባቶች ካህናት ስመ ክርስትናቸውን በቅዳሴ ጸሎት ጊዜ እንዲያነሷቸው ያሳስባሉ። አንተስ እንዲህ አድርገህ ነበር።?

ይህ ሁሉ መንፈሣዊ አገልግሎትህን ይመለከት ነበር። አለማዊ አገልግሎትህ እንዴት ይሆን? አለማዊ አገልግሎትህን በቀጣይነት ተመልክተኸው ነበር። ነዌ ለደሃው ለአልዓዛር ባልራራለት ጊዜ እንዴት እንደጠፋ አታስታውስም? በተጨማሪም





ጌታ በግራ በኩል ለሚቆሙት "ተርቤ አላበላችሁኝም ተጠምቼም ነበር አላጠጣችሁኝም..." ማቴ 25፥42-43 ብሎ እንደሚወቅሳቸው አልሰማህምን? ስለዚህ ሁሉ ምን አደረክ? ወንድሞችህ በመከራና በመጥፎ ነገር ሳሉ አንተ ግን ተድላ ደስታ ፈልገህ ብዙዎችን ረስተህ ነበር።

ንግግሩን ከዚህ በላይ ልቋቋም አልቻልኩም። በሀዘን ጩኸት ጌታዬ እባክህ ታገሰኝ። አሁን በምንም አይነት ወደዚህች ከተማ ልገባ እንደማይገባኝ አረጋግጫለሁ። በራሴ ለብዙ ጊዜ እመካ ነበር። አሁን ግን ሁሉንም ካወኩ በኋላ እንደ እውነተኛና ታማኝ አገልጋይ ለመሆን ሌላ ዕድል ጠየኩ።

መልአኩም መለሰልኝ። የራስህ ዕድል ነበረኽ። ነገር ግን ይህን ባለመጠቀምህ ተጎዳህ። አሁንም በምድር ላይ የምትኖርበት ዘመንህ አልቋል።

እኔም በፊቱ ራሴን አዋረድኩ፣ ለመንኩት፣ አለቀስኩ ነገር ግን በርህራሄና በፍቅር ዐይን ተመለከተኝ፤ ከዚያም በዚህ እየጮኽኩ ሳለሁ ብቻዬን ትቶኝ ሄደ። ሌላ ዕድል እፈልጋለሁ! ሌላ ዕድል! ነገር ግን ከዐይኔ ተሰወረ። እኔም ሌላ ዐድል እፈልጋለሁ! በማለት ጩኸቴን ቀጠልኩ። ሰማይ ምድሩ ዞረብኝ ራሴንም ስቼ ወደኩ።

ወደ ራሴ ከመመለሴ በፊት ብዙ ሰዓታት አለፉ፤ ራሴንም ለማወቅ ዐይኖቼን ከፈትኩ በሚያስደንቅ ሁኔታ በክፍሌ ውስጥ ብቻዬን ተንጋልዬ ቁጭ ብዬ ነበር። ወዲያና ወዲህ አማተርኩ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ነገሮች ሁሉ ምትሀት መሰለውኝ ነበር ግን ሁሉም ነገር እውነት ነበር፡፡

እግዚአብሔር ሆይ ምህረትህ እጅግ የበዛና መዓትህ የራቀ መሐሪ አምላክ ነህ! በውኑ መልካም አገልጋይ ስመሆን ሌላ ዕድል አለኝ ማለት ነው! ልቤን አሰባስቤ ጥልቅ በሆነ የምስጋና ጸሎት ተነሣሁ ወደዚያች ከተማ ለመግባት የተገባቸው እንዲሆኑ ለጓደኞቼ ለመንገር ወሰንኩ፡፡ የማስታወሻ ደብተሬን ወሰድኩና በዚያች ሌሊት የሆነውን ሁሉ መጻፍ ጀመርኩ፡





# በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ ሀሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን፡ ፊል 2÷5

*እነሆ እያንዳንዳችሁ ወደ ቤት የምትበታተኑበት፣ እኔንም ለብቻዬ የምትተዉበት ሰዓት ይመጣል ዮሐ 16÷32*

<u>ለብቻው ቆመ</u>

ሰው ወዳድና ርኅሩህ የሆነው እሱ "መልካም እያደረገ ዞረ" የሐ.ሥራ 10÷38 ከአንዱ መንደር ወደ ሌላኛው፤ ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላኛው ከተማ ሄደ "... የመንግሥትም ወንጌል እየሰበከ በህዝቡም ያለውን ደዌና ህመም ሁል እየፈወሰ.. ይዞር ነበር" ማቴ 4÷23

ይሁንና ህይወቱን በሙሉ በመከራ አሳለፈ፡፡ ከእርሱም ጋር አንድም ሰው አልነበረም፡፤ በመከራው ጊዜ ብቻውን ቢሆንም እርሱ ግን በመሀሪነቱ አንዳቸውንም አልተወም፡፡ አንዳች ረዳትና አጋዥ ሳይኖረው በመከራውና በችግሩ ብቻውን ነበር፡፡ ኢሳ 63÷3፡፡

በጌቴሴማኒ በአትክልት ቦታ ወደ አባቱ ጸለየ፡፡ በቅንነት "አባት ሆይ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ" ሲል ተናገረ፡፡ ሉቃ 22÷42 ነገር ግን የሚወዳቸው ደቀመዛሙርቱና ወዳጆቹ ብቻውን ትተውት ተኝተው ነበር፡፤ ወደ ሦስት ጊዜ ወደ እነርሱ በመመለስ እንዲጸልዩ ጠየቃቸው ነገር ግን ለአንድ ሰዓት ያህል እንኳን ከእርሱ ጋር ሊተጉ አልቻሉም፡፡ ማቴ 26÷38-45



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ጌታ በተያዘ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ እያንዳንዳቸው ተበታትነው ወደ ቤታቸው ሄዱ:: ዮሐ 16÷32:: እርሱ ለብዙ ኃጢአተኞች ተሟጋች ሆኖ ሳለ እርሱ በተጠየቀ ጊዜ አንዳች ጠበቃ አልነበረውም:: በመከራው ጊዜ ማንም አላጽናናውም:: ስንሰደድ፣ ብቸኝነት ሲሰማን፣ ወዳጆቻችን ናቸው ያልናቸው ሰዎች እንኳን ሲጠይቁንና ራሳችንን ብቻውን በምናገኘው ጊዜ ይህ ከጌታ የምንማረው ታላቅ ትምህርት ነው::

ጌታ በመከራው ጊዜ ብቻ አልነበረም ብቻውን የተተወው፤በዘመነ ሥጋዊው ሁሉ እንጂ:: አንድ ጊዜ በቤተ መቅደስ ውስጥ ሳለ ስለ ሥጋና ደሙ መስጠት እየነገራቸው ሳለ ነገር ግን ደቀመዛሙርቱ ይህን መረዳት አልቻሉም ነበር:: ወንጌላዊው ዮሐንስ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ ወደ ፊትም ከእርሱ ጋር አልሄዱም:: ኢየሱስም ለአስራ ሁለቱ:- እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁ? ሲል የተናገረው ይህን አይደለምን? ዮሐ 6÷፷፯::

በሌላ አጋጣሚ ሰዎችን ራት ጋበዘ:: ነገር ግን ሁላቸውም በአንድነት ያመካኙ ጀመር:: ከእነርሱም ፊተኛው መሬት ሰለገዛና ሄዶ ማየት ስላለበት፣ ሌላኛው አምስት ጥማድ በሬዎች ስለገዛና ስለሚፈትናቸው፣ ሦስተኛውም አዲስ ሙሽራ ስለሆነ ሁሉም በግብዣው ላይ መገኘት እንደማይችሉ ገለጹለት ሦስቱም ምንም እንኳን የግብዣው ተጠቃሚ ቢሆኑም እንኳን ይቅርታ እየጠየቁ ቀሩ::





ብቻውን ስለተተወው ስለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማውራት ጊዜው አይበቃም:: "የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም" ዮሐ 1÷11:: እርሱም ይህ ብርሃን ነበር ብርሃን ወደ አለም ስለመጣ ሰዎች ሥራቸው ክፉ ስለነበር ከብርሃን ይልቅ ጨለማን መረጡ:: በዮሐ 3÷19 ::

ይህ ሁሉ በፊት ተደርጎ አልፏል፣ አሁንም እየተደረገ ነው:: ያ! ጥንት የነበረ ጌታ ከበፊቱ ጋር በሚመሳሰል አሁንም ድረስ በፊታችን ብቻውን ቆሟል:: ነገር ግን አንድም ሰው ክርስቶስን ያሰበ የለም:: ነገር ግን አንድም ሰው ክርስቶስን ያሰበ የለም:: ነገር ግን ፀጉ ዕድልን መረጠች የተባለላት የማርታ እህት ማርያም ከእግሩ ሥር ተቀምጣ ቃሉን ትሰማ እንደነበር፤ ደረቱን እንደተደገፈው እንደዘብዴዎ ልጅ እንደ ዮሐንስ ከእግሩ ሥር ተቀምጦ ቃሉን ለመስማት ማንም አልተቀመጠም:: እግሩንም እንዳጠበችው እንደ ኃጢያተኛዋ ሴት ማንም አላደረገም:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ይህንን ብቸኝነት፣ ብዙኀኑም ትተውት እንደሚሄዱ ያውቅ ነበር:: በቃሉም የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነት ያገን ይሆን?
ሉቃ 18÷8 ሲል በአድናቆት ተናግሯል::

አንተስ? አንተም ክርስቶስን ብቻውን እየተውከው ነው? ከእርሱ ሊለይህ የሚችል ነገር አለን? አስኪ ራስህን መርምር::



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



## በሀሳቡ ልዩ ነበር፡-

ከዋለበት የሚውሉ ካደረበት የሚያድሩ ደቀ መዛሙርቱ ሳይቀሩ እንኳን በሐሳባቸው ከእርሱ ጋር የማይስማሙበት የራሳቸው ግንዛቤ ነበራቸው፡፡

ጌታ ወደ ሳምራውያን መንደር ከያዕቆብና ከዮሐንስ ጋር በሄደ ጊዜና በዚያም ባልተቀበሉት ጊዜ እነዚህ ደቀመዛሙርት "ጌታ ሆይ እሳት ከሰማይ እንዲመጣና እንዲያጠፋቸው እድናዝ ትፈልጋለህ?" አሉት፡፡ እርሱ ግን "ምን ዓይነት መንፈስ እንደሆነላችሁ አታውቁም፤ የሰው ልጅ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም፡፡" ሉቃ 52-6 ሲል ገሰጻቸው፡፡

እነዚህ ሁለት ደቀ መዛሙርት ከመልካም መምህራቸው ተለይተው ያስቡ ነበር፡፡ ምክንያቱም እርሱ ከዚህች ከተማ ብዙዎችን እንደሚመርጥ ያውቅ ነበረ፡፡

ይህ የደቀ መዛሙርቱ ክፉ ሀሳብ ከተቃዋሚዎቻቸው ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን የመነጨ ነበር፡፡ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሀሳቡ ከእነርሱ ልዩ ነበር፡፡ ጌታ ግን እጅግ ይወዳቸዋል፤ ይራራላቸዋል፤ ወደ እርሱም ሊያቀርባቸው ይፈልጋል ስለዚህ ስለመልካሙ ሳምራዊ ነገራቸው

ጌታ በተጨማሪም ለአህዛብ የተለየ አመለካከት ነበረው፡፡ በአይሁድ ዘንድ የተናቁና የተወገዙ የሆኑትን እኒህን አህዛብ ጌታ በግልጽ ያመሰግናቸው ነበር፡፡ "እውነት እላችኋለሁ በእስራኤል እንኳን እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም" ማቴ 8÷10





በማለት የከነናዊቷንም ሴት እምነት ሲያደንቅ እንመለከታላን፡፡ ማቴ 15÷28፡፡

በዕለት ተለት ኑሮው ሌሎች የተለያየ መንገድ ቢኖራቸውም ጌታ ግን ከሌሎች የተለየ የራሱ መንገድ ነበረው፡፡ በዝሙት ኃጢአት የተያዘችውን ሴት አይሁድ በአንድ ሀሳብ ሊወግሯት በዙሪያዋ በተሰበሰቡ ጊዜ እርሱ ግን ከእነርሱ በተለየ መልኩ ያስብላት ነበር፣ "ከእናንተ ማንም ኃጥያት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት አላቸው" ከታናሽ ጀምሮ እስከ ታላቅ ድረስ ትተዋት ሄዱ "እኔም አልፈርድብሽም፣ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጥያት አትስሪ " አላት ዮሐ 8÷7-11

ውጫዊውን ማንነት ብቻ አይታ በምትፈርድ ዓለም ውስጥ የውስጥ ማንነትን መረዳት የሚችል እርሱ ብቻ ነበር፡፡ አለምም በእርሱ እጅግ ተደነቀች፡፡ ይህም በሚከተሉት ሁለት ድርጊቶች የሚረጋገጥ ነው፡፡

አንድ ጊዜ ጌታ ከኢያሪኮ እየሄደ ሳለ ሁለት ዐይነ ስውር በመንገድ ላይ ተቀምጠው ጌታ እንዳለፈ በሰሙ ጊዜ በመጮህ "የዳወዊት ልጅ ማረን" አሉ፡፡ ይከተሉ የነበሩት በአለማዊ ሀሳባቸው የዐይነ ስውሮቹ ጩኸት የክብርን ጌታ ያውከዋል ብለው ዝም ይሉ ዘንድ አስጠነቀቋቸው፤ ርኅሩህ የሆነው ጌታ ግን ለሁሉም እንደሚያደርገው ጠራቸውና ዐይናቸውን አበራ፡፡ ማቴ 20÷29-34 ጌታም በእነዚህ ሰዎች የልመና ጩኸት ምንም አልተቆጣም፡፡



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



አንድ ጊዜ ተመሳሳይ ነገር ተደረገ:- ህፃናት ጌታን ከበው ሳለ ደቀ መዛሙርቱ ጌታ ይበሳጫል በማለት ህፃናቱን ገሰጿቸው:: እርሱ ግን "ህፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው፣ መንግሥተ ሰማይ እንደእነርሱ ላሉት ናትና" አላቸው ማቴ 19÷14

<u>አገልግሎቱ በተለየ ዓይነት መልኩ ነበር</u>

እስራኤላውያን ጌታ ንጉሠ ነገሥታቸው እንዲሆንና ከሮማውያን ቅኝ ግዛት ነፃ እንዲያወጣቸው እያሰቡ ሳለ እርሱ ግን በተለመደው መንፈሣዊ ንግሥና የሰዎችን ልቡና ዙፋኑ አድርጎ እንደሚገዛ ያስብ ነበር:: "መንግስቴም ከዚህ ዓለም አይደለችም" ዮሐ 18÷36 ሲልም በብዙ አጋጣሚ ይገልጽላቸው ነበር

ስለዚህ አገልግሎት ማለት ከአገልግሎቱ ብዛት ብዙ ውጣ ውረድ ያለበት መከራ ወይም የመስቀል ጉዞ እንደሆነ ያውቃል:: ነገር ግን ይህን ሀሳብ ሐዋርያቱ እንኳን አልተገነዘቡትም ነበር::

ስለዚህ:- ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም ይሔድ ዘንድ ከሽማግሌዎችና ከካህናት አለቆች ከዳኞችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጽላቸው ጀመር:: ሐዋርያው ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ "አይሁንብህ ጌታ ሆይ ይህ ከቶ አይደርስብህም" ብሎ ይገስጸው ጀመረ:: እርሱ ግን "ወደ ኋላዬ ሂድ አንተ ሠይጣን" በማለት ገሰጸው ማቴ 16÷22-23::

ጌታ የዚህን የደካማውን የጴጥሮስን ምክር ተቀብሎ ቢሆን ኖሮ አለም እንዴት ሊድን እንደሚችል ሳስብ እጅግ ይደንቀኛል::





በሌላ አጋጣሚ ጌታ ከፊቱ መከራ እየጠበቀው ደቀ መዛሙርቱ ከእነርሱ ማን ፊተኛ እንደሚሆን ይወያዩ ነበር:: ከዚያም የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከልጆቿ ጋር መጣችና እየሰገደች ጌታዬ ሆይ ልጆቼ በመንግስትህ አንደኛው በቀኝህ አንደኛው በግራ እንዲቀመጡ እዘዝ ስትል ለመነችው:: እርሱ ግን "የምትለምኑትን አታውቁም እኔ ልጠጣው ያለውን ጽዋ ልትጠጡ፣ እኔ የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁ?" ማቴ 20÷20-22 ሲል የአገልግሎቱን ትክክለኛ ሀሳብ ገለጸላቸው::

ጌታ ስለ እውነተኛ አገልግሎት ከሰው በተለየ ያስብ ነበር:: ስለ ቃሉ ለሕዝቡ ለብዙ ሰዓት እየነገራቸው ሳለ በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እሱ መጥተው "ሰዓቱ አልፏል ወደ መንደሮች ሄደው ለራሳቸው ምግብ እንዲገዙ ህዝቡን አሰናብት" ማቴ 14÷16 አሉት:: ሆኖም ደቀ መዛሙርቱ የጌታን አገልግሎት በቃል ብቻ የሚወሰን ስለአደረጉት ፍቅርና ርኅራኄ ያልታከለበት መሰላቸው::

ስለዚህም ጌታ:- "እናንተ የሚበሉትን ስጧቸው እንጂ ሊሄዱ አያስፈልግም" ሲል ርኅራሄውንና ፍቅሩን ገለጸላቸው::

<u>ብቻውን ያገለግል ነበር</u>

አለም እርስ በእርሳቸው በሚቀናቀኑና በሚለያዩ አገልጋዮች ተጨናንቃለች እያንዳንዱም ሰራተኛ ረዳትና አጋዥ ይፈልጋል:: የክብርም ጌታ በመዋዕለ ስብከቱ "መኸሩ ብዙ ነው፤ ሠራተኞቹ ግን ጥቂት ናቸው:: እንግዲህ የመኸሩ ጌታ ወደ መኸሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት ማቴ 9÷37-38 ሲል አሁን



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ድረስ ይናገራል ጌታ በስራው የረዳው አንድም አጋዥ አልነበረውም እያንዳንዱ ሰው እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝ? ሲል የመልስ መልስ ይሰጣል:: ውድ ወንድሜ አሁን እዚህ ውስጥ ጥቂት መንስዔዎች አሉ:: እራሴንም ተመልክቼበታለሁ::

በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ደሃ ባልና ሚስት ነበሩ:: የበኩር ልጃቸው ታዳጊ ነበር፤ ተከታዩ ደግሞ ገና ህፃን ነበር:: የቤተሰቡም የገቢ ምንጭ አባወራው ሎሚ ነግዶ ከሚያገኘው ለዚያውም ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሯቸውን ከማይሸፍን ከጥቂት ገንዘብ አያልፍም ነበር:: ብዙ ጊዜ የሚላስ የሚቀመስ አይኖራቸውም:: እናቲቱም ህፃናት ልጆቿን አዝላ ወደ ህፃናት ማሳደጊያ ለልመና ትሰማራ ነበር:: ጥቂቱን የገላቸውን ክፍል እንኳን ስለማይሸፍነው ልብሳቸው ልነግርህ አልሻም:: የበጋውን ሐሩር የክረምቱን ቁር እንዴት እንደሚቋቋሙት እግዚአብሔር ይወቀው! ከዚህ በተጨማሪ የሚኖሩበት የኪራይ ቤት የዋጋ ንረት እርሱ ይመልከተው! የቤቱን ባለቤት ዘለፋና እርግማን እንዲሁም ዛቻ ተቋቁመው እንዳያባርሯቸው በመስጋት የሚኖሩትን የሰቀቀን ኑሮ እርሱ ይቁጠረው!

በአንድ የሐይማኖት ተቋም ውስጥ የልብስ ስፌት ሥራ እየሰራች ልጆቿን የምታሳድግ የአንዲት መበለት ታሪክ እነሆ ይህች ሴት በምግብ እጦት ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ለ2 ወር ያህል ታመመች:: በዚህ ምክንያት ይህ የሃይማኖት ተቋም ከሥራዋ አገዳት:: እንዴት ህክምናውን እንዳገኘች ወይም ገንዘብ እንዴት እንዳገነች አላውቅም ደህና በሆነች ጊዜ በጨለማ ተከባ ራሷን ብቻውን አገኘችው::





ብዙ ተመሳሳይ ምሳሌ መናገር ይቻላል:: ጌታ ኢየሱስ ግን ስለ ሁሉም ጥበቃ በማድረግ፣ ምግብን በመስጠት፣ ከደዌያቸው በመፈወስ የትዕግስትንና የመከራን ኑሮ እያስተማራቸው ከእነርሱ ጋር ይኖራል:: ምንም እንኳን ኃጢያተኛ ብንሆንም የዚህን አገልግሎት ክብር እንድንካፈል ይፈልጋል:: ይሁን እንጂ አዝመራው ብዙ ሠራተኞቹም ጥቂት ሆነው አገኛቸው:: ሁላችን እርሱን ትተን ወደ የራሳችን የአገልግሎት መስክ ተበታትነን አገኘን::

<u>ጌታን በመተው የሚጎዳ ጌታ ወይስ?</u>

እኛ ብንተወውም እንኳን እርሱ ብቻውን አይደለም:: ምክንያቱም አባቱ ከእርሱ ጋር ነውና:: በተጨማሪም እርሱ የእኛን እገዛ አይሻም:: እኛ ግን እርሱ ጌታችን እንዲሆን እንሻለን:: በዚያም የመለኮቱ ባህርይ ተካፋዮች እንሆናለን::

በብቸኝነት ከእርሱ ጋር እንድንሆን በሚጠራን ጊዜ የእኛን ጥሩ ነገር ስለሚሻ ነው:: ምክንያቱም *"እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል* ሮሜ 8÷31:: በእረግጥም ከክርስቶስ ጋር የሚሄድ መንፈሣዊ ደስታን ያገኛል:: ስለዚህ *"ከጥላው በታች እጅግ ወድጄ ተቀምጬአለሁ"* ተብሏል መኃ.መኃ.ስሎ 2÷3:: ከክርስቶስ ጋር የሆነ እርሱ ክፉውን አይፈራም:: መዝሙረኛው ቅ.ዳዊት "በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉውን አልፈራም በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያድኑኛል:: መዝ 23÷4" "ሰራዊት ቢሰፍርብኝ ልቤ አይፈራም መዝ 27÷3 ይላል::



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



እነሆ ክርስቶስ ድምጹን ሰምተህ እንድትከፍትለት ከዚያም ወደ አንተ ሊገባና ከአንተም ጋር ራት ሊበላ በመፈለግ የቤትህን ደጃፍ ያንኳኳል። ራዕ 3፥20

አሁንም እርሱን ብቻውን ልትተወው ትፈልጋለህ?





# ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ህብረት አለው? 1ኛ ቆሮ 6፡14

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ። ምድርም ባዶ ነበረች አንዳች አልነበረባትም፤ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበር፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር። እግዚአብሔርም፦ «ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ እግዚአብሔር ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ። እግዚአብሔር ብርሃንና ጨለማን ለየ። እግዚአብሔር ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው፣ ጨለማውንም ሌሊት አለው።» ዘፍ 1፡1-5

ጌታ ሆይ አንተ ጨለማ አይሁን አላልክም። ነገር ግን ብርሃን ይሁን አልክ እንጂ፤ ብርሃንም ሆነ። ነገር ግን በብርሃን መፈጠር ጨለማ ህልውናውን አላጣም። ሁለቱም በየራሳቸው ይኖሩ ጀመር።

ብርሃንን መልካም ሆኖ ካየኸው ለምን ጨለማን አላስወገድከውም? ለምንስ ህልውናውን አጸናህለት? ጨለማ የሚል አጠራርስ ለምን ሰጠኸው? እንዳልከውስ «ነገር ግን የጨለማ ግዛትና ዘመን ነው» ስትል ኃይልን ለምን ሰጠኸው?

አንተ የማይቀርበው ብርሃን ሆነህ ሳለ ጨለማን አስወግደህ ሌትና ቀኑን በብርሃን ለምን አላፈራረክም? ለምንስ ህልውናውን አጸናህለት? ለምንስ ሰዎች ከብርሃን ይልቅ ይመርጡታል? ጨለማ በዚህ ዓለም ከመታወቁ በፊት እንዳይታወቅ ማድረግ ይቻልሃል፤ ከታወቀም ቡኋላ ማስወገድ ይቻልሃል። የጨለማን መኖር ብትፈቅድም ፈጽሞ ከአንተ ባህርይ ጋር አይስማማም። ለምን ይሆን እንዲህ ያደረከው?«እንክርዳዱን ስትለቅሙ ስንዴውን ከእርሱ ጋር እንዳትለቅሙ አይሆንም። እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ። በመከር ጊዜም አጫጆችን እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ንቀሉ በእሳት ለማቃጠል በየነዶው እሰሩ ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ ማቴ 13፡29 ስትል የእንክርዳዱን ፍጻሜ እንደተናገርከው ስለዚህ ጨለማ ህልውናውን የሚያጣበት ጊዜ አለው? በጨለማ ውስጥ የሚኖሩ የብርሃን ልጆች መቅረብ ከማይቻላቸው



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



*ከእውነተኛ ብርሃን ከአንተ ጋር መች ይሆን ህብረት የሚፈጥሩት? ኃጢአተኞች በጥቅሉ ጨለማ ውበጥ ይጣላሉ እውነት አይደለምን?ስለዚህ ይህ ጥልቅ ጨለማ ዘላለማዊ ነዋ በእርግጥ ልክ ነው። ነገር ግን ከሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም የተለየ ዓለም ነው። የእግዚአብሔር ልጆች ካሉበት በእጅጉ ይርቃል።*

## ጨለማ ካለመኖር ወደ መኖር መቼ መጣ?

«ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበር» ይህ እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን ከማለቱ በፊት ነው» ታዲያ መቼ ይሆን?

እግዚአብሔር በዘላለማዊ ክብሩ ሳለ ጨለማ አልነበረም፤ ምክንያቱም እርሱ ብቻ ነበር እንጂ አንዳች ፍጥረት አልነበረምና። እርሱም እውነተኛ ብርሃን ነው። ጨለማስ ወዴት ነበር? የተፈጠረውስ መች ነው? እንዴት ተፈጠረ? ለምንስ ተፈጠረ? አምላኬ ሆይ ስለዚህ ሁሉ ዕውቀት ስለሌለኝ እባክህ አሳውቀኝ።

በተፈጥሮ ሂደት ውስጥ ጨለማ ብርሃንን ይቀድማልን? ብርሃን ቀድሞ ስለመገኘቱ ጥርጥር የለውም። ጨለማ አካል ገዝፎ የመጣው የጸሐይ ብርሃን በውሃ ላይ ባረፈ ጊዜ በሚፈጠረው የትነት ውጤት ነው። ስለዚህ ውሃዎች በፍጥነት ይተናሉ ይህም የፀሐይን ብርሃን የሚጋርድ ጭጋግና ጉም ይፈጥራል። ስለዚህ የፀሐይ ብርሃን ተጋረደ ማለት የጨለማን መኖር አስከተለ። ይሁን እንጂ ይህን ዓይነቱ የዕውቀት መንገድ አልከተለውም። ይልቁንም ስለብርሃን መኖር ለማወቅ ብጥር ይሻለኛል።

«ጨለማ በጥልቁ ላይ ነበር» ይህ ማለት ጨለማ በውሃና በምድር ላይ ነበር።

ምድርም ሆነች ውሆች እግዚአብሔርን አያውቁትም። ይህ አለማወቃቸው ማንን የሚመለከት ነው። እግዚአብሔር ወይስ ጨለማን?

የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሃ ላይ ሰፍፎ ነበር። ነገር ግን ውሃ እግዚአብሔርን አላወቀም። ይህ በሐዋርያው «ብርሃን በጨለማ ይበራል፣ ጨለማም አላሸነፈውም» ዮሐ 1:5 እንዳለው። ውሃም እግዚአብሔርን ለማወቅ ብርሃን የሚያስፈልገው አይደለምን? ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ አለ «ብርሃን ይሁን» ብርሃንም ሆነ። ይህ «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የሰማያትም ጠፈር የእጆቹን ሥራ ያወራሉ።» መዝ 19:1 ከሚለው ጥቅስ ጋር ይዛመዳል።

ይህ ብርሃን በመጀመሪያ ወደ ዓለም የገባው ብርሃን ነው? አሁንም ድረስ አለ። በእርግጥ አሁንም ድረስ ቢኖርም እንኳን ጨለማን አላሸነፈውም። የጨለማ መኖር ለምን አስፈለገ። አምላኬ ሆይ የምረዳበትን ነገር አጥብቄ እጠይቅሃለሁ። አእምሮዬንም ብሩህ አድርግልኝ የህይወት ቃልንም እቀበል ዘንድ ልቤን ክፈት።

ከዚህ ብርሃን ውጭ ብዙ ብርሃናት አሉ። ይህም የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብትን ብርሃን ነው። ጌታም ደቀመዛሙርቱን «እናንተ የአለም ብርሃን ናችሁ» ሲል ስለሌላ ብርሃን ሲናገር እናያለን። እግዚአብሔር ወልድም ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ነው። ከዚያም «ፀጋና እውነትን ተሞልቷ በእኛ አደረ» ዮሐ 1:14 ክብሩንም አየን። ማንም ያላየው አባትም ሊቀርቡት የሚይቻል ብርሃን ነው። የሰው ልጅ ህገ እግዚአብሔርን ሲፈጽም እርሱ የብርሃን ልጅ ይባላል። በአጠቃላይ መልካም ነገር ሁሉ ብርሃን ነው። ጽድቅ፣ጥበብን፣ ዕውቀትን የመሳሰሉትን ያካትታል።

በስነ-ፍጥረት ታሪክ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ብርሃንን በስሜት ህዋሳችን እንድንረዳው አድርጎ ፈጠረው። ብርሃንንም መልካም እንደነበረ ተመለከተ። ይሁን እንጂ በመንፈሱ ውስጥ የሰው ልጅ እግዚአብሔርን እስኪያገኝ ድረስ በውስጡ የሚሰራ ሌላ ብርሃን ሰላለ ያኛው ብርሃን ከዚህኛው ብርሃን የተለየና ዝቅተኛ ነው። ታዲያ የዚህ ዝቅተኛ ብርሃን ተፈጥሮው ምንድነው? ሰው ከተፈጠረ በኋላስ የዚህ ብርሃን ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነቱ ምን ይሆን? እግዚአብሔር ብርሃን ነው። የሰው ልጅ መልካም የሆነው ሁሉ እንዲበራለት እግዚአብሔር የመለኮታዊ ባህርዩ ተከፋይ አድርጎታል። ነገር ግን ይህ ብርሃን በቸርነቱ የሚሰጥ እንጂ ከመለኮቱ የሚከፈል አይደለም።

ነገር ግን እግዚአብሔር የብርሃንን መልካምነት ለምን ተመለከተ? ምክንያቱም ከእርሱ ብርሃን ጋር የሚተካከል አልነበረምና። እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ጨለማም በእርሱ ዘንድ አይኖርም። እርሱ ባለት ሁሉ በዚያ ብርሃን ይሆናል። በዚህ





www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ብርሃን የማይመላለስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ይርቃል፤ ወደ ጥልቁም ይወረወራል።

አሁን አንድ ነገር ልጠይቅህ እወዳለሁ፤ እግዚአብሔር ጨለማን ከብርሃን ከለየ ጨለማ እንዴት ወደ ሰው ገባ? እንዴትስ ሊቆይ ቻለ? እንዴትስ ሰው ከብርሃን ይልቅ ይመርጠዋል? ነገር ግን የጥያቄውን መልስ ለእያንዳንዳችን እተዋለሁ።





# የጽሞና ጊዜ

ጌታዬ ሆይ ከራሴ ጋር ብቻዬን የምሆንበት ሰዓት በእርግጥ የተቀደሰ ሰዓት ነው። ብቻዬን በምሆንበት ጊዜ ባላይህም አንተ ከእኔ ጋር ስለሆንክ እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ። ይህ እንግዳ ነገር አይደለም፤ አንተ በዓለም ሳለህ አለም ግን አላወቀህም።

በዚህ ዓለም ሳለሁ ትልቁ ኃጢአቴ ብቸኝነትን መጥላቴ ነው። ብቻዬን ከራሴ ጋር የምቀመጥበት ጊዜ አልነበረኝም፤ ከራሴ ጋር ወይም ከአንተ ጋር እንድሆን የተሰጠኝን አማራጭ አልተጠቀምኩበትም። አወይ አለማወቅ ከራሴ ጋር ብቻዬን መቀመጤ ስንፍና ስለሆነብኝ ትርፍ ጊዜዬን ለማሳለፍ አዲስ ነገርን ተመኘሁ።

በአለም በምኖርበት ጊዜ በሀሳብ ደረጃ በብቸኝነት ከራሴ ጋር የመሆንን ጥቅም እረዳ ነበር፤ በተግባር ግን ቦታ አልሰጠሁትም። ይልቁንም ዲያብሎስ ትርፍ ጊዜ እንዳይኖረኝ ያብከነክነኛል።

ስለዚህ ጌታዬ ሆይ በውስጤ ያለውን የተሰወረ ዕንቁ አላወኩም። ያውም አንተን! ብቻዬን ብዙ ጊዜ በምቀመጥበት ጊዜ በውስጤ ያለኸውን አንተ. በግልጽ ትመጣብኛለህ፤ እኔም ለብዙ ሰዓት አንተን ለመሸሽ ብቸኝነቴን እጠላዋለሁ። በእርግጥ ከአንተ የማስቀድማቸው ብዙ ነገሮች ነበሩኝ፡- ይኸውም አስቀድሜ አባቴን ልቀብር፣ እርሻዬን ልጎበኝና በሬዎቼን እፈትን ዘንድ እወድ ነበር።

ነገር ግን በስተመጨረሻ ጌታ ሆይ አንድ ቀን የጽሞና ጊዜ ወስጄ ለብቻዬ ተቀምጬ ሳለሁ በውስጤ የተሰወረውን ዕንቁ አንተን አገኘሁ። ከዚያም ያለኝን ሁሉ ሸጬ ያንን ዕንቁ ገዛሁት። ያም ዕንቁ አንተ ነህ። ስለዚህ ከዚያን ሰዓት ጀምሮ አንተ የእኔ ነህ።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



## <u>የንስሐ ቃሌን ለአንተ እሰማለሁ።</u>

ብቻዬን በማሳልፋቸው ሰዓታት ሁሉ ከዚህች ዓለም ይልቅ የከበርኩ ፍጥረት እንደሆንኩ ይሰማኛል። አንተ «ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ቢጎዳ ምን ይጠቀማል» ማር 8፡36 ስትል እንደተናገርከው።

ሁሌም ክቡር ፍጥረት መሆኔን ሳስብ አለምን አጥብቄ እጠየፋታለሁ፤ እያንዳንዱንም ነገር ለመናቅ ኃይልን ከአንተ እወስዳለሁ። የዓለምን ነገር ሁሉ በምንቅበት ጊዜ «ከአንተ ጋር ስለሆንኩ አትፍራ» ዘፍ 26፡26 በማለት ታበረታታኛለህ።

ከራሴ ጋር ብቻዬን በምሆንበት ጊዜ ውስጡን ስረዳና በውስጡ ያለውን እንግዳ ነገር ስመለከት በውስጡ ያለውን ቅድስና ላረክስ ተዳፈርኩ። ሁሉንም ነገር ላንተ እናገራለሁ ከባዕዳን እጅ እንድታድነኝ እጠይቅሃለሁ። ጊዜው በፍጥነት እያለፈ ነው፤ አሁንም የምነግርህ ብዙ ነገር አለኝ። ለእኔም የምለው አለኝ። ስለዚህ ከሌሎች የማገኘው መጽናናት በእኔ ዘንድ ዋጋው ጥቂት ነው። በህብረትና በማህበር ደስታንና ተድላን ማፈራረቅ አልሻም። ይልቁንም በብቸኝነት፣ በገለልተኝነትና በጽሞና ጊዜ መጽናናትን አገኛለሁ። በዚህ ጊዜ አንተ ከኔ ጋር ነህና ይህን ብቸኝነት እንደ ብቸኝነት አልቆጥረውም።

ብቻዬን በጽሞና በምቀመጥበት ጊዜ የእኔን ትክክለኛነት አገኛለሁ። በፊትህም አመድና ትቢያ መሆኔን አረጋግጣለሁ። ስለዚህ እራሴን ባዶ አደርጋለሁ፤ የዓለምም ክብር እኔነቴን ሊቀይር የማይችል የውሸት ገጽታ እንዳለው ይሰማኛል።

ብቻዬን ስቀመጥና ምን ያህል ደካማ እንደሆንኩ ሳስብ ከአንተ ውጭ ምንም ነገር ማድረግ አለመቻሌን በመገንዘብ ወደአንተ በፍጥነት እገሰግሳለሁ። ዕለት ዕለት ወደአንተ ግስጋሴዬ አንተ እንድትገለጽልኝና መጠጊያ እንድትሆነኝ ነው። ይህ እጅግ እንድወድህና ከሰዎች ጋር ከመሆን ይልቅ ከአንተ ጋር መሆንን እንድመርጥ ያደርገኛል። በየአንዳንዱ ጊዜ ስለአንተ አዲስ ነገር አገኛለሁ፤ በዚህም ነፍሴ ወደአንተ ይበልጥ እየቀረበች ትመጣለች።





እባክህ ጌታ ሆይ ሰዎችን እንድተውና እራሴን ከአንተ ጋር አንድ እንዳደርግ፣ እራሴን እንድረሳና ሐሳቤን በአንተ ላይ እንዳደርግ እርዳኝ። ይህ ለእኔ እጅግ መልካም ነውና።



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



# ቅድስና

አእምሮዬ ውስን ነፍሴም ፍጡር ስለሆንና በሥጋ ምኞት የተያዝኩ ሥጋ ለባሽ ስለሆንኩ ወደ አንተ መምጣት በምፈልግበት ጊዜ የሥጋ ፍቃዴ ያግደኛል:: ይሁን እንጂ አንተ ወደኔ መጣህ::

ጌታ ሆይ በሥጋ ስራዎች እባክናለሁ፤ ብዙ ፍላጎቶችም ያደናቅፉኛል:: በምኞቴም ምክንያት ይህን ንዝህላልነት በራሴ ለማስወገድ አልጥርም፤ ነገር ግን በኃጢአት ላይ ኃጢአት እጨምራለሁ:: ስለዚህ ጌታ ሆይ አንተ ወደኔ ልትመጣ እንጂ እኔ ወደ አንተ ልመጣ አልችልም:: ጌታ ሆይ ናና እራስህን ግለጽልኝ:: አገልጋይህና ልጅህ የሆንኩትን እኔን ጎብኘኝ:: አንተ እውነተኛ አፍቃሪ ነህ፤ አንተ ፍቅር ነህ::

ጌታ ሆይ «እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ሠራተኞቹ በከንቱ ይደክማሉ»:: መዝ 127:1:: ነቢዩ እግዚአብሔር ዳዊት እንዲህ ካለ ለአንተ ማደሪያ የማዘጋጅ እኔ ማነኝ? ቅድስት ኢየሩሳሌምን የመሠረትክ አንተ አይደለህ! ስለዚህ ጌታ ሆይ እኔን አትጠብቅ፤ አንተ ና:: እንዳትዘገይ::

እኔም በራሴ ላውቅህ አልችልም:: ጌታ ሆይ አንተን የማውቅህ በአንተ እርዳታ እንጂ የኔ ጥረት ዋጋ የለውም:: በምትሰጠኝ ፀጋም አውቅሃለሁ:: በፍቅርህ አንተነትህን ትገልጽልኛለህ::

ነገር ግን አንተን ካልወደድኩህ እንደማትገለጽልኝ አውቃለሁ:: ስለዚህ አንተነትህን ካልገለጽክልኝ እንዴት እንደምወድህ ንገረኝ ለአንተ ያለኝ ፍቅር እንዲጨምር አንተነትህን ግለጽልኝ:: ምክንያቱም በወደድኩህና በቀረብኩህ መጠን አይሃለሁና::

ስለዚህ ራስህን የምትገልጥበት ተቀዳሚው መንገድ ጸሎት ስለሆነ አንተነትህን ትገልጽልኝ ዘንድ እጸልያለሁ:: ከሌሎች ሰዎች አልያም በመጻሕፍት አማካኝነት እንድትገልጽልኝ አይደለም:: ነገር ግን ሐዋርያው «በዓይኖቻችን ያየነውን የተመለከትነውን እጆቻችን የዳሰሱትንም...» 1ኛ ዮሐ 1:1 እንዳለው እንደዚሁ እራስህን ግለጽልኝ::





ከቅዱሳት መጻሕፍትና አንተን ከሚያውቁህ ሰዎች ስለአንተ በቂ እውቀትን ማግኘት አልችልም:: ከአንተ ጋር አብረው ያድሩና ይውሉ የነበሩት ደቀመዛሙርትህ እንኳን ስለአንተ በቂ ማብራሪያ ለመስጠት ያዳግታቸዋል:: የሚናገሩበት ቃልና አንደበት ያጥራቸዋል:: ማድረግ የሚችሉት ነገር ቢኖር እያንዳንዱን ሰው ስለአንተ በጥቂቱ የቅምሻ ያህል እንዲያውቁ ማድረግ ብቻ ነው:: «እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ እዩም...» መዝ 34:8:: ስለዚህ ስለራሳችን እውቀት ሳይቀር ግልፅ የሆነ ነገር ማስቀመጥ አይችሉም:: ይህ እንኳን ከአእምሯቸው በላይ ነው::

ይሁንና ጌታ ሆይ ራስህን ብትገልጽልኝ እንኳን ያለቅድስና ማንም ሊያይህ አይችልምና እንዴት ላይህ እችላለሁ? ቅድስናን ስጠኝ ምክንያቱም የሥጋ ፍላጎቴ በራሴ ላይ ስለሰለጠነብኝ ቅድስና ከእኔ አቅም በላይ ነው::

ዘወትር እስካከልማለሁ:: ዘወትር ማግኘት የምናፍቀው ነገር ቢኖር ቅድስናን ነው:: ይህ ደግሞ ለእኔ ህልም ሆኖብኛል:: ነገር ግን ቅድስናን ገንዘብ ማድርግ እችል ይሆን! አንተን ፈጽሞ አላይህም ማለት ነው?:: እባክህ ጌታ ሆይ አንተን ማየት የምችልበትን የልብ ቅድስናን ስጠኝ::

«በሂሶጵ እርጨኝ እነጻማለሁ፤ እጠበኝ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ» መዝ 50:7



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



# አማኑኤል

ይህ ርዕስ ሁሉንም ሰው አይመለከትም:: የተወሰነ መንፈሳዊ ማዕረግን ይመለከታልና:: ይህ ማዕረግ የሌለው የዚህች ርዕስ ተጠቃሚ አይሆንም::

ጌታ ሆይ በነገሮች ሁሉ ጣልቃ መግባት ተፈጥሮዬ ነው:: ጣልቃገብነት ስል በሌሎች ሰዎች ጉዳይ ላይ ማለቴ አይደለም:: ነገር ግን በራሴ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ እገባለሁ:: በእርግጥ የእኔ ሕይወት እኔን ብቻ የሚመለከት አይደለም ይልቁንም አንተን እንጂ::

እኔ እራሴ የእኔ አይደለሁም፤ የአንተ እንጂ:: ምክንያቱም በከበረ ደምህ ገዝተኸኛልና:: በዚህም የአካልህ ብልት ሆንኩ:: ስለዚህ በራሴ ህይወት በብቸኝነት ጣልቃ ልገባ መብቱ የለኝም፤ ምክንያቱን በቅዱስ ፈቃድህ ትንከባከበኛለህና::

በምሄድበት ሁሉ እንድትመራኝ ሙሉ ህይወቴን ሰጥቼህ በራሴ ህይወት ጣልቃ መግባቴን የማቆመው መቼ ይሆን? በምርጫህና በስጦታህ የምረካው መቼ ይሆን?

የምጠይቀው ነገር ሳይኖረኝ ለምስጋና በፊትህ የምቆመው መቼ ይሆን? ምክንያቱም ሳለምንህ የምሻውን አውቀህ ትሰጠኛለህና::

በራሴ ጥረትና ትጋት አንዳች ነገር ያልሰራሁበትን የራሴን ትጋትና ጥረት ትቼ ሥራዎቼን ሁሉ ለአንተ የምተወው መች ይሆን? ነገር ግን እነዚያ ያበጁኝና የሰሩኝ እንዲሁም ህሙማንን ሁሉ የሚፈውሱ እጆችህን የማስታውሰው መች ይሆን?

ህይወቴን ሁሉ ለአንተ ሰጥቼ በመለኮታዊ ምሪትህ የምመራበት ጽኑእ እምነት የሚኖረኝ መች ይሆን? ምክንያቱም አንተ በባህሪህ መልካም ነህና:: ስለዚህም በስውር ስለምታደርግልኝ ነገር ሁሉ አመሰግንሃለሁ::

ጌታ ሆይ በአንተ ዘንድ ምን ያህል አላዋቂ ነኝ? አላዋቂነቴም ባልከፋ፤ ነገር ግን የአንተን መለኮታዊ አሰራር ለመገደብና የሞኝነቴን እስተሳሰብ ለማከናወን መሞከሬ የከፋ





በደል አይደለምን? በአንተ ስራ ውስጥ ዝምታን ብመርጥና የሥራዎችህ አድናቂ ብሆን ኖሮ ምን ያህል ጥበበኛ በሆንኩ ነበር:: የጥበብህን ምንጭ በተመለከትኩ ነበር::

ጌታ ሆይ ስለራሴ ካንተ ይልቅ አስባለሁ:: በራሴም በእጅጉ እታመናለሁ እንጂ በአንተ አልታመንም:: አንተን በእውነት እንዳመልክህ ይህ የእኔነት ጣዖት መች ይሰበር ይሆን? ይህን በራሴ ማስወገድ ስለማልችል እባክህ ጌታ ሆይ በኔ ዘንድ የሆነውን ጣዖት ከውስጤ አስወግድ:: ከዚያም አንተ በውስጤ ነግሰህ ትኖራለህ:: ስለዚህ እወድሃለሁ፤ በጽኑዕ እምነትም አመልክሃለሁ::

ጌታ ሆይ ስለራሴ ከማስብ ስለአንተ ባስብ፣ በራሴ ከምታመን በአንተ ብታመንና ከእኔ የልቅ አንተን ብወድ አንተን ለማወቅ ራሳቸውን እንደካዱ እንደቅዱሳን እንደምሆን ጥርጥር የለውም::

ጌታ ሆይ ከዚህ ነገር መች ነፃ ታወጣኛለህ? ከዚያስ መቼ ይሆን አንተን የማገኘው?::

ነፍሴ ከእስራት መች ትፈታ ይሆን፤ አገልጋይህንስ መቼ በሰላም ታሰናብተዋለህ? መዝ 142:7:: ሉቃስ 2:29:: ስለአንተ እራሴን አሳልፌ መቼ እሰጥ ይሆን? በዚያም በድጋሚ እራሴን አገኘዋለሁ:: ስለአንተ ህይወቴን መቼ አሳልፌ እሰጥ ይሆን? በዚህም በአንተ ውስጥ ህይወት ይኖረኛል:: ወደእራሴ ስለመለከት፣ ወደ ዓለምና ወደ ሰዎች ስመለከት አንተን የማየው መቼ ይሆን? በነገሮች ሁሉ በእኔ ውስጥ የምትሆነው መቼ ይሆን?

«እነሱም ይጠፉሉ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ፤ ሁሉም እንደልብስ ያረጃል እንደመጎናጸፊያም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጡማል አንተ ግን አንተ ነህ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም»::

እራሴን ማወቅ እንዳለብኝ ተነገረኝ፤ ነገር ግን ጌታዬ ማወቄ ለበደሎቼ ሁሉ መንስኤ ሆነ:: ነገር ግን ምን ግዜም በትጋት በተመለከትኩህ ጊዜ አንተን አይሃለሁ:: ሀሴትም አደርጋለሁ::

በሞት ጥላ ስር ብገዝም በዚያ በሁሉ ቦታ እንደማገኝህ አስባለሁ:: «በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ነህና ክፉውን አልፈራም በትርህና ምርኩዝህ እነሱም ያጽናኑኛል፤» መዝ 23:4:: ሀይወት እንዲኖረን አድርገህ ፈጠርከን፤ እኛ ግን በኃጢአታችን ሞትን መረጥን:: ይሁንና የዋህ የሆንከውንና በፊትህ ሁሉ ነገር ንጹሕ የሆነው አንተ ሞትን ድል ነስተህ የሀይወት መንገድ አደረከው:: በእውነት ትክክለኛ የሀይወት በር! አንተ «ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል ነፍሱንም ስለእኔ የሚያጠፋ ያገኛታል::» ማቴ 10:39:: በተጨማሪም «እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፣ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ::» ማቴ 16:24:: እንዳልከው::





# እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ

ጌታ ሆይ አንተ በእውነት በሁሉ ያለህ ነህ:: ደካሞች ያንተን መኖር ያምናሉ፤ በአንተም ይጽናናሉ:: ኃያላንም የአንተን መኖር ይረዳሉ:: ስለዚህ «እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ አለ» የሚለው እንደሚያስጨንቅ ሁሉ መጽናናትንና ሀሴትን ይሰጣል::

ምንም እንኳን ሀልውናህ የሚታወቅ ቢሆንም ብዙ ሰዎች መኖርህን አያውቁም:: ለዚህም ጠቢቡ ሰሎሞን ከተናገረው እንደምሳሌ ፦ «እኔም ተመለከትኩ ከጸሐይ በታችም የሚደረገውን ግፍ ሁሉ አየሁ» እነሆም የሰዎች እንባ ነበር፤ የሚያጽናናቸውም አልነበረም መክ 4:1

ታዲያ ጌታ ለምን ዝም ትላለህ

ጌታ ሆይ «አምላካችሁ የት አለ» ብለው እንዳያሳፍሩን ምህረትህን ግለጽልን፤ ስለህልውናህም ማረጋገጫ ስጠን:: ጌታ ሆይ በምሽቱ መጨረሻ ላይ ከደቀመዛሙርትህ ጋር በባህር ላይ ሳለህ ደቀ መዛሙርትህ ሲታወኩና ሲረበሹ ለምን ዘገየህ? መጽሐፍ እንደማትዘገይ ቶሎ እንደምትመጣ ይናገራል ታዲያ ለምን ትዘገያለህ?

ጌታ ሆይ ና! አትዘግይ:: ነቢዩ ዳዊትም በመዘግየትህ ግራ ተጋብቶ እንዲህ ብሏል «አቤቱ እኔን ለማዳን ተመልከት፣ አቤቱ እኔን ለመርዳት ፍጠን» ... ረዳቴ ታዳጊዬም አንተ ነህ አቤቱ አትዘግይ» መዝ 10:1-5

ጌታ ሆይ ምህረትህ እንደምትመጣ እናውቃለን:: አባት በገዛ ሥልጣኑ ያዘጋጀውን ሰዓት ማወቅ ለእኛ አለተሰጠንም::7:: ነቢዩም «ከማለዳው ሰዓት ጀምሮ እስከ ሌሊት ነፈሴ በእግዚአብሔር ታመነች» መዝ 130:6:: ሲል እንደተናገረ እኛም መምጣትህን በእምነት እንጠባበቃለን::

ጌታ ሆይ መምጣትህን በሙሉ ልብ እንጠባበቃለን፤ በኃይልና በጥበብ እንደምትፈጽመው እርግጠኛ ነን:: በትክክለኛው ሰዓት በፍቅርህ ትገልጸዋለህ:: በፊታችንም «አባቴ



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



እስከ ዛሬ ይሰራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ» ዮሐ 5:17 የሚለውን የጌታን ቃል እናገኛለን::

ጌታ ሆይ ፍትህንና መልካምነትን ስለምትወድ አድርግ! ሰዎች ለነፍሳቸው ረዳት እንዲያገኙ ህይወታቸውን በእጅህ አሳልፈው እንዲሰጡህ ሥራ! ከዚያም ሥራህን በአንክሮ እየተመለከቱ «እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል እናንተም ዝም ትላላችሁ» ዘጸ 14:14:: የሚለው መዝሙር ይዘምራሉ::

በሥራህ ይደነቃሉ፣ በልበ ሙሉነት «አምላካችን ይመጣል» አዎ በእውነት «አምላካችን ይመጣል» እያሉ ይዘምራሉ::



www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org